ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ሆነው ጉድለት አልባና ሕጸጽ አልባ መሆናቸውንም ያምናል፡፡ እንደ ተናገረው በእውነት ከሰማይ የመጣ ከሆነ፣ ሊታወቅ በሚቻልበት ስፍራ ላይ አለ ማለት ነው፡፡



## ምድብ ዘጠኝ
## ኋለኛው የዮርዳኖስ ማዶ አገልግሎት

**§ 112**
**ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ሄደ**
**(ዮሐ 10፥40-42)**

[40]ከዚያም ኢየሱስ፣ ቀደም ሲል ያጠምቅበት
ወደ ነበረበት፣ ወደ ዮርዳስ ማዶ ተመለሰ፤ በዚያም
ሰነበተ፣ [41]ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጡ፡፡ እነርሱም፣
«ዮሐንስ አንድም ታምራዊ ምልክት አላደረገም፤ ነገር
ግን ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ» አሉ፡፡
[42]በዚያም ስፍራ ብዙዎች በኢየሱስ አመኑ፡፡

በቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ላይ በኢየሩሳሌም ለሁለተኛ ጊዜ በድንጋይ ሊወግሩት ተቃርበው ሳለ (ዮሐ 10፥31-33)፣ ኢየሱስ ገዳዮቹ ከሚሆኑት ሸሽቶ በስተ ምሥራቅ ወደሚገኘው ዮርዳኖስ ማዶ አመለጠ፡፡ ይህ ግዛት በሄሮድስ አንቲጳስ ሥር ነበር፡፡ ስለዚህ የኢየሩሳሌም መሪዎች ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሊይዙት አይችሉም፡፡ ከዚህም በላይ የዚህ ግዛት ነዋሪዎች ለመጥምቁ ዮሐንስ ዘላቂ ፍቅር ነበራቸው፡፡ ይህ ፍቅራቸው ኢየሱስ የቸርነት ታምሩን ካደረገ በኋላ ወደ እርሱ ተላልፎ ነበር፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል ያለሥጋት ይኖር ነበር፡፡

**§ 113**
**መንግሥተ ሰማይ ስለ መግባት የቀረበ ጥያቄ**
**(ሉቃ 13፥22-30)**

በሉቃ 13፥21 እና 22 መካከል የዮሐንስን 10፥22-42ን ጣልቃ በማስገባት የሉቃስን የሐሳብ ፍሰት ገተነዋል፡፡ ይህ ለሁለቱ ስምምነት የሚያግዝ ቢሆንም እንኳ፣ ለሉቃስ ዐውድ ዳግም ትኩረት መስጠት አለብን፡፡ የሉቃስን መጽሐፍ ብቻ ማንበቡ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደምትስፋፋ ኢየሱስ በሰጠው ትምህርት ላይ፣ «ወደ መንግሥተ ሰማይ በሚገቡት ብዙ ሰዎች ናቸው? ወይስ ጥቂት?» የሚል ጥያቄ ማስነሣቱ

አይቀርም:: በአንድ በኩል ትልቅ ይመስላል፤ በሌላ በኩል ግን ወደዚያ ለመግባት አስቸጋሪ ነው (ከማቴ 7÷13-23 ጋር ያነጻጽሩ)::

ሉቃ 13÷22-25ሀ

[22]ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እየመራ ሳለ፣ በሚያልፍባቸው ከተሞችና መንደሮች እያስተማረ ያልፍ ነበር:: [23]አንድ ሰውም ቀርቦ፣ «ጌታ ሆይ፤ የሚድኑት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸውን?» አለው::

እርሱም እንዲህ አላቸው፤ [24]«በጠባቧ በር ለመግባት ተጣጣሩ፤ እላችኋለሁ፤ ብዙዎች ለመግባት ይፈልጋሉ ነገር ግን አይሆንላቸውም፤[25] የቤቱ ባለቤት ተነሥቶ በሩን ከቆለፈ በኋላ በውጭ ቆማችሁ ጌታ ሆይ፤ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ማንኳኳት ትጀምራላችሁ:: ...»

ሉቃስ፣ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በመሄድ ላይ ነበር ይላል:: ከኢየሩሳሌም ማምለጡን ደግሞ ከዮሐንስ እንረዳለን:: ከዚህም በላይ ሳይመለስ ለሦስት ወር እዚያው ይቆያል:: ስለዚህ ሉቃስ፣ «የኢየሱስ አእምሮና ልብ በቍርጠኝነት ያመሩት ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ነበር» ማለቱ ነው ብለን እናነባለን (ከሉቃ 9÷51፤ 13÷33-34፤ 17÷11፤ 19÷28:41 ጋር ያነጻጽሩ)::

ኢየሱስ ዮርዳኖስ ማዶ እየተዘዋወረ በሚሰብክበት ጊዜ አንድ ሰው ይህን ቀላልና ተገቢ ጥያቄ አቀረበ:- የሚድኑት ጥቂቶች ናቸው ወይስ ብዙ በማለት:: የመምህራኑ ሐሳብ የተለያየ ነበር:: ኢየሱስ እንኳን አዎ ወይም አይደለም የሚል መልስ ነበር የሰጠው:: እውነት ነው በሩ ጠባብ በመሆኑ የሚገቡት ጥቂት ናቸው (ቍ 24-28):: በሌላ በኩል ግን ብዙዎች ይድናሉ (ቍ 28-30):: ጥቂት አይሁድ የሚድኑ ይመስላል፤ ግን ብዙዎች አሕዛብ ይድናሉ (ከሮሜ 11÷11-15 ጋር ያነጻጽሩ):: ምናልባት ኢየሱስ በምሳሌዎቹ ያስተማረውን በመድገም



ላይ ነው:: ሲጀምር መንግሥቱ ትንሽ ነው፤ ሆኖም ይስፋፋል (ሉቃ 13÷18-21፤ ከቍ 64ሠ፣ ከ64ረ ጋር ያነጻጽሩ)::

በጠባቡ በር መግባት ቀላል ሥራ አይደለም:: «ተጣጣሩ» የሚለው ግሪክኛ ቃል 'አጎኒዞ' ነው:: ከዚህ «አስጨነቀ» የሚለውን ቃል እናገኛለን:: አንድ ሰው በአትሌቲክስ (በስፖርት) ውድድር ወይም ግጥሚያ ወቅት የሚያሳየውን ልዩ ጥረት ለመግለጽ አገልግሎት ላይ የዋለ ቃል ነበር:: ወደ መንግሥቱ መግባት ከባድ ነው:: ኢየሱስ በቀላሉ ትገባላችሁ የሚል ተስፋ ከቶ አልሰጠም! ጥረት፣ ትግልና ጽናት ይጠይቃል:: ስለ ኢየሱስ የድነት ስብከት በደንብ ማሰብ ይኖርብናል:: በጥረት የማናገኘው ስጦታ ነው:: ነጻ ወይም ቀላል ስጦታ አይደለም:: ብዙዎች ጥረት ባለማድረጋቸው ወደ ውስጥ በመግቢያው ጊዜ (ከማቴ 7÷13-23 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በሩ አንድ ጊዜ ከተዘጋ በኋላ ከበር ውጭ በጸጸት ይቆማሉ:: ኢየሱስ ይህን ያህል ጠባብ በር ነው፤ ይህም ሊሆን የቻለው እርሱ በጠባቡ የሚያስብ ሆኖ ሳይሆን፣ ወደ አብ መግቢያው በር እርሱ ብቻ በመሆኑ ነው (ዮሐ 14÷6)::

ብዙ ሰዎች ለመግባት ጥረት የሚያደርጉ ይመስላል:: ነገር ግን ለመግባት ብቁ የሚያደርጋቸው ነገር የላቸውም:: ኢየሱስ የሚናገረው ይህን ሳይሆን ለንስሐ ጊዜ አለ ነው የሚለው:: ከልክ በላይ ከቆየህ በእጅጉ ትዘገይ ይሆናል:: እንዲያውም የበሩ መዘጋት የሞት ምልክት ሊሆን ይችላል:: በሕይወት ሲኖር ዕድሉ ሰፊ ነው:: አንድ ሰው ከሞተ በሩ ለዘላለም ተዘግቶበታል (ዕብ 9÷27):: ጊዜው ካለፈ በኋላ፣ ከሞት በኋላም እንኳ ሳይቀር፣ መግባት ይፈቀድላቸው ዘንድ ብዙዎች እግዚአብሔርን ይለምኑታል:: የንስሐው ጊዜ ግን ያልፋል::

«እርሱ ግን፣ ማን እንደ ሆናችሁና ከየት እንደ መጣችሁ አላውቅም ብሎ ይመልስላቸዋል::»

ሉቃ 13፥25ለ-27

26«እናንተም 'ከአንተ ጋር አብረን በልተናል፤
ጠጥተናል፤ በአደባባያችንም አስተምረሃል ትላላችሁ'::
27«እርሱም፣ እላችኋለሁ፤ ማን እንደ ሆናችሁና ከየት እንደ መጣችሁ
አላውቅም፤ እናንተ ዐመፀኞች ሁሉ ከእኔ ራቁ ይላል:: ...»

ወደ መንግሥቱ የምንገባው በሥራ ሳይሆን፣ ከኢየሱስ ጋር ባለን ግንኙነት ነው:: ኢየሱስ «ማን እንደ ሆናችሁና ከየት እንደ መጣችሁ አላውቅም» ሲል፣ «ከእናንተም ጋር ሆነ ከቤተ ሰዎቻችሁ ጋር ግንኙነት የለኝም» ማለቱ ነው::[1] ይህ ለአይሁድ ጆሮ ብርቱ ቃል ነው:: በር የሚከፈተው የቤተ ሰብ አባላት ለሆኑት ብቻ ነው::

እነዚህ ሰዎች ፈጽሞ እንግዶች ናቸው ማለት አይለም:: የቤቱን ጌታ ያውቁታል:: የመብላትና የመጠጣት ልምድ በባህላቸው ውለኛ ምልክት ነበር:: ከዚሁ ልምምድ ጋር አንድ ዐይነት ትስስር አለ:: ከዚህም በላይ የቤቱ ጌታ በጐዳናዎቻቸው ላይ አስተምሮአል:: አንድ ዐይነት ግንኙነትን አግኝተዋል፤ በዚህ ግንኙነትም ወደ ቤቱ እንገባለን ብለው ኣስበው ነበር:: በሩ ክፍት የሆነው ለቤተ ሰቡ ነበር:: በተመሳሳይ ምንባብ ማቴዎስ 7፥21-23 ውስጥ ሰዎቹ የተማመኑት በሥራቸው ነው:: አገልጋዮች እና ወዳጆች ነን ብለዋል:: እንዲገባ የሚፈቀድለት ግን ቤተ ሰቡ ብቻ ነበር::

«ከቤተ ሰቡ» በቀር ሌላ ሰው አይገባም:: ቃሉ እንደ ስም ሲ ግል «ክሕደት» ተብሎ ተተርጕሟል:: በሌላ አነጋገር የቤቱ ባለቤት ከእነርሱ ጋር ምንም ዐይነት ግንኙነት አይኖረውም:: ለምን? የጋለ ፍላጎት ስላልነበራቸው ነውን? ጀልባው ስላመለጣቸው ነውን?

[1] Packett ከ"*Ouk oida humas, Pothen este*" («ከየት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም») ወደ "*Ouk oida humas. Pothen este?*" (አላውቃችሁም፤ ከየት ናችሁ?» በማለት እንለውጠዋለን:: ይህ አስቸጋሪ የሆነውን ሐረግ ቀና በማድረግ ወደ ቍ 26-27 መልካም የሆነ ሽግግር ያደርሳል ይላል (E.B. Packett, "Luke 13:25" *ExpT* 67 [1955-56]: 178).



አይደለም! «ጽድቅ ያልሆነ ነገር አከናዋኞች» ናቸው:: ወደ መንግሥቱ የማይገቡት ሰዎች ችግራቸው ጊዜን ማደለደሉ ሳይሆን ኀጢአት ነው:: ዘግናኝ ወንጀል ፈጽመዋል ማለት ነው? አዎ! ኢየሱስን አልተቀበሉትም:: ልጁን አልቀበልም ማለት በማንኛውም አባት ዘንድ ወደር የማይገኝለት ወንጀል ነው::

ሉቃ 13፥28-30

28«አብርሃምን፣ ይስሐቅንና ያዕቆብን
ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ
ስታዩ፣ እናንተ ግን ወደ ውጭ ተጥላችሁ ስትቀሩ
በዚያን ጊዜ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል:: 29ሰዎች
ከምሥራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከሰሜንና ከደቡብ መጥተው
በእግዚአብሔር መንግሥት በማእድ ይቀመጣሉ:: 30እነሆ
ከኋለኞች መካከል ፊተኞች የሚሆኑ፣ ከፊተኞች
መካከልም ኋለኞች የሚሆኑ አሉ::»

የቤተ ሰብ ግንኙነት ዋና ሐሳብ ቍ 28 ላይም ይቀጥላል:: ቀደም ካሉት ሰማዕት አንዳቸውም ፍጹማን አልነበሩም:: እንዲያውም አንዳንዶቹ በጣም ጥሩዎች የሚባሉ እንኳን አልነበሩም:: ሆኖም ለድነታቸው የተማመኑት ሥራቸውን ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ነበር:: እዚህ ላይ የቀረበው ሥዕል አይሁድ ተስፋ ያደረጉት መሲሓዊ ግብዣ ነበር:: ለእነርሱ በመሲሐዊው ግብዣ ላይ ለመገኘት ካለመቻላቸው ይብስ የከፋው ነገር መቀመጫቸው በርኩስ አሕዛብ ሰው ተይዞ እነርሱ በመስኮት አጮልቀው ማየታቸው ነበር:: ለፖሊስትና አይሁዳውያን ይህ እጅግ ዘግናኝ ሥዕላዊ ትእይንት ነው («ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት»፤ ማቴ 8፥12፤ 22፥13፤ 24፥51፤ 25፥30 ይመ)::

የሚድኑት ብዙ ናቸው ወይስ ጥቂት? ለሚለው የሰውየው ጥያቄ እዚህ ላይ ሁለተኛውን መልስ እናገኛለን:: ብዙዎች ይድናናሉ! ከምድር ዳርቻ ሁሉ ይመጣሉ:: ይህ ብዙ ጊዜ ተተንብይዋል (ኢሳ 2፥2፤ 19፥16-24፤ 25፥6-12፤ 60፥8-14፤ 66፥18-24፤ ሆሴ 1፥10-11፤

ዘካ 14÷16-21):: አይሁድ መሲሐቸውን ሳይቀበሉት ቀሩ:: አሕዛብ ግን ወደ እርሱ ጐረፉ::

የመጨረሻዎቹ (አሕዛብ) የመጀመሪያ ይሆናሉ (ከአይሁዳውያን በላይ)[2]:: ይህ ኢየሱስ ከሚደጋግማቸው አባባሎች አንዱ ነበር:: ዐውዱ ውስጥ የሚታየው የእግዚአብሔር ሐሳብ ከሰው የተለየ መሆኑ ነው:: ሰዎች ከእግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ ነገሮችን በቅደም ተከተል ያስቀምጣሉ:: እኛ ለሚታዩና ለሚዳሰሱ ሥራዎች ክብር እንሰጣለን:: እግዚአብሔር ግን ንጹሕ ልብንና እውነተኛ የቤተ ሰብ ግንኙነትን ያከብራል:: በፍርድ ቀን እግዚአብሔር ሥራችንንና የሐሰት ጽድቅ መሣሪያችንን ከንቱ በሚያደርግበት ጊዜ የምንሆነውን እናጣለን:: ከኢየሱስ ጋር ብቻ እንቆማለን፤ ወይም ከበር ውጭ ብቻችንን እንቀራለን::

**§ 113ለ**
**ፈሪሳውያን ስለ ሄሮድስ ኢየሱስን አስጠነቀቁት**
**(ሉቃ 13÷31-35)**

31በዚያን ሰዓት ከፈሪሳውያን አንዳንዶች ቀርበው «ሄሮድስ ሊገድልህ ይወዳልና ከዚህ ውጣና ሂድ» አሉት::

32እንዲህም አላቸው፤ «ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ፦ እነሆ፣ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ፤ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ በሦስተኛውም ቀን እፈጸማለሁ በሉአት:: ዳሩ ግን ነቢዩ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም ልሄድ ያስፈልገኛል::»

(ነባሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ 1953)

2 አሕዛብ በደረጃ የመጨረሻ ነበሩ:: ርኩሳን ናቸው ተብለው የሚታዩት ከዚህ የተነ''' ነበር:: በተጨማሪም ወንጌልን ለመቀበል የመጨረሻዎቹ ነበሩ:: በ... ያት ሥራ መጽሐፍ በሙሉ አይሁድ ለመስማት ምንጊዜም የመጀመሪያዎቹ ናቸው:: ኢየሱስን ባለመቀበላቸውም በሚሰሓዊው ግብዣ ላይ መቀመጫዎቻቸው በአሕዛብ ተያዙ (ሐሥ 13÷46፤ 18÷6፤ 19÷8-9፤ 28÷28)::



ሄሮድስ አንቲጳስ የሚያሳዝን ሰው ነበር (በቍ. 71 ሁ-ለ ውስጥ የሚገኙትን ማስታወሻዎች ይመ):: መጥምቁ ዮሐንስን ያስገደለው እርሱ ነው:: ኢየሱስንም በክፉ ዐይኑ የሚያየው ይመስላል:: እንዲያውም መጥምቁ ዮሐንስና ኢየሱስ የአንድ እንቅስቃሴ አካላት ናቸው (ሉቃ 9÷9):: ኢየሱስ እንደውም «ዳግም ሥጋ ለብሶ» የመጣው ዮሐንስ ነው ተብሎ እስከ መታመን ተደርሷል (ማቴ 14÷1-2):: የባሰው ደግሞ ኢየሱስ ከመጥምቁ ዮሐንስ ይልቅ ዝነኛ መሆኑ ነው:: እንዲያውም ከሄሮድስ ሹማምንት አንዳንዶቹ ኢየሱስን የሚከተሉ ሆኑ (ሉቃ 8÷3፤ ከሐሥ 13÷1 ጋር ያነጻጽሩ):: ሄሮድስ ኢየሱስን ለመያዝ መከታተሉ የሚያስደንቅ አይደለም (ሉቃ 9÷9፤ 23÷7-12)[3]:: ከያዘው ደግሞ በኢየሱስ ላይ ግድያ እንደሚመጣበት የታወቀ ነው:: ኢየሱስ ግን ሞት አልፈራም:: የመጣውም ለዚህ ነው:: ከመጣ መቆየት ያለበት በመቃርያስ ሳይሆን ኢየሩሳሌም ውስጥ ነው::

ሄሮድስ በአይሁድ ዘንድ ተወዳጅ አልነበረም:: በተለይ ፈሪሳውያን ይጠሉት ነበር:: እንዲያውም የእርሱን ረዳቶች በተለይ ሄሮድሳውያንን ይጠሏቸዋል:: ከሄሮድስና ከወዳጆቹ ከሄሮድሳውያን የበለጠ ፈሪሳውያን ኢየሱስን ይጠሉት ነበር (ሉቃ 5÷17:21:30፤ 6÷2:7፤ 7÷30፤ 11÷38-54፤ 14÷1-6):: ከባዕዳን ወዳጆች ጋር የተባበሩትም ለዚህ ነው (ማቴ 22÷14-16፤ ማር 3÷6):: ይህን ጠላታቸውን ለማስወገድ ሁለቱ ወገኖች በአንድ ላይ ሠሩ:: ይህ ሆኖ ሳለ ለምንድነው ፈሪሳውያን ሄሮድስ ሊይዝህ ይፈልጋል በማለት ኢየሱስን ያስጠነቀቁት? ምናልባት እነዚህ ከሄሮድስ ጋር የተባበሩት መጥፎ ፈሪሳውያን ሳይሆኑ፣ ደጋጎቹ ሳይሆኑ አይቀሩም:: መልካም የሆኑ ፈሪሳውያንም አሉ (ለምሳሌ፣ ኒቆዲሞስ፣ የአርማትያው ዮሴፍ፣

3 J.B. Tyson, "Jesus and Herod Antipas," *JBL* 79 (1960): 239-246 በሚለው ጽሑፉ ሄሮድስ ኢየሱስን ለመያዝ ያደረገውን ክትትል ተጀምሮ እስከሚጨረስ ያሳያል::

ገማሊያል):: ይሁን እንጂ በአገልግሎቱ መጨረሻ፣ ጊዜ ስለ ሄሮድስ ኢየሱስን የሚያስጠነቅቁት ሰዎች ብዙ ወይም ደፋሮች አልነበሩም::

ይህ የዕቅዳቸው አካል ሳይሆን አይቀርም:: ሉቃስ ስለ አታላይነታቸው ባይጠቅሳቸውም፣ ኢየሱስ ያን ስፍራ ለቆ ይሄድ ዘንድ ሰዎቹ ድብቅ ዐላማ ያላቸው ይመስላል:: በመጀመሪያ ዮርዳኖስ ማዶ ሽንፈት ገጥሞአቸዋል:: ሰዎች በብዛት ኢየሱስን በመከተል ላይ ናቸው፤ እዚያ በቆየ መጠን ደግሞ ተከታዮቹ ይበዙ ጀመር:: ሁለተኛ ኢየሩሳሌም ውስጥ እንዲሆን ይፈልጋሉ:: ኢየሱስ ከይሁዳ ይልቅ በገሊላና በዮርዳስ ማዶ ከፍተኛ ተቀባይነት አለው:: ፈሪሳውያን ደግሞ በይሁዳ በተለይ ደግሞ በኢየሩሳሌም ከፍተኛ ተቀባይነት አላቸው:: በመጨረሻ ነገር ያገኙት ያህል ሆነ:: በአንድ የመጨረሻ ጥረት የሚፈልጉትን ሰው ያገኙት ይሆናል::

ምን ለማለት እንደ ፈለጉ ኢየሱስ ያውቃል:: ልባቸውን ያያል:: እንዲያ የሚመልስላቸው በትክክል ከዚህ የተነሣ ነው:: ሄሮድስን ቀበሮ ብሎታል:: በብሉይ ኪዳን ቀበሮ የሚያመለክተው አነስተኛና እዚህ ግባ የማይባል ነገር የሚያቅድን ሰው ነው (ነህ 4፥3፤ መሓ 2፥15):: ከዚህም በላይ ኢየሱስ «ቀበሮ» ያለው በአንስታይ ፆታ ነው:: ይህን ያለው ከሄሮድስ በስተጀርባ ሆና የምታንቀሳቅሰውንና የምታናውጠውን የሄሮድስን ሚስት ለማጋለጥ ነው በማለት ብዙዎች ያምናሉ:: ኢየሱስ በዚህች ሴት ምክንያት ፍርሃት ያደረበት አለመሆኑ የታወቀ ነው:: ጉዳዩን ይብስ ያከፋው ደግሞ ሄሮድስ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን በአንበሳ መመሰል የነበረበት መሆኑ ነው:: ታዲያ ሄሮድስን ከአንበሳ ይልቅ ቀበሮ ብሎ መጥራት የአገዛዙን ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ነው::[4]

[4] E.A. Hermanson, "Kings Are Lions, but Herod Is a Fox: Translationg the Metaphor in Luke 13:22," *BT* 50/2 (1999): 235-240.



ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነት በሚያስደንቅ ግልጽነት ይገነዘባል:: እርምጃዎቹ ሁሉ በእግዚአብሔር የተወሰኑ ናቸው:: ሄሮድስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማሰናከል ዐቅም የለውም! ኢየሱስም እዚህ ግባ በማይባል ማስፈራሪያ ከተነሣበት ዐላማ አይዛነፍም::[5] ይህን ትምህርት ማስተዋል ይኖርብናል:: እግዚአብሔር ሁሉን ይቆጣጠራል:: እኛ ሕዝቦቹ እንደ መሆናችን መጠን እቅፉ ውስጥ ማረፍ አለብን:: ታዛገሮች ከሆን ራሳችንን በጥበቃው ሥር እናገኛለን:: ይህ ማለት ግን ፍጹም ጉዳት አይደርስብንም ማለት እንዳልሆነ ከኢየሱስ አይተነዋል:: እግዚአብሔር ለታዛዥ ልጆቹ ያለው ዕቅድ ግን ከቶ አይዛነፍም::

ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ውስጥ እንደሚሞት ሲናገር ፈሪሳውያን እርቃናቸውን የቀሩ ያህል ሳይሰማቸው አይቀርም:: የመሞቱን ዕጣ ፈንታ አሜን ብሎ በመቀበል አሳፋሪ ፍላጎታቸውን አጋልጧል:: አዝኗል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል:: ሐዘኑ የፈሰሰው ለኢየሩሳሌም ነው:: የጽዮን ውበት፣ የኢየሩሳሌም ተስፋና ምኞት እፊታቸው በቆመው ሰው ውስጥ ነው:: ይሁን እንጂ የገዳዮች ቤት ወደ ሆነችው ኢየሩሳሌም በጉጉት አጣደፉት::

34«ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ነቢያትን
የምትገድዪ፣ ወደ አንቺ የተላኩትንም በድንጋይ
የምትወግሪ! ዶሮ ጫጩቶቿን በክንፎቿ ሥር
እንደምትሰበስብ፣ ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ
ፈለግሁ፤ እናንተ ግን እምቢ አላችሁ፤
35እነሆ፣ ቤታችሁ
ወና ሆኖ ቀርቶአል:: እላችኋለሁ፤ በጌታ ስም የሚመጣ
የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ አታዩኝም::»

**ሉቃ 13፥34-35**

[5] የሉቃስ ወንጌልን የሚያነቡትን «ሦስት ቀን» የሚለው ስለ ትንሣኤ በርግጥ አሳሰባቸው:: ይሁን እንጂ አጭር ጊዜን ከማመልከት በቀር ምንም ማለት ላይሆን ይችላል::

በእጅጉ ስሜትን የሚነካውና አሳዛኝ የሆነው ንግግር[6] ከዚህ ላይ ይገኛል:: ከኢየሱስ ሞት ትንሽ ቀናት ቀደም ብሎ ማቴዎስ (23፥37-39) እነዚህኑ ቃሎች ይደግማል:: ነቢያትን ስለ መግደላቸው ማቴዎስ ሙሉ ታሪክ ያቀርባል (23፥29-36):: ለሥርዐትና ለታሪክ ታማኝ የሆነችው ኢየሩሳሌም የራሷን ክርስቶስ አልቀበልም ብላ በመስቀል ላይ ሰቀለችው፤ እጇን በመታጠብም፣ «ከዚህ በኋላ ሰላም ይኖረናል!» አለች:: በራሳቸው ላይ ስለሚያመጡት መከራና በቅርብ ቀንም እውን ስለሚሆነው ጥፋት የሚያውቁት ነገር አልነበረም (ቍ 35)::

ኢየሩሳሌም[7] «ወና» (ቃል በቃል ባድማ፣ ወና ማለት ነው) ሆና ትቀራለች:: ይህ ደግሞ ሁለት አንድምታዎች አሉት:: በመጀመሪያ ኢየሱስ ሚሰሓቸው ነው:: እርሱን ቢገድሉት ተስፋ የሚያደርጉት[8] ሰው አይኖራቸውም:: ሁለተኛ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ በፈጸሙት ዘግናኝ ወንጀል የተነሣ (ከማቴ 24፥1 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሉቃ 19፥41-42፤ 21፥20-24) በአንድ ትውልድ ዘመን ውስጥ ከተማዋ ዕዳ ትከፍላለች:: ኢየሩሳሌምን የውስጡ ብጥብጥ ከጎዳት በኋላ የሮም ወታደሮች በ70 ዓ.ም. በመክበብ፣ ብትንትን አድርገው አወደሚት:: ከውስጥ

[6] ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌም ስለ ማልቀሱ ሉቃስ ከጻፋቸው አራት ሁኔታዎች ውስጥ ይህ የመጀመሪያ ነው::

[7] «ኢየሩሳሌም» የሚለው ቃል በአንድ መደዳ ሁለት ጊዜ ተደግሞአል፤ ይህም ለጉዳዩ ብርቱ ትኩረት ይሰጠው ዘንድ የተደረገ ድግግሞሽ ነው::

[8] L. Baltzer, "The Meaning of the Temple," *HTR* 58 (1965): 263-277 «ቤት» የሚለው ቃል «ቤተ መቅደስ» ተብሎ ግንዛቤ እንዲገኝበት ሐሳብ ያቀርባል:: ያም ሆነ ይህ በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም ውስጥ *አይኮስ oikos* ለቤተ መቅደስ የተለመደ ቃል ነው:: ሉቃስ ብዙ ጊዜ *ሄሮን hieron* የሚለውን ቃል የሚጠቀም ሲሆን፣ የእርሱ ጽሑፍ ከማቴዎስ ወይም ከማርቆስ ጋር ጉድኝት ሲያደርግ ለቤተ መቅደስ ግን *አይኮስን oikos* ይጠቀማል:: ከዚህም በላይ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን የሽኩናህ ክብር ይዞአል ይላል (ሉቃ 9፥28-36፤ ሐሥ 7፥55-9፥3-5):: ስለዚህ ኢየሱስ ቤተ መቅደስን ትቶ ሲሄድ ወይም (የእግዚአብሔር ሕዝብ አንቀበልህም ሲሉት) የእግዚአብሔር ክብር [ካቦድ - kabod] ተለይቶ ሄዷል:: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ቤትን [ይኸውም ቤተ መቅደስን] ትቶ ሲሄድ፣ አምላካቸውም ትቷቸው ሄዷል::



መከፋፈልና የእርስ በርስ ጦርነት፣ ከውጭ ደግሞ የሮም ወታደሮች ሆነው፣ የኢየሩሳሌም ከዚህ ቀደም ከቶ ያላየችው ወይም ከዚያ ወዲህ ያላጋጠማት ዘግናኝ ሁኔታና ጥፋት ደረሰባት::

«በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው» (መዝ 118፥26) ብለው እስከሚጮኹ ድረስ ዳግመኛ እንደማያዩዋት ኢየሱስ ተናግሮአል:: በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከኢየሩሳሌም ውጭ ያሉ ሕዝቦች ኢየሱስ በድል አድራጊነት ወደ ከተማይቱ ሲገባ በደስታ በመቀበል እነዚህን ቃሎች ከፍ ባለ ድምፅ ያሰማሉ:: ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ እንኳ ኢየሱስ ይህን ትንቢት በድጋሚ ተናገረው (ማቴ 23፥37-39):: በሆሣዕና ዕለት ይህ ነገር አልተፈጸመም ማለት ነው:: 70 ዓመተ ምሕረት ኢየሱስ ወደ ከተማይቱ ለፍርድ ሲመጣ የሚሆነውን ነገር የሚያሳይ ነው በማለት በዘይቤአዊ አገላለጽ እንመልከተው? ይህ ደግሞ እነርሱ ካሰሙት የሐሤት ዜማ ጋር አይገጣጠምም:: ስለዚህ ይህ ገላጣ ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለትን፣ ምላስም ሁሉ ጌታ ነው ብሎ የሚገልጽለትን (ፊል 2፥9-11፤ ማቴ 24፥30-31፤ ራእ 1፥7) ጌታ ዳግም ምጽአትን ይመለከታል ብለን እንደመድማለን:: ምናልባትም ይህ ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ[9] በደስታ የሚቀበሉትን ብዙ አይሁድ ድነት ሳያመለክት አይቀርም (ሮሜ 11፥25-27)::

[9] D.C. Allison, "MT 23:39 = Lk 13:35b as a Conditional Prophecy" *JSNT* 18 (1983): 75-84 በሚለው ጽሑፉ በመዝ 118፥26 ዐውድ ውስጥ እነዚህ ቃሎች የፈንጠዝያ ውዳሴ ናቸው፤ በማቴ 23፥39 እና በሉቃ 13፥35 ዐውድ ውስጥ ግን ፍርድን ያሳያሉ ይላል:: ይህን እንዴት እናስታርቃለን? ጽሑፉ፣ «መሲሕ ሲመጣ ሕዝቡ ይባርኩታል (ያወድሱታል)» ማለት አይደለም፤ ነገር ግን «እስራኤል ሲባርኩት (ሲያወድሱት) መሲሕ ይመጣል ብሎ» ሐሳቡን ይሰነዝራል:: አንዳንድ ድጋፍ ሰጭ ማስረጃዎችን መሠረት በማድረግም ይህ ምንባብ ቅድመ ሁኔታን ያዘለ ትንቢት ነው በማለት ሐሳቡን ያቀርባል:- (ሀ) አይሁድ መሲሕ የሚመጣ መሆኑን ማመናቸው ከንጽሕናቸውና ንስሓ ከመግባታቸው ጋር የተያያዘ ነው:: (ለ) *ሄዎስ Heos* የሚለው ቃል ከግሪክ ቋንቋ ዐረፍተ ነገር ጋር የተያያዘ ነው:: (ሐ) «ይህ ከሆነ ዘንድ» ለሚለው የአይሁድ ሥነ ጽሑፍ ይህ መዋቅር አገልቆታዊ

**§ 114**
**እራት ከፈሪሳውያን ጋር፣ በአካል እብጠት ይሠቃይ የነበረውን ሰው መፈወስ**
**ሉቃ 14÷1-24[10]**

ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር ሦስት ጊዜ ከበላባቸው ማእዶች (7÷36፤ 11÷37፤ 14÷1) ይህ የመጨረሻው ነው። የመጀመሪያው ኀጢአተኛዋ ሴት እግሩን በዘይት እንድትቀባ በፈቀደ ጊዜ በጠብ ተጠናቀቀ። ሁለተኛውም በጠብ ተጠናቀቀ፤ ምክንያቱ ኢየሱስ ከመብላቱ በፊት እጁን አለመታጠቡ ነው። ስለዚህ ከፍተኛ የመቀመጫ ስፍራን ለራስ መሻትን በመንቀፍ ኢየሱስ ጋባዡንና እንግዶቹን በመውቀሱ የተነሣ[11]፣ ይህኛውም ማእድ በመቋረጡ በጣም አልተደነቅንም።

**ሉቃ 14÷1-6**

1 አንድ ሰንበት ቀን፣ ኢየሱስ ምግብ ሲበላ ከፈሪሳያን አለቆች አንዱ ወደ ነበረ ሰው ቤት በገባ ጊዜ
ሰዎች በዐይን ይከታተሉት ነበር። 2 በዚያም በአካል
እብጠት የሚሠቃይ አንድ ሰው ከፊት ለፊቱ ነበር።
3 ኢየሱስም ሕግ ዐዋቂዎችንና ፈሪሳውያንን፣ «በሰንበት ቀን ሕመምተኞችን መፈወስ
ተገቢ ነው ወይስ አይደለም?» ሲል ጠየቃቸው። 4 እነርሱ ግን ዝም አሉ። እርሱም
ሰውየውን ይዞ ፈወሰውና አሰናበተው።
5 ደግሞም፣ ከእናንተ አንዱ ልጁ[ሸ] ወይም በሬው በሰንበት ቀን ጉድጓድ
ቢገባበት ፈጥኖ የማያወጣው ማን ነው?» አላቸው። 6 እነርሱም ለዚህ አንዳች መልስ
ሊያገኙ አልቻሉም።

[ሸ5] *አንዳንድ ቅጆች አህያው ይላሉ።*

ሉቃስ ሁለት ዝርዝር ጉዳዮችን በማመልከት ሊመጣ ስላለው ጠብ አንባቢዎችን ያዘጋጃል። በመጀመሪያ ግብዣው የተካሄደው ዕውቅ በሆነው፣ ቃል በቃልም፣ «ከፈሪሳውያን አለቆች» በአንዱ ቤት ነው። ይህ ሰው ምናልባት የፍርድ ሸንጎ አባል ሳይሆን አይቀርም፤ ወይም በዚያ ሰንበት ዕለት ያመለኩበት ምኲራብ አለቃ ሳይሆን አይቀርም። ሁለተኛ ይህ የሆነው በሰንበት ዕለት ነው፤ ቀደም ሲልም ችግር አስከትሎአል (ከቍ 50-52 ጋር ያነጻጽሩ፤ ከ100 ጋር ያወዳድሩ፤ 110)።

ከዚህ ዕውቅ ፈሪሳዊ ሐሳብ ዓላማ በስተጀርባ ያለውን ነገር አናውቅም (ለኢየሱስ በጎ ያስብ ወይም ክፉ ያስብ)። የግብዣው ውጤት ግን ኢየሱስ በፈሪሳውያን ሁሉ በጥንቃቄ መታየቱ ነው። «ይጠብቁት» የሚለው ቃል ሉቃስ ወንጌል ውስጥ ሁለት ጊዜ (6÷7፤ 20÷20) አገልግሎት ላይ ውሏል። በሁለቱም ጊዜ ፈሪሳውያን ስሕተት ነው ብለው የሚቈጥሩትን ነገር ኢየሱስ ሲያደርግ ለማየት ጥረት ማድረጋቸውን ያመለክታል።

ከሕዝቡ መካከል የአካል እብጠት ያለበት ሰው አለ። ዛሬ ይህ ሕመም ውሃ የመቋጠር በሽታ ይባላል። በቀላሉ ሲገለጥ ሰውየው የተከማቸ ውሃ አለበት ማለት ነው። ለክፉ የማይሰጥ ይመስላል። ይሁን እንጂ ይህ ዐይነቱ በሽታ የልብን ወይም የጉበትን መታመም

ይመስላል። (መ) ይህ በመዝ 118 ላይ ተስፋ የተደረገውን ድነትና ማቴ 23 እና በሉቃ 13 ውስጥ ያለውን የፍርድ ዐውድ አሜን ብሎ ይቀበላል። (ሠ) ሐዋርያት ሥራ 3÷19-21 እና 2ጴጥሮስ 3÷11-12 ሁለቱም የክርስቶስን ዳግም ምጽአት አርቱዕ በሆነ መንገድ ያመለክታሉ።

10 ሉቃስ ወንጌል ም. 13 እና 14 ምናልባት ከፈሪሳውያን ጋር እንደ ተደረጉ መንትያ የውዝግብ ማማዎች መነበብ ሳይኖርባቸው አይቀርም። በምዕራፎቹ ውስጥ የሚታዩ ጉልህ ንፅፅሮች አሉ፡- (ሀ) 13÷10-17 እና 14÷1-6 በሰንበት ስለ ተከናወነ ፈውስ የሚገልጹ ናቸው (ለ) 13÷22-30 እና 14÷15-24 ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገቡ እነማን እንደሆኑ የሚናገሩ ናቸው (ሐ) 13÷31-35 እና 14÷25-35 ስለ ኢየሱስ መከራ፣ ስለ ኢየሩሳሌምና አንድ ደቀ መዝሙርን በሚመለከት የቀረቡ ናቸው።

11 ጄ. ቲ. ካሮል የተባሉ ጸሐፊ በ"Luke's Portrayal of the Pharisees," *CBQ* 50 (1988):604-621 ላይ ኢየሱስ ከፈሪሳውያን ጋር የነበረው ውዝግብ እንዴት እንደ ጀመረ ጠቁመዋል። ኢየሱስንና ተከታዮቹን የሚደግፉ አንዳንድ ፈሪሳውያን ምንጊዜም የነበሩ ሲሆን (ለምሳሌ ዮሐ 3÷1-2፤ የሐዋ ሥራ 5÷33-40፤ 23÷6-10) በሉቃስ ዘገባ መሠረት የነበሩት ሁኔታዎች ከለብታ ወደ ግለት የተሸጋገሩት በተለይ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጨረሻ ጉዞ ባደረገበት ወቅት ነበር (ሉቃ 5÷21:26፤ 6÷1-11፤ 7÷29-30:36-50፤ 11÷37-54፤ 12÷1፤ 14÷1-6:7-11:12-14:15-24፤ 15÷1-2፤ 16÷14-31፤ 17÷20-21፤ 18÷9-14)።

ያመለክታል። መነሻ ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን ይህ የአካል እብጠት ሊድን ይችላል፤ አንዳንድ ጊዜ ግን ለሞት ያደርሳል። በዚህም ሆነ በዚያ ሰውየው አሳዛኝ ሕመምተኛ ነው።

ለምን በበዓሉ ላይ ተገኘ? የነገር መነሻ ይሆን ዘንድ (ከሉቃ 5÷17፤ 6÷7 ጋር ያነጻጽሩ) በሕዝብ መካከል እንዲገኝ ተደርጎ ሊሆን ይችላል። የሚመስለው ግን ፈውስን ለማግኘት ኢየሱስን ከሚከተሉት ሕመምተኞች መካከል አንዱ ሳይሆን አይቀርም። ተመልካቾቹ ለታላቁ በዓል በአደባባዩ ተሰብስበው ሳለ ይህም ሰው ከእነርሱ ጋር ተቀላቅሏል።

ኢየሱስ የሚጠይቀው ጥያቄ በጣም ግልጽ፣ (ቍ 3)፤ መልሱም በጣም የታወቀ ነው! ፈሪሳውያን ግን ዝም አሉ። ኢየሱስ ትውፊትን በፈውስ ይሽረው ዘንድ ይፈልጋሉ (ከቍ 51 እና 110 ጋር ያነጻጽሩ)። አሁን ግን ወጥመድ ውስጥ ገብተዋል። በሰንበት ቀን በሽተኛን መፈወሱ ሕጋዊ ነው ለማለት አይችሉም። በኢየሱስ ላይ የሚለጥፉት አንዳች ወንጀል የላቸውም፤ ከትውፊታቸው (ከወጋቸው) ጋርም ይጣረሳሉ። ሕጋዊ አይደለም ማለትም አይችሉም። ይህን ቢሉ ከምክንያታዊነት፣ ከርኅራኄ፣ በጎና ጽድቅ ከሆነው ሁሉ ጋር መቃረን (መጣላት) ይሆንባቸዋል። ድርጊቱ ግብዝነታቸውን ያጋልጣል፤ ተከታዮቻቸውም ኢየሱስን ለመከተል ከእነርሱ ዘወር ይላሉ።

የኢየሱስ መልስ ሰውየውን በእነርሱ ፊት መፈወስ ነው። ነገር ሊዘበራረቅ ነው። ኢየሱስ ይህ ሰው በውዝግብ መሐል እንዲያዝ አልፈለገም (ከዮሐ 5÷1-18፤ ከ9÷1-34 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ወደ ቤቱ እንዲሄድ አደረገና ከፈሪሳውያን ጋር ያለውን ጉዳይ ለመጨረስ ትኩረቱን መለሰ። እነርሱም በሰንበት ዕለት እንደሚፈውሱ አስታወሳቸው። እነርሱ ልጅን ወይም በሬን የሚያድኑ ከሆነ፣



ኢየሱስም ይህን የአካል እብጠት ያለበት ሰው ለማዳን ይችላል።[12] ግልጽ የሆነው ልዩነት ፈሪሳውያን በሰንበት የሚፈጽሙት ሕይወትን ለማዳን ብቻ መሆኑ ነው።[13] ኢየሱስ እሑድ ድረስ ሊቆይ የሚችለውን ፈውስ በሰንበት ዕለት በመፈጸሙ ከሚፈለገው በላይ ተጉዟል። ዋናው ጉዳይ የሚገኘው እዚህ ላይ ነው። ኢየሱስ ሰንበታቸውን የሚሽረው እግዚአብሔር ለምሕረትና ለርኅራኄ ያለውን ሀሳብ በመምረጥ ነው።

የኢየሱስ ምክንያታዊነት አሸነፋቸው «ዝም አሉ» የሚለው ሐረግ ቀጥታ ሲተረጎም፣ «እነዚህን ነገሮች በመቃወም የሚሉት ነገር አልነበራቸውም» ማለት ነው። የታሰረው አንደበታቸው ብቻ ሳይሆን ሁለንተናቸው ነበር። እንደ ተሸነፉ ዐውቀዋል። እጅግ መጥፎ በሆነው ስልት በመምጣት ኢየሱስን ግራ ሊያጋቡት ፈለጉ፤ ግን ምንም ሊያደርጉበት አልቻሉም።

> 7 ኢየሱስ ተጋባዦቹ የክብር ስፍራ ሲመርጡ ተመልክቶ፣ እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ ለእነርሱ ነገራቸው፤ 8 «አንድ ሰው ሰርግ ቢጠራህ፣ በክብር ስፍራ አትቀመጥ፤
>
> ሉቃ 14÷7-11
>
> በክብር ከአንተ የሚበልጥ ሰው ተጠርቶ ከሆነ፣ 9 ሁለታችሁንም የጋበዘው መጥቶ፣ ስፍራውን 'ለዚህ ሰው ልቀቅለት' ይልሃል፤ አንተም አፍረህ ወደ ዝቅተኛው ስፍራ ትሄዳለህ። 10 ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ ዝቅተኛውን ስፍራ ይዘህ ተቀመጥ፤ ጋባዥህም ሲመጣ፣ ወዳጄ ሆይ፤ ወደ ላይ ከፍ በል ይልሃል፤ አንተም በዚያን ጊዜ አብረውህ በማእድ በተቀመጡ ሰዎች ሁሉ ትከበራለህ። 11 ምክንያቱም ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ራሱንም ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ሁሉ ከፍ ይላል።»

---

[12] አንዳንድ ቅጅች «ልጁ» በማለት ፈንታ» «አህያው» ይላሉ።

[13] በሙት ባሕር ጽሑፎች ውስጥ "Cairo Damascus Covenant" 11:13-15 በሚለው ላይ፣ በሰንበት ዕለት አንዲት እንስሳ ስትወልድ መርዳት ወይም ጉድጓድ ውስጥ ስትገባ ማውጣት በቁምራን የእምነት ወገኖች የተከለከለ እንደ ነበር ተገልጾአል። በብሉይ ኪዳንና በዕብራዊው ሕግ ግን የተፈቀደ ነበር (*Shabbath* 128b).

የአይሁድ ግብዣ የፈረስ እግር ቅርጽ ባለው የምግብ ገበታ የሚካሄድ ሲሆን፣ ከመሬት ከፍ የሚለው ስንዝር ያህል ነው። በምግብ ገበታው ዙሪያ ሦስት ሰዎች የሚደገፉበት ትራስ ይገኛል። ጋባዡ በምግብ ጠረጴዛው ራስጌ ይቀመጣል። የክብር ስፍራ በቀኝ ጐኑ የሚገኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው የክብር ስፍራ ደግሞ በግራ ጐኑ ይገኛል። ይህ የመቀመጫ ድልድል እስከ «መጨረሻው» መቀመጫ ድረስ በዚሁ ቅደም ተከተል ይጓዛል።

በዚህ በዓል ላይ ግልጽ የሆነ ተዋረድ አለ። አንድ ወይም ሁለት ደረጃ ከፍ ብለህ ትቀመጥ ይሆናል። በጣም ደፋር ከሆንክ ግን ጋባዡ ክብር ላለው ተጋባዥ ቦታ እንድትለቅ መጠየቅ ይኖርበታል። ይህ ደግሞ ያሳፍራል።

እነዚህ ሰዎች ከመኪና ፊት ወንበር ላይ መቀመጥ አለብኝ ብለው እንደሚከራከሩ ሕፃናት ናቸው። ድርጊታቸው አሥቂኝ ራስ ወዳድነትና ትዕቢት ነው። በዕድሜ የገፉ ሰዎች በትራስ ላይ ለመቀመጥ[14] እርስ በርስ በሚያደርጉት በዚህ ተራ ፉክክር፣ የኢየሱስ ሐሳብ ተጠምዶአል። «ባጋጠማችሁ ከፍተኛ ስፍራ ላይ አትቀመጡ፤ ዝቅተኛው ስፍራ ላይ ተቀመጡ» አለ። ይህ ደግሞ በመንፈሳዊ ረገድ ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ረገድም መልካም ምክር ነው (ከምሳ 25÷6-7 ጋር ያነጻጽሩ)። ለውርደት በመጋለጥ ፈንታ ለክብር ስፍራ ትመረጣለህ። ራስን የማዋረድ ውጤቱ በአደባባይ ክብርን መቀበል ነው።

ኢየሱስ የሚናገረው ስለ ግብዣ ሥርዐት አይደለም። ይህ ደንብ የሚመለከተው ከመኪና ማቆሚያ ስፍራ ጀምሮ እስከ ከምፓኒ

[14] ሉቃስ ይህ ትዕይንት ለተወሰነ ጊዜ የቀጠለ መሆኑን በማሳየት ኢፍፁም የሆነውን ግስ ይጠቀማል። ኢየሱስ «እየተመለከተ ነበር» (ኤፔኮ - *epecho*) ትርጉሙ «እየተገነዘበ ነበር» ማለት ነው።



ግብገር ድረስ ያለውን ማንኛውንም የሕይወት ገጽታ ነው። በትዕቢት የምንሠራ ከሆን፣ እግዚአብሔር ያለጥርጥር በምትካችን ሌላ ሰው ያመጣል። ለአጭር ጊዜ እንጓዝ ይሆናል፤ በመጨረሻ ግን ይህ ሕፃናዊ እራስ ወዳድነት የከፍተኛ ኀፍረት ምክንያት ይሆናል።

ተቃራኒውም እውነት ነው። ዝቅተኛ ቦታ በመምረጥ ራሳችንን የምናዋርድ ከሆን፣ ውሎ አድሮ ማንነታችን በእኩዮቻችን ዘንድ መታወቁ አይቀርም። ምሥጢሩ ራስህን ከማስታወቅና ከፍ ከፍ ከማድረግ ይልቅ ሌላ ሰው እንዲያውቅልህ ማድረጉ ነው።

የእግዚአብሔር አሠራር ከእኛ ልዩ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከእኛ ተቃራም ነው። ሕይወት ሲያበቃ ደግሞ እግዚአብሔር የማዕረግን (የመታወቂያን) ቅደም ተከተል ይገለብጠዋል። አናት ላይ የነበሩት ግርጌ፣ ግርጌ የነበሩት ደግሞ አናት (ከፍተኛ ቦታ) ላይ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ይህን ለማድረግ ይችላል። ምክንያቱም እርሱ ልብን አይቶ ይፈርዳል፤ እኛ ለመፍረድ የምንችለው የላይ ገጽታንና ሥራን ብቻ በማየት ነው። እግዚአብሔር የውስጥ ማንነትን በማየት የአንድ ሰው ምክንያት ንጹሕ ወይም ዋጋ ቢስ መሆኑን ያውቃል።

[12]ኢየሱስም የጋበዘውን ሰው ደግሞ እንዲህ
አለው፤ «የምሳ ወይም የእራት ግብዣ በምታደርግበት
ጊዜ፣ በአጸፋው እንዳይጋብዙህና ብድራትን
እንዳይመልሱልህ፣ ወዳጆችህን ወይም ወንድሞችህን
ወይም ዘመዶችን ወይም ከበርቴ ጐረቤቶችህን አትጋብዝ። [13]ነገር ግን ግብዣ
ባዘጋጀህ ጊዜ ድኾችን፣ አካለ ስንኩሎችን፣ ሽባዎችንና ዐይነ ስውሮችን ጥራ፤
[14]ትባረካለህም። እነዚህ ብድር ሊመልሱልህ ስለማይችሉ፣ በጻድቃንም ትንሣኤ
ብድራትህ ይመለስልሃል።

**ሉቃ 14÷12-14**

የሚቀጥለው ምክር የሚመለከተው ጋባዥን ነው። ዐይነተኛው ነገር ሲታይ ለተጋባገሮቹ ከተሰጠው ምክር ጋር አንድ ነው። ሊታይ

ልታይ ከምትልና የራስህን ጥቅም ከመሻት ይልቅ፣ ትሑትና ለጋሽ ሁን:: ይህ እንዴት ይቻላል? አዘውትረህ የታወቁ ሰዎችን አትጋብዝ::[15] ወዳጆቻችንን ወይም ዘመዶቻችንን ለእራት መጋበዙ በመሠረቱ ስሕተት የለበትም:: የምትጋብዘው እነርሱን ብቻ ከሆነ ግን ችግር አለብህ ማለት ነው:: ግብዣውን ለማሰናዳት ከፍተኛ ወጭ ተደርጎአል:: ራሳቸውን በበቂ ሁኔታ ለሚመግቡ ሰዎች ያ ሁሉ ተሰናድቷል:: ግብዣው በእጅጉ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች አልተጠሩም::

ሀብትን በአንድ ቋሚ ነገር ላይ የማዋሉን ጥቅም ሁላችንም እናውቃን:: ያለንን ገንዘብ ሁሉ አሁን የምናባክን ከሆን፣ በኋላ ሐሤት የምናደርግበት ገንዘብ አይኖረንም:: ለድኾች መስጠት ገንዘብን ቋሚ ነገር ላለው ጉዳይ ማዋል ነው:: ይህን ስናደርግ በእግዚአብሔር እንድንታወቅ በእኩዮቻችን በኩል ይኖረን የነበረውን ከበሬታ መተዋችን ነው:: እርሱ በትንሣኤ ዕለት አሳምሮ ይሸልመናል::

**ሉቃ 14፥15-20**

15ከኢየሱስ ጋር በማእድ ከተቀመጡት መካከል አንዱ ይህን ሰምቶ «በእግዚአብሔር መንግሥት ቀርቦ ከማእድ የሚበላ ብፁዕ ነው» አለው::

16ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «አንድ ሰው ትልቅ ግብዣ አዘጋጅቶ ብዙ ሰው ጠራ፤ 17የግብዣውም ሰዓት በደረሰ ጊዜ የተጋበዙትን እንግዶች፣ እነሆ፤ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶአልና ኑ ብሎ እንዲጠራ አገልጋዩን ላከባቸው::

18«ነገር ግን ሁሉ የየራሳቸውን ምክንያት ይፈጥሩ ጀመር፤ አንደኛው፣ ገና አሁን መሬት ስለ ገዛሁ ሄጄ ማየት አለብኝ፤ እባክህ፣ ይቅርታ አድርግልኝ አለው::

19«ሌላኛውም 'አምስት ጥማድ በሬዎች ገዝቻለሁ፤ እነርሱን ልፈትናቸው ስለ ሆነ እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ' አለ::

[15] የግሪኩ የአሁን ጊዜ ትእዛዛዊ አንድምታ ይኸው ነው::



20«ሌላው ደግሞ፣ 'ገና ሙሽራ ስለሆንሁ ልመጣ አልችልም' አለ:: ...»

ኢየሱስ በጻድቃን ትንሣኤ ጊዜ አማኝ ስለሚያገኘው ሽልማት የሚያደርገውን ንግግር በዚህ ጊዜ አጠናቆአል (ቊ 14):: ይህም አንድን ሃይማኖተኛ ፈሪሳዊ ስለ መሲሐዊ ግብዣ (ኢሳ 25፥6-12፤ 65፥13-16) ያስብ ዘንድ ማነሣሣቱ አይቀርም:: ይህ ሰው ዒላማ ውስጥ ነው:: የሚያሳዝነው ነገር ግብዣው ላይ የተገኙት ብዙዎቹ በመሲሐዊ ግብዣ ላይ የማይገኙ መሆናቸው ነው (ከ13፥28-30 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህ የሆነው ባለመጋበዛቸው ሳይሆን በተጠሩበት ጊዜ ባለመምጣታቸው ነው:: የኢየሱስ ተግሣጽ የቀረበው በምሳሌ መልክ ሲሆን፣ ይህንኑ ታሪክ ከመሞቱ በፊት ባለው ማክሰኞ ዳግመኛ ይናገረዋል (ማቴ 22፥1-14):: መጠነኛ የአጽንዖት ለውጥና ለየት ያሉ ዝርዝሮች ቢኖሩትም፤ ዋናው ጉዳይ ግን ያው ነው::

እግዚአብሔር ለልጁ ለኢየሱስ ሲል ግብዣ እያደረገ ነው:: መጪውን ግብዣ ይፋ በማድረግ (ቊ 16) በሰፊው ጥሪ ተደርጎአል:: ምግቡ እንደ ተዘጋጀ እንዲህ የሚል ሁለተኛ ጥሪ ተላከ (ቊ 17):- «ወደ በዓሉ በፍጥነት ኑ::» ሀብታምና ዝነኛ የሆነውን ሁሉ ጨምሮ ሰው የተባለ ሁሉ አንድ ሳይቀር ተጋዞአል (ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ይህ አይሁድን ያመለክታል):: ሆኖም ሁሉም ግብዣውን ሳይቀበሉ ቀሩ [አፖ ማያስ - *apo mias*]:: ቃላቸውን አንድ በማድረግ በእምቢታ አገልጋዩን መለሱት::

ሦስት ምክንያቶች ተፈጥረዋል::[16] የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ተመሳሳዮች ናቸው:: አንድን ነገር አስቀድሞ ምንነቱን ሳያረጋግጥ የሚገዛ ሰው ምን ዓይነት ሞኝ ነው? ሐቁ ግን እነዚህ ሁለት ሰዎች የሚገዙትን አረጋግጠዋል:: ላለመምጣት ነው ምክንያት የሚያደርጉት::

[16] ምክንያት መፍጠር ማለት፣ «መራቅ፣ መተው፣ አልቀበልም» ማለት ሊሆን ይችላል::

ነገሩን የሚያባብሰው ግብዣው ፀሐይ ስትጠልቅ የጀመረ የምሽት ግብዣ መሆኑ ነው። የሚገዙትን ነገር በጨለማ አይተው ሊያረጋግጡ አይችሉም። ይህ ምክንያታቸውን ደካማና ጎጂ ያደርገዋል። ሦስተኛው ሰው ግን ተቀባይነት ያለው ምክንያት ሳይኖረው አልቀረም። በቅርብ ጊዜ ያገባ ስለሆነ ከሙሽሪት ጋር ጊዜውን ለማሳለፍ ይፈልጋል። እነዚህ ግብዣዎች የተቀናጁ ባለመሆናቸው በቅርብ የተጋቡ ሰዎች ግብዣው ላይ ሊገኙ አይችሉም። ዘዳግም 24፥5 ሙሽራው ላቀረበው ምክንያት ድጋፍ ይሰጣል። በዚያ ላይ በቅርብ ቀን ያገባ ሰው ቤት ውስጥ ሆኖ ሚስቱን ያስደስት ዘንድ ለአንድ ሙሉ ዓመት ከውትድርና አገልግሎት ነጻ ሊሆን ይችላል ይላል (1ቆሮ 7፥33ንም ይመልከቱ)። የእርሱ ምክንያት ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በእጅጉ ድፍን ብሎ ነው የቀረበው።

ሉቃ 14፥21-24

21«አገልጋዩም ተመልሶ መጥቶ ይህንኑ ለጌታው
ነገረው። በዚህ ጊዜ የቤቱ ጌታ ተቆጥሮ አገልጋዩን፣
'ቶሎ ብለህ ወደ ከተማው አውራ ጎዳናዎችና
መተላለፊያ መንገዶች ውጣ፤ ድኾችንና አካለ
ስንኩሎችን፣ ዐይነ ስውሮችንና ዐንካሶችን ወደዚህ
አስገባቸው' አለው።
22አገልጋዩም፣ 'ጌታዬ ያዘዝኸው ሁሉ ተፈጽሟል፤ ገና አሁንም ቦታ አለ'
አለው።
23«ጌታውም አገልጋዩን፣ 'ወደ ጎዳናዎችና ወደ ገጠር መንገዶች ውጣ፤
ቤቴም እንዲሞላ ያገኘውን ሁሉ በግድ አምጥተህ አስገባ፤' 24እላችኋለሁና ከተጋበዙት
... ያ ሰዎች መካከል አንድ ሰው እንኳ ግብዣዬን አይቀምስም' አለው።»

አይሁድ የራሳቸውን መሲሕ አንቀበልም አሉ፤ ስለዚህ ድነት ወደ አሕዛብ ዞረ (ከሐሥ 28፥28፤ ከሮሜ 11፥1-24 ጋር ያነጻጽሩ)።



በምሳሌው ውስጥ ስለ ግብዣው ጥድፊያ ይታያል። ምክንያቱ ምግቡ በመቀዝቀዝ ላይ መሆኑ ነው። መሲሐዊው ግብዣ ግን እየቀዘቀዘ ወይም እየተበላሸ አይደለም። ቢሆንም ለግብዣው ጥድፊያ ይታያል። እግዚአብሔር የዚህን ዘመን ዕድሜ ወስኖአል። መለኮታዊው ሰዓት ወደ ፍጻሜው በተሽከረከረ ቊጥር ሌሎችን ለመጋበዝ ያለን ዕድል እየሳሳ ይሄዳል። የእያንዳንዱ ሰው ቀን የተወሰነ ነው። አንድ ሰው በፍጥነት ካልመጣ፣ መልስ ለመስጠት ያለው ዕድል ከንቱ ሊሆን ይችላል።

ስለዚህ አገልጋዮቹ በየአቅጣጫው ተላኩ። መንገድ ላይ የሚነገሩ አራት ልዩ ልዩ ቃላትና ሐረጎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ቊ 21 ውስጥ የሚገኙት ቃላት ሁለት ዐይነት የከተማ ጐዳናዎችን ያሳያሉ። ቊ 23 ውስጥ የሚገኙት ሁለቱ ደግሞ የገጠር መንገዶችን ያሳያሉ። መንገዶቹ ሰፋፊ ናቸው። መተላለፊያዎቹ ግን ጠባብ ነበሩ። የገጠሮቹ መተላለፊያዎች (ቊ 23) ደግሞ ወሮበሎች የሚጠለሉባቸው ቊጥቋጦዎች ወይም አጥሮች አሉባቸው። መልእክተኞቹ እንግዶች የሚመላለሱባቸውን መንገዶች ሁሉ ማዳረስ ነበረባቸው።

ድኾችን፣ አካለ ስንኩሎችን፣ ዕውሮችንና አንካሶችን ጨምሮ ሁሉንም መጋበዝ አለባቸው። ከእነዚህ ተጋባዦች አንዳንዶቹ በነበረባቸው የአካል ጉዳት የተነሣ በአይሁድ አምልኮ ሙሉ ተሳታፊ እንዳይሆኑ የተከለከሉ ናቸው። እንዲህ መሆኑ ግብዣውን የላቀ ተወዳጅ ያደርገዋል። ጌታው ለልጁ ክብር ሲል ግብዣውን ሰው በሰው ለማድረግ ከነበረው ዕቅድ የተነሣ አገልጋቹን እንደ ገና ላካቸው። በዚህ ጊዜ ግን አገልጋዮቹ ሰዎችን መጋበዝ ብቻ ሳይሆን፣ «እንዲመጡ» ማድረግም ነበረባቸው። አገልጋይ ማንንም እንዲመጣ ማስገደድ አይችልም። ሆኖም ግብዣው የቱን ያህል አስፈላጊና አጣዳፊ እንደ ሆነ በማስረዳት አጽንዖት ለማድረግ ይችል ነበር። እንዲሁም እኛ እንደ

ወንጌላዊነታችን ወደ ኢየሱስ የመምጣትን አጣዳፊነት መግለጽ ያስፈልገናል:: እንዲህ የሚያደርጉ ታላቅ ክብር ይጠብቃቸዋል::

ይህ ምሳሌ የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነትና የሰዎችን መልስ በአንድ ላይ አጣምሮ ይዞአል:: ወደ ክርስቶስ መምጣታችን ከጉብዝናችን፣ ከማስተዋላችን፣ ወይም ዋጋ ያለን ሰዎች ከመሆናችን የተነሣ እንዳልሆነ እናስተውላለን:: የተጠራነው በእግዚአብሔር ሲሆን፣ የተማረክነው ደግሞ በአገልጋዮቹ ነበር:: በሌላ በኩል ግን አንዳንዶቹ ልባቸው በእጅጉ ደንድኖ ጥሪውን አንቀበልም በማለታቸው እንዳይገቡ ይደረጋሉ:: በአጸፋውም እግዚአብሔር በሉዐላዊ ፍርዱ ልባቸውን ያደነድነዋል (ቊ 24፤ ኢሳ 6፥9-10፤ ማቴ 13፥15፤ ዮሐ 12፥40፤ ሐሥ 28፥26-27፤ ሮሜ 11፥1-24):: ከዚያ በኋላ ወደ ግብዣው የመምጫው ጊዜ በጣም የዘገየ ይሆናል::

**§ 115**
**የደቀ መዝሙራትን ዋጋ ማሰብ**
**(ሉቃ 14፥25-35)**

እኩልነትና ከልክ ያለፈ ቁሳዊነት ባለበት በዛሬው ዓለም የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ስለሚያስከፍለው ከፍተኛ ዋጋ ለመናገር ያስቸግራል:: ነጻ የጸጋ ስጦታን ከርካሽ ሥራ ጋር አምታተነዋል:: በመልካም ሥራችን እግዚአብሔርን እጅ ጠምዝዘን ድነታችንን ለማምጣትም አንችልም:: በሌላ በኩል ድነት በነጻ የሚገኝም አይደለም! ቤተ ሰባችንን፣ ትዳራችንን፣ ልጆቻችንን፣ ሀብታችንን፣ ማዕረጋችንንና ጊዜያችንን በዋጋነት ያስከፍለናል:: ሁሉንም መተውን ይጠይቃል::

ሉቃ 14፥25-27

[25]ብዙ ሕዝብ አብሮት እየተጓዘ ሳለ፣ ኢየሱስ
ዘወር ብሎ እንዲህ አላቸው፤ [26]«ወደ እኔ የሚመጣ
ሁሉ አባቱንና እናቱን ሚስቱንና ልጆቹን፣ ወንድሞቹንና



እኅቶቹን፣ የራሱን ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፣
ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም፤ [27]የራሱንም መስቀል
ተሸክሞ የማይከተለኝ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም::

[ቊ 25-27 = ማቴ 10፥37-38፤ የቊ 70ስን ማብራሪያ እና ማቴ 16፥24፤ ማር 8፥34፤ ሉቃ 9፥23 ይመልከቱ]

በፈሪሳዊው ቤት የተነሣው ታላቅ የነገር ፍንዳታ (ቊ 114) ሌላ አያሌ ሕዝብ በመሳብ ትኩረትን አስገኝቶአል:: ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ከአንድ ፈሪሳዊ ጋር በተመገበ ጊዜ (ሉቃ 12፥1) የሆነው ይኸው ነበር:: እነዚህ ድግሶች በከፊል ሕዝባዊ በመሆናቸውና የኢየሱስ የድግስ ላይ ንግግሮችም ወደ አንድ አቅጣጫ ያነጣጠሩ በመሆናቸው ማኅበረ ሰባዊ ፍላጎትን አነሣሡ::

ተከታዩ ሕዝብ ሲጓዝ ሳለ፣ ኢየሱስ ሳይታሰብና ከበፍተኛ ስሜት ወደ ሕዝቡ ዘወር አለ:: ይህ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ከሕዝቡ ለመጣው ባዶ አድናቆት መልስ ነበር:: ዛሬም ቢሆን ኢየሱስ ብዙ አድናቂዎች አሉት፤ ጠበቆቹ ግን ጥቂት ናቸው:: ግማሽ ምሁራዊ በሆነ መንገድ ስለ እርሱ መናገር ዝናን የሚያስገኝ ሆኖአል፤ ወይም ይሁዲ ወክርስትና የሆነን ሥነ ምግባር በተወሰነ መልኩ መከተል ዝና የሚያተርፍ ነው:: ይሁን እንጂ እውነተኛ ደቀ መዝሙር መሆን ከዚህ የሚለይ ነገር ነው:: ኢየሱስ ልዩነቱን ይገልጻል::

ደቀ መዝሙር መሆን ሙሉ ታማኝነትን ይጠይቃል:: ከቤተ ሰባችን እንኳን አስበልጠን ኢየሱስን መውደድ አለብን::[17] «መጥላት» የሚለው ቃል የተጋነነ ነው:: ለኢየሱስ ካለን ፍቅር ጋር ሲነጻጸር ግን

[17] ከአሕዛብ ወገን ተነሥቶ የእስራኤልን ሃይማኖት ከነሙሉ ግዴታው መከተል፣ ቤተ ሰብን መተውን ይጠይቅ እንደ ነበር Philo በሚያስደንቅ መልኩ ልብ ይላል (*De Specialibus Legibus* 51-52). M. Lattke, "The Call to Discipleship and Proselytizing" *HTR* 92/3 (1999): 359-362 ጋር ያነጻጽሩ::

ለቤተ ሰብ ያለን ፍቅር እንደ ጥላቻ ሊቈጠር ይችላል:: በተለይ በኢየሱስ ዘመን ኢየሱስን አክብሮ የቤተ ሰብ ኀላፊነትን ችላ ማለት እንደ ጥላቻ ይቈጠር ነበር:: የምንነጋገረው ስለ ቅደም ተከተል ነው:: የላቀ ትኩረት የሚሰጠውና ዋነኛ የሆነው ማን ነው? ከኢየሱስ በቀር ማንም የቅደም ተከተላችን የመጀመሪያ ከሆነ፣ ደቀ መዛሙርቱ ለመሆን ዝግጁዎች አይደለምን ማለት ነው::

ከዚህም በላይ አንድ ደቀ መዝሙር መስቀሉን በየቀኑ መሸከም አለበት (ቃል በቃል የራሱን መስቀል):: አንድ ሰው መስቀሉን ሲሸከም ወደ ኋላ የማይመለስበትን አንድ አቅጣጫ መንገድ በመያዝ ቀጥ ብሎ ይጓዛል:: መስቀሉ እንዲሁ ዝም ብሎ ሸክም፣ አገልግሎት፣ ወይም ምቾት ማጣት አይደለም:: ወይም ደግሞ ለኢየሱስ ለመሞት ፈቃደኛ መሆን አይደለም:: በኢየሱስ አድማጮች ላይ ድንጋጤ ያሳደረ የመግደያ መሣሪያ ነው:: እንግዲህ ልብ በሉ፤ የስቅላት ግድያ የሮም ቅኝ አገዛዝን የሚያስታውስ አስቀያሚ ማስታወሻ ነው:: የድርጊቱን ክፉነት ለማስገንዘብ ዘዳግም 21÷22-23 በዕንጨት ላይ የሚሰቀል የተረገመ ነው በማለት በግልጽ ያመለክታል:: አይሁዳውያን የተቀየሙት እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን በሚለውና ድፍረት የተሞላበት የኢየሱስ ጥያቄ ነው:: እውነቱ ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን ለዕድሜ ልክ የሞት ፍርድ የተጋለጠ መሆኑ ነው (ከገላ 2÷20-21፤ ከ2ቆሮ 5÷14-21፤ ከፊል 3÷4-11 ጋር ያነጻጽሩ)::

**ሉቃ 14÷28-30**

28«ከእናንተ አንድ ሰው ሕንጻ ለመሥራት
ቢፈልግ፣ መደምደም መቻሉ አለመቻሉን በመጀመሪያ
ተቀምጦ ዋጋውን የማይተምን ማን ነው? 29መሠረቱን
ጥሎ መደምደም ቢያቅተው፣ ያዩት ሁሉ ይዘባበቱበታል፤
30እንዲህም ይላሉ፤ 'ይህ ሰው ማነጽ ጀምሮ ነበር፤
መደምደም ግን አቃተው::' ...::»



ኢየሱስ ዋጋን ስለ መተመን ከተናገራቸው ሁለት ምሳሌዎች ይህ የመጀመሪያው ነው:: «መተመን» የሚለው ቃል መጀመሪያ የነበረው ትርጉም «በጠጠር ማስብ» ማለት ነው:: አንድን ዋጋ በጥንቃቄ ማስብን ያመለክታል:: እንዲሁ ግምት ሳይሆን፣ አንድ በአንድ እየታሰበ የተሰላ ሒሳብ ነው::

መሠረት የአንድ ሕንጻ በጣም አስፈላጊና ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ ክፍል ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ጅማሬ ብቻ ነው:: ብዙ ደቀ መዛሙርት በእምነት ይጀምራሉ፤ ከዚያም እምነታቸው ይሟጠጣል:: በዐፈር ምሳሌ ውስጥ ቋጥኝ የበዛበት መሬት ማለት ናቸው:: ዘሩ ቶሎ ይበቅላል፤ ግን ሥር አልሰደደም:: ስለዚህ ፀሐይ በመጠኑ እየሞቀ ሲሄድ ይጠወልጋል::

ሰው ዋጋ የሚያሰላበት አንድ ምክንያት መሣቂያ ላለመሆን ነው:: በጅምር የቀረ መሠረት የሞኝ ቤተ ሠሪ የገልተኝነቱ ማስታወሻ ሐውልት ሆኖ ሲቀር፣ የከተማው ሁሉ መሣቂያ መሳለቂያ ይሆናል::

**ሉቃ 14÷31-33**

31«ወይም አንድ ንጉሥ ከሌላው ንጉሥ ጋር
ጦርነት ሊገጥም በሚነሣበት ጊዜ፣ ሃያ አንድ ሺህ
ሰራዊት አስከትቶ የሚመጣበትን ንጉሥ፣ በዐሥር ሺህ
ሰራዊት መመከት እንደሚችል ተቀምጦ የማይመክር ማን ነው? 32መቋቋም
የማይችል ከሆነ፣ ሌላ ንጉሥ ገና ሩቅ ሳለ፣ መልእክተኞች ልኮ ዕርቅ ይጠይቃል::
33እንደዚሁም፣ ከእናንተ ማንም ያለውን ሁሉ የማይተው፣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን
አይችልም::

ይህ ሁለተኛ ምሳሌ በሕንጻ ላይ ሳይሆን በውጊያ ላይ ያተኩራል:: ለመዋጋት፣ ለመሸሽ ወይም ለመደራደር ትችላለህ:: ለመጋጠም ዐቅም ከሌለህና ለመሮጥ የማትችል ከሆንክ፣ ብትደራደር ይሻልሃል! ዋናው ጉዳይ ውጊያ ከመግጠምህ በፊት ውጊያውን በድል

ለመወጣት የሚያስፈልገው ነገር ያለህ ስለ መሆኑ በደንብ ማሰብህ ነው:: እንደዚሁም ወደ ኢየሱስ ከመምጣትህ በፊት በረጅሙ ጎዳና ለመጓዝ የሚስፈልገው ዐቅም ያለህ መሆኑን ማሰብ ይኖርብሃል:: የሚድኑት የታይታዎቹ ሳይሆኑ ታማኝ የሆኑት ናቸው!

በዓለም ያለነው «ለማሸነፍ የሚያበቃው ነገር አለውን?» ብለን እንጠይቃለን:: ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር «ይድን ዘንድ ሁሉን ነገር ትቷልን?» ብሎ ይጠይቃል:: ዓለም እናተርፍ ዘንድ፣ ክርስቶስ ግን እንሞት ዘንድ ይጠራናል:: ይህ ማለት ግን ምንም ዐይነት ሀብት ከቶ መያዝ የለብንም ማለት አይደለም:: ያለን ሀብት ሁሉ የእኛ አይደለም ብለን እንድናስብ ማስገንዘቡ ነው::[18] በዚህ መሠረት እንግዲህ ያለን ሁሉ በእግዚአብሔር ቊጥጥር ሥር ነው:: በመረጠው መንገድ ይገለገልበታል::

**ሉቃ 14፥34-35**

34«ጨው መልካም ነው፤ ጨው ጣዕሙን ካጣ ግን እንዴት ተመልሶ የጨውነት ጣዕም ሊኖረው ይችላል?

35ለመሬትም ሆነ ለማዳበሪያነት የማይጠቅም በመሆኑ ወደ ውጭ ይጣላል::

«ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ::»

[ቊ 34-35 = ማቴ 5፥13 በቊ 54ሐ ውስጥ ያለውን ማብራሪያና እንዲሁም ማር 9፥50 እና 91ን ይመልከቱ]

[18] የአፖታሴታዪ:- *apotassetai* («የማይተው») አንድምታ ይኸው ነው:: የአሁን ጊዜ ግስ መሆኑ በራስ ቊጥጥር ሥር ያለን ንብረት አዘውትሮ መተውን ያመለክታል:: T.E. Schmidt, "Burden, Barrier, Blasphemy: Wealth in Mt 6:33, Lk 14:33, and Lk 16:15," *TrinJ* 9 [n.s.] (Fall 1988): 171-189 በሚለው ጽሑፉ ኢየሱስ «ገንዘብን ስለ መተው በተናገረውና» እና እኛ ደግሞ የእርሱን ትእዛዝ ለመስማት ወይም ለመፈጸም ስላደረብን ቸልታ ብልኀነት የሞላበት ትንታኔ አለው::



ይህ በጣም የታወቀ የኢየሱስ ንግግር ነው::[19] ወደ ፍግ ማከማቻ መጣል አለበት የሚለው ተጨማሪ ዝርዝር ያለው እዚህ ቊጥር 35 ውስጥ ብቻ ነው:: ሶዲየም ክሎራይድ (ጨው) የማይቀየር ኬሚካል ነው:: ጨውነቱን አያጣም:: ስለዚህ የውሸት ስለ ሆነው ጨው መነጋገር አለብን:: ጨው ይመስላል፤ የጨው ባሕርይ ግን የለውም:: ዋጋ ቢስ በመሆኑ ኬሚካላዊ ንጥረ ነገሮች የሉትምና ለማዳበሪያነት እንኳ አያገለግልም::[20] ፈጽሞ ዋጋ የሌለው ነገር ነው::

ይህ አስፈላጊ ነገር ነው:: ኢየሱስ አድማጮቹ እንዲነቁና ለዕብራዊ ምሳሌ ጆሮቻቸውን እንዲሰጡ ያደረገውም ከዚህ የተነሣ ነው፤ «ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ::»



**§ 116**
**ጠፍቶ የነበረውና የተገኘው ምሳሌዎች**
**(ሉቃ 15፥1-32)**

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝና «ጠፍቶ ስለ መገኘት» የሚናገር ታላቅ ምዕራፍ ነው:: በመጀመሪያዎቹ ሁለት ጥቅሶች የተጀመረ ፍንዳታ መሰል ክርክር ነው:: ኢየሱስ ጠፍቶ የነበረ ሰው ሲገኝ የሚፈጠረውን ደስታ በማስመልከት ከዳር እስከ ዳር ሦስት ምሳሌዎችን ይናገራል:: የዚህ ምንባብ ሐሳብ ብዙ ሳይቆይ በፈሪሳዊው

[19] W. Nauck የአዲስ ኪዳን ዐበይት «የጨው» አባባሎች (ማር 9፥49-50፤ ሉቃ 14፥34-35፤ ማቴ 5፥13፤ ቈላ 4፥6 የረቢያዊ ጽሑፍ *Derek 'Erec Zuta* በጨው ላይ የሰጠውን ምሳሌ ዳራ በማድረግ ይተነትናል:: በደቀ መዝሙርነት ዐውድ ውስጥ የጨው ዘይቤ በእያንዳንዱ ጽሑፍ ላይ የጥበብና የታታሪነት ዘይቤ ተደርጎ ቢተረጎም በሚገባ ግንዛቤ ይገኝበታል ይላል:: ይህም ኢየሱስን ሲከተሉ በሚገባ ዋጋን ማስላትና ቃሉንም በጥበብ መስማት (ይኸውም መታዘዝ) ከሚለው ከያዝነው ዐውድ ጋር በሚገባ ይገጣጠማል (W. Nauck, "Salt as a Metaphor," *ST* [1952]: 165-178).
[20] E.P. Deatrick, "Salt, Soil, Savior." *BA* 25 (1962): 41-48.

የእራት ግብዣ ላይ መነሣቱ ሁኔታውን በተለይ አሳዛኝ ያደርገዋል::

> 1 አንድ ቀን ቀረጥ ሰብሳቢዎችና
> «ኀጢአተኞች» ሁሉ ሊሰሙት በዙሪያው ተሰበሰቡ::
> 2 ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ «ይህ ሰው ኀጢአተኞችን
> ይቀበላል፤ ከእነርሱም ጋር ይበላል» እያሉ አጉረመረሙ::
>
> *ሉቃ 15÷1-2*

ነገሩ የተጀመረው ኢየሱስ ከ«ኀጢአተኞች»[21] ጋር ወዳጅ በመሆኑ ፈሪሳውያን ባጉረመረሙ ጊዜ ነው:: በንቀትም እንዲህ አሉ፤ «ይህ ሰው ኀጢአተኞችን ይቀበላል፤ ከእነርሱም ጋር ይበላል ...::» የተነገረው እውነት ቢሆንም፣ የሚያዋርድ ሐሳብ ነው:: ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ስለሚበላ እርሱም እንደ እነርሱ ነው በማለት በነገር ጐሸሙት:: «አንድ ዐይነት ላባ ያላቸው ወፎች በአንድ ላይ ይበራሉ» የሚለውን አነጋገር ማመልከታቸው ነው:: ኢየሱስ ኀጢአተኞችን የሚቀበል በመሆኑ ዝናን አትርፎአል (ከሉቃ 7÷29:34:37 ጋር ያነጻጽሩ):: ቀረጥ ሰብሳቢ የሆነውን ማቴዎስን እንኳ ሳይቀር ከልዩ ሐዋርያቱ አንዱ እንዲሆን ጠርቶታል (ማቴ 9÷9-13):: ለመጋበዝ እቤቱ እስከ መሄድ ደርሶአል! በኋላ ደግሞ ዋና ቀረጥ ሰብሳቢ ከሆነው ዘኬዎስ ጋር ይመገባል::

ኢየሱስ ከኀጢአተኞች ጋር ሲበላ እነርሱ አያረክሱትም፤ እርሱ ግን ንጹሕ ያደርጋቸዋል:: ለምጻሙን በፈወሰ ጊዜ እንደ ሆነው ማለት ነው:: እርሱ ርኩስ በመደረጉ ፈንታ ለምጻሙ ንጹሕ ሆነ:: ኀጢአተኛን ፈልጎ ማግኘትና ማዳን ለኢየሱስ ምን ያህል ታላቅ ደስታ ነው!

[21] አመት (NIV) «ኀጢአተኞች» የሚለውን ቃል በጥቅስ ምልክት ማስቀመጡን ልብ ይበሉ:: ሉቃስ ራሱ ሳያደርግበት ይህ በቃሉ ላይ የተመለከተው የአርታዒ ጭማሬ ፈሪሳውያን ስለ ኢየሱስ ያላቸው ሐሳብ (አዝማሚያ) ምን እንደሚመስል ያንጸባርቃል::



**የጠፋው በግ** (ከማቴ 18÷12-14 ጋር ያነጻጽሩ)፤ አጽንዖት:- የጠፋው

> *ሉቃ 15÷3-7*
>
> 3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
> ነገራቸው፤ 4 «ከእናንተ መካከል አንዱ መቶ በጎች
> ቢኖሩትና ከእነርሱ አንዱ ቢጠፋበት፣ ዘጠና ዘጠኙን
> በሜዳ ላይ ጥሎ የጠፋውን እስኪያገኝ ድረስ ሊፈልገው
> የማይሄድ ማነው?
> 5 ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ተሸክሞ፣ 6 ወደ ቤቱ ይመለሳል፤ ወዳጆቹንና
> ጎረቤቶቹንም በአንድነት ጠርቶ፣ 'የጠፋውን በጌን አግኝቻለሁና ከእኔ ጋር ደስ
> ይበላችሁ' ይላቸዋል:: 7 እላችኋለሁ፣ እንደዚሁም ንስሓ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና
> ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፣ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል::

በእርሻ ሙያ የሚተዳደሩት አይሁዳውያን የኢየሱስ አድማጮች ይህን በቀላሉ ለመረዳት ይችላሉ:: በዙሪያቸው ሁሉ በጎች አሉ:: በጎች እንደሚጠፉም ማንም ሰው ያውቃል:: የታወቀና የጋራ ችግር ነው:: ሣር እየጋጡ እንዲሁ ይባዝናሉ:: ወዲያውኑ ቀና ብለው ሲመለከቱ ብቻቸውን ሆነው ያገኙታል:: የተለመደው ነገር አንዲት የጠፋች በግ እስከምትገኝ ድረስ ተኝታ የምትጮህ መሆኑ ነው:: ብዙ ጊዜ የጠፋን በግ መፈለግ የቡድን ጥረት ነው:: ስለዚህ ከኢየሱስ አድማጮች ብዙዎቹ ለራሳቸው ባይሆንም እንኳ ለወዳጅ ወይም ለጎረቤት ሲሉ፣ «የጠፋን በግ በመፈለግ» ተመክሮ ውስጥ ዐልፈዋል::

ጠፍቶ የነበረ በግ ሲገኝ የሚገኘውን ደስታ ሰዎቹ ያውቃሉ:: በጎች ጠቃሚ የግብርና ውጤቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ አጫዋቾችም ነበሩ:: እያንዳንዳቸው የራሳቸው ስም ያላቸው ሲሆኑ፣ ሙሉ በሙሉም በእረኛው ክብካቤ ሥር ናቸው:: ስለዚህ እረኛውና በጎቹ መልካም ግንኙነት ነበራቸው:: የጠፋን በግ መፈለግ ተገቢ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የጠፋ-

ሰዎቹን መፈለጉ አይቀርም ብለን ማሰብ የለብንም (ከ1ጴጥ 2፥25 ጋር ያነጻጽሩ)? ኢየሱስ የሚያደርገው እግዚአብሔር ያደርገዋል ብለን ተስፋ የምናደርገውን ነው፤ ይኸውም የጠፉትን መፈለግና ማዳን ነው። ይህ ይበልጥ እውነት ሆኖ የሚገኘው፣ ብሉይ ኪዳን ውስጥ፣ በግ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ መሆኑን ስንገነዘብ ነው (ከመዝ 23፥1 ጋር ያነጻጽሩ፤ 119፥176፤ ከሕዝ 34፥1 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዘካ 11፥16-17፤ ኢሳ 40፥11፤ 53፥6፤ ኤር 23፥1)።

እረኛው አንዱን በግ ለመፈለግ ሲሄድ ዘጠና ዘጠኙን ምናልባት ለረዳቶቹ ዐደራ ሰጥቶ ይሆናል። ዐጥር በሌለው ሜዳ ማንም ሰው የበግ መንጋውን ያለ ጠባቂ ትቶ አይሄድም። የጠፋውን የበግ ግልገል እንዳገኘ ትከሻው ላይ ይሸከመዋል። ይህ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የታወቀ ሥዕል ነበር፦

> ማንኛውንም የካታኮምቡ ክፍል ስንቃኝ ወይም ጥንታውያኑን የክርስቲያናዊ ቅርሶች ከምችት ገጾች ስናገላብጥ፣ ይህን ዐይነቱን ሥዕል በተደጋጋሚ ሳንመለከት አናልፍም። ከተርቱልያን ጽሑፎች እንደምንረዳው ብዙ ጊዜ በጽዋዎች ላይ ተሥሉ ነበር። ርጥበት ባለው ፕላስተር አማካይነት፣ በማስጌጫ ቀለም በመቃብሮች ግድግዳና በሮች ላይ ተቀርጾ እናገኘዋለን። ወይም በድንጋይ መቃብር ላይ ተቀርጾ እናያለን። በብርጭቆ ላይ በወርቅ ተቀርጾ፣ በመብራት ላይ እንደዚሁ ሆኖ እናገኘዋለን፤ በጣት ቀለበቶች ላይም ቅርጽ ሆኖ ይታያል፤ በሸምር ቃል ሲወርድ ሲዋረድ በመጣልን በማንኛውም ክርስቲያናዊ ቅርስ ላይ ተቀርጾ እናገኘዋለን።[22]

የጠፋን በማግኘት ደስታ አለ። ይህ ደግሞ ተፈጥሯዊ፣ ሰብዓዊና መለኮታዊ ባሕርይ ነው። የጠፋ ነገር በመገኘቱ ሐሤት

[22] Vincent, *Word Studies in the New Testament,* Vol 1. p. 383



እንደምናደርግ ሁሉ እግዚአብሔርም እንደዚሁ ሐሤት ያደርጋል። ባንክ ውስጥ ብር 1000.00 ቢኖረንና የብር 20.00 የገንዘብ መጠየቂያ ሰነድ ቢጠፋብን እስከምናገኘው ድረስ እንፈልገዋለን። ስናገኘው ደግሞ በባንክ ውስጥ ካለን ብር 1000.00 ይልቅ፣ ጠፍቶ ባገኘነው የብር 20.00 የገንዘብ መጠየቂያ ሰነድ ይበልጥ ደስ ይለናል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ ውድ ናቸው። ይሁን እንጂ የጠፉትን ነፍስ «በማግኘት» ረገድ በእግዚአብሔር ዘንድ ልዩ ደስታ አለ፤ «አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው የተስፋ ጌታ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ፣ ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ጴጥ 3፥9)።

**የጠፋው ሳንቲም፤** አጽንዖት፦ ፍለጋው

**ሉቃ 15፥8-10**

> 8«ወይም ዐሥር የብር ሳንቲሞች ያሏት ሴት ከዐሥሩ አንዱ ቢጠፋባት፣ እስክታገኘው ድረስ መብራት አብርታ፣ ቤቷን ጠርጋ፣ አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት? 9ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆቿንና ጎረቤቶቿን በአንድነት ጠርታ፣ 'የጠፋብኝን የብር ሳንቲም አግኝቸዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ' ትላለች። 10እላችኋለሁ እንደዚሁም ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል ...።»

አንዳንድ አስተውሎቶች ይህን ምሳሌ ከሕይወት ጋር ያስተሳስሩታል። በመጀመሪያ ይህች ሴት የጠፋባት ገንዘብ ከዐሥር የብር ሳንቲሞች አንዱ ነው። የአንድ ቀን ሥራ ዋጋ ያህላል። ሁለተኛ በዚያን ወቅት ሴቶች ከመደበኛ የቤተ ሰብ ሥራ ውጭ ራሳቸውን ችለው እንደማይሠሩ ስናስብ ይህ ገንዘብ ባሏ የሰጣት ወይም የማጫዋ ገንዘብ ክፍል ይሆናል ልንል እንችላለን። Jeremias የተባለ ሰው ማጫዋ

የራስ ልብስ ሆኖ ሊለበስ የሚችል ሲሆን ከተሰጣት ማጫ ውስጥ አንዱ ጠፍቶአል በማለት ያመለክታል።[23] ያም ሆነ ይህ የጠፋበት ለእርሷ ውድ የሆነ ሀብት ነው፤ ካጣችው አሳፋሪ ይሆንባታል። የጠፋባትን ለመፈለግ መብራት አበራች። አንድም ቤቷ በቂ መስኮት የለውም፤ ወይም የንጋቱን ብርሃን ለመጠበቅ ፈቃደኛ አይደለችም። አሁን ማግኘ ት አለባት! በዐፈር ወለል ላይ የምትኖር ከሆነ፣ አንድ ነገር ጠፍቶ ረጅም ሰዓት ከቆየ በዚያው ሁኔታ መቆየቱ አይቀርም። «ወዳጆቿን» የሚለው ግሪክኛ ቃል አንስታይ ጾታ መሆኑን እናስተውላለን። ለባሏ ስለ መናገሯ ርግጠኞች ለመሆን አንችልም። ሆኖም ለልብስ ሰፊ ወንፈልተኞቿ ተናግራለች። በዚህ ሁኔታ ነው ኢየሱስ፣ «ጠፍቶ ነበር ተገኘ» የሚለውን ትምህርት ወንዶችና ሴቶች በሚረዱት መንገድ የገለጸው።

<u>የጠፋው ልጅ፤</u> አጽንዖት:- እንደ ገና መመለስ

ሉቃ 15፥11-16

[11]ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ «አንድ
ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። [12]ከእነርሱም ታናሹ ልጅ
አባቱን፣ 'አባቴ ሆይ፤ ከሀብትህ ድርሻዬን ስጠኝ' አለው፤ አባትየውም ሀብቱን ለልጆቹ
አካፈላቸው።

[13]ብዙም ቀን ሳይቆይ፣ ታናሹ ልጅ ድርሻውን ሁሉ ጠቅልሎ ወደ ሩቅ አገር
ሄደ፤ በዚያም በማጋጣነት ንብረቱን አባከነ። [14]እርሱም ያለውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ፣
በዚያ አገር ሁሉ ጽኑ ራብ ሆነ፤ ይቸገርም ጀመር። [15]ስለዚህ ከዚያ አገር ነዋሪዎች
አንዱን ተጠጋ፤ ሰውየውም ዐሣማ እንዲቀልብለት ወደ ዕርሻ ላከው። [16]ዐሣማዎቹ
የሚመገቡትን ዐሠር እንኳ ለመብላት ይመኝ ነበር፤ ነገር ግን ይህን እንኳ
የሚሰጠው ሰው አልነበረም።»

[23] Jeremias, *Parables of Jesus,* (Philadelphia: Westminster, 1972), p. 134, contra J.D.M.Derrett, "Fresh Light on the Lost Sheep and the Lost Coin," *NTS* 26 (1979-80): 36-60.



Charles Dickens የተባለ ደራሲ ስለዚህ ምሳሌ ሲናገር፣ «ተጽፎ የማያውቅ እጅግ ውብ አጭር ታሪክ ነው» ብሏል። ከሦስቱ ምሳሌዎች ይህ እጅግ ዝነኛ ነውና ከተከታታዮቹ ታሪኮች ምጡቁ የሆነው ክፍል ነው። ይህ ብቻም አይደለም ኢየሱስ ከተናገራቸው ምሳሌዎችም ረጅሙ ነው። ሁለት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ስለ ጠፋው ልጅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ስለ አልጠፋው ልጅ ነው። ታሪኩ ውስጥ በቅድሚያ የቀረበው ልጅ በውጭ ጠፋ፤ ሁለተኛ ደግሞ ቤት ውስጥ ጠፋ። ሁለተኛው ልጅ እንደ ጠፋው ልጅ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ፈሪሳውያን (ያልጠፉት ልጆች) ከጠፉት ልጆች ጋር ኅብረት አለው ብለው ኢየሱስን ወደሚከሱበት ወደ ቍጥር 1-2 መልሶ ያመጣናል።

ታሪኩ ጊዜው ሳይደርስ የውርስ ድርሻውን በጠየቀው ታናሽ ልጅ ይጀምራል። የአንድ አይሁዳዊ ውርስ የሚካፈለው ባሉት ልጆች ቍጥር ልክና አንድ ዕጣ በሚባለው ስሌት ነው። ሦስት ወንድ ልጆች ካሉት በአራት ዕጣ ይከፋፈላል፤ አራት ወንድ ልጆች ካሉት በአምስት ዕጣ ይከፋፈላል፤ ወዘተ። የበኵር ልጅ «ሁለት እጅ» (ዘዳ 21፥17) የተባለውን ተጨማሪውን ድርሻ ይወስዳል። በታሪኩ የተጠቀሰው ሰው ሁለት ወንድ ልጆች አሉት። ርስቱ ለሦስት ዕጣ ተከፋፍሎ ነበር። አንድ ሦስተኛው ዕጣ አባት ሲሞት ለታናሹ ወንድ ልጅ እንዲሆን ተደርጎ ነበር።[24] ይሁን እንጂ እስከዚያ ድረስ የውርስ ድርሻውን የመጠየቅ ምንም ዐይነት መብት አልነበረውም። እንዲያውም የውርስ ድርሻን ጊዜው ሳይደርስ መጠየቅ ማለት፣ «አባዬ ሙት» እንደ ማለት ነው።[25] ይህ አሳፋሪ ቀበጥ ወጣት በአባቱ ጣራ ሥር ከእንግዲህ

[24] J.D.M. Derrett, "Law in the N.T.: The Parable of the Prodigal Son," *NTS* 14 (1967-68): 56-74፣ በሚለው ጽሑፍ ውስጥ የተወሰነ ሀብት የዕርሻውን መሬት ደኅንነት ለመጠበቅና ላላገቡ ሴት ልጆች ተለይቶ የሚቀመጥ መሆኑን ያመለክታል። ስለዚህ የልጁ ድርሻ ከ1/3 ይልቅ 2/9 ሳይሆን አይቀርም።

[25] E.H. Hiel, "'The Lost' Parables in Luke's Gospel Account" *CJ* 18 (1992); 244-258.

እንደማይኖር በድርጊቱ በመግለጥ ላይ ነው:: ማንኛውንም ነገር ሊያገኝ የሚችለው በአባቱ ቸርነት ብቻ ነበር::

አባት ንብረቱን ለሁለቱም ልጆቹ ማከፋፈሉን ልብ እንላለን:: ትልቁ ልጅም ድርሻውን ያገኛል:: ምናልባት እንደ ወንድሙ በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን በተስፋ ቃል ይሆናል ድርሻውን ያገኘው:: ድርሻውን የመቀበሉ ነገር ግን በምሳሌው መጨረሻ እንዳየነው ቅሬታውን አስከፊ አድርጎታል::

ታናሹ ልጅ ለነጻነት በመጓጓት፣ የተሻለ ነገር ፍለጋ ወደ ሩቅ ስፍራ ተጓዘ:: ትልቅ መከራ ገጠመው:: ሀብቱን በከንቱ የሚያባክንን እንዲህ ያለ ሰው መከራ እጅግ ነው የሚያጠቃው:: ተስፋ ቈረጠ:: ስለዚህ በአካባቢው ዐማማ አርቢ ለሆነው በአገልጋይነት ተቀጠረ:: ታስፈልገኛለህ ለማይለው ወይም ለማይፈልገው የሌላ ሀገር ሰው ራሱን ዳረገ:: በዚህ ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ፣ እንዲያውም ለአንድ አይሁዳዊ አስጸያፊ የሆነ ሥራ እንዲሠራ ተገደደ:: ሥራው ዐማማዎችን መመገብ ነበር:: አንድ አይሁዳዊ የደረሰበትን ወራዳ ሁኔታ ለማሳየት፣ ከዚህ የከፋ ሥዕል መሣሉ አስቸጋሪ ነው::

ነገሮች የከፉ ሊሆኑ አይችሉም በሚባሉበት ጊዜ ሆነው ይገኛሉ:: በጣም ስለ ራበው ለዐማማዎች የተዘጋጀውን ምግብ ለመብላት ወሰነ:: እንዲህ ያለው ምግብ የሚበላው የሚበላ ምግብ ሲታጣ ብቻ ነው:: በአይሁዳውያን ሌላ ጽሑፍ በጣም በከፋ ችግር ውስጥ እንዲህ ያለው ምግብ ተጠቅሷል፤ እንዲህ ያለው ምግብ የሚያገለግለው፣ የሚላስ የሚቀመስ ሲታጣ ብቻ ነው:: ምግቡ ትንንሽ ቀንዶች በሚመስል ቅርፅ ስለሚዘጋጅ *ኬሬሽን* - *keration* «ትናንሽ ቀንዶች» የሚል ስያሜ አግኝቶአል::



**ሉቃ 15፥17-20**

[17]«ልብ በገዛ ጊዜ ግን እንዲህ አለ፤ 'አንተ
የአባቴ ሠራተኛ ምግብ ተርፎታል፤ እኔ ግን እዚህ በራብ
ልሞት ተቃርቤአለሁ! [18]ተነሥቼ ወደ አባቴ ልሂድና፣
እንዲህ ልበለው፤ 'አባቴ ሆይ፤ በሰማይና በአንተ ፊት በድያለሁ፤ [19]ከእንግዲህ ልጅህ
ተብዬ ልጠራ አይገባኝም፤ ከተቀጠሩት አገልጋዮችህ እንደ አንዱ ቍጠረኝ::'
[20]ስለዚህም ተነሥቶ ወደ አባቱ ሄደ:: ...»

«ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና ለልጁ በጣም አዘነለት፤ ሮጦ በመሄድም አቅፎና ሳመው»::

ይህ ሁሉ አሳዛኝ ሁኔታ ይህን ልጅ ወደ እውነታ መለሰው:: «ልብ ... ገዛ::» ይህ ሐረግ ወደ ጤንነቱ መመለሱን ያመለክታል:: ወጣቱ ጥበበኛ ሆኖ ወደ አባቱ ቤት መመለስን መረጠ:: ዐማማ አርቢው ገበሬ፣ ባሪያ ከሚሆን ለአባቱ ባሪያ ቢሆን ይሻለዋል:: ወደ እርሻው እንደ ተቃረበ አባትየው አየውና ሊቀበለው ሮጠ:: በመካከለኛው ምሥራቅ እሩጫ የውርደት ድርጊት ነው::[26] ይህ አባት በልጁ ደስ ስለ ተሰኘ ተገቢውን ፕሮቶኮል ችላ አለ:: ቁሞ መጠበቁን ወይም ዝም ብሎ እስከ ጕዞው ፍጻሜ ያየው መሆኑን አይደለም ኢየሱስ የገለጠው:: አባት ለዕርቅ የመጀመሪያውን እርምጃ (ተነሣሽነት) መውሰዱን ነው ያስገነዘበው:: የዐማማን ቆሻና ክርፋት እንደዚሁም የተበጣጠሰውን ልብስና ባዶ ኪሶች ችላ ብሎ በናፍቆት በመሳሳም [*ካቴፊለሰን* - *Katephilesen*] ልጁ አንገት ላይ ተጠመጠመ::

**ሉቃ 15፥21-24**

[21]«ልጁም፣ 'አባቴ ሆይ፤ በሰማይና[27] በአንተ
ፊት በድያለሁ፤ ከእንግዲህ ልጅህ ተብዬ ልጠራ
አይገባኝም' አለው::»

---

[26] ስለዚህ ታሪክ ሌላ ተጨማሪ ዝርዝር ለመረዳት K.E. Bailey, "The Pursuing Father," *CT* 42/12 (1998). 34-40 ይመልከቱ::

[27] «በሰማይና . . . በድያለሁ» የሚለው ገለጣ ዕብራዊ አባባል ሲሆን፣ «እግዚአብሔርን በድያለሁ» ማለት ነው:: በደሌ «ሰማይ ደርሶአል» የሚለውንም ሊያመለክት ይችላል (Liefeld, ገጽ 984)::

[22]«አባቱ ግን አገልጋዮቹን እንዲህ አላቸው፤ 'ፈጥናችሁ ከሁሉ ምርጥ የሆነውን ልብስ አድርጉለት፤ [23]የሰባውንም ፍሪዳ አምጡና ዕረዱ፤ እንብላ እንደሰት፤ [24]ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፤ አሁን ግን ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር፤ ተገኝቶአል::' ከዚያም ይደሰቱ ጀመር::»

*[*21] አንዳንድ ቅጆች ከተቀጠረት አገልጋዮችህ እንኳ እንደ አንዱ ቁጥረህ ተቀበለኝ የሚል አገባብም አላቸው::*

ጠፍቶ የነበረው ከመጀመሪያውኑ ልጅ በአባቱ ቤት አገልጋይ እሆናሁ ብሎ ዐሰበ:: በንግግሩም ይህንኑ ቃል በቃል አጥንቶአል (ቊ. 18-19):: ነገር ግን አባት የልጁን ግማሽ ንግግር እንኳን ሳይሰማ (ቊ. 1)፣ አገልጋዮቹን ማዘዝ ጀመረ፤ ለልጁም ለጨዌ ልጅ የሚደረገውን ነገር ሁሉ ለመፈጸም ብዙ ገንዘብ አወጣ::

ምርጥ ልብስ፣ ቀለበትና ጫማ የምቾት ምልክቶች ከመሆን በላይ የልጅነትና የነጻነት ምልክቶች ናቸው:: ልብሱ ለተከበረ እንግዳ የሚሰጥ ዐይነት ሲሆን፣ ቀለበት የሥልጣን ምልክት ነው:: ባሮች ባዶ እግራቸውን ይሄዳሉና ጫማ ነጻነትን ይወክላል:: አባት የጠፋ ልጁን በተከበረ ቦታ ላይ መልሶ አስቀመጠው:: በአጭር ቃል፣ «አሁን ልጁ ሕያው ሆኖአል::» «ለትንሣኤ» የሚሆነው ይህ አገላለጽ የኀጢአት ውጤት ምን ያህል የከፋ መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ምሳሌ የአዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት ዘር አለው - በኀጢአት ሙት ግን በክርስቶስ ሕያው መሆን (ሮሜ 6÷4:9:11፤ 7÷4፤ 8÷10-11፤ ኤፌ 2÷5፤ ቈላ 2÷13)::

ሉቃ 15÷25-32

[25]«በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጅ በዕርሻ ቦታ ነበረ፤ ከዚያም ተመልሶ ወደ ቤት በተቃረበ ጊዜ፣ የሙዚቃና



የጭፈራ ድምፅ ሰማ፤ [26]እርሱም ከአገልጋዮቹ አንዱን ጠርቶ ነገሩ ምን እንደ ሆነ ጠየቀው:: [27]አገልጋዩም፣ 'ወንድምህ መጥቶአል፤ በሰላም በጤና ስለ መጣም አባትህ የሰባውን ፍሪዳ ዐርዶለታል' አለው::

[28]ታላቅ ወንድሙም ተቈጣ፤ ወደ ቤትም መግባት አልፈለገም፤ አባቱም ወደ ውጭ ወጥቶ እንዲገባ ለመነው:: [29]እርሱ ግን መልሶ አባቱን እንዲህ አለው፤ 'እነሆ፤ ይህን ያህል ዘመን እንደ ባሪያ አገለግዬሃለሁ፤ ከትእዛዝህም አንዱን እንኳ አላጓደልሁም፤ አንተ ግን ከባልንጀሮቼ ጋር እንድደሰት አንዲት የፍየል ግልገል እንኳ አልሰጠኸኝም፤ [30]ነገር ግን ይህ ልጅህ ንብረትህን ከጋለሞቶች ጋር አውድሞ ሲመጣ፣ የሰባውን ፍሪዳ አረድህለት::'

[31]«አባቱም ልንዲህ አለው፤ 'ልጄ ሆይ፤ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ [33]ይህ ወንድምህ ግን ሞቶ ነበር፤ ሕያው ሆነ፤ ጠፍቶ ነበር ተገኘ፤ ስለዚህ ደስ ሊለንና ፍሥሐ ልናደርግ ይገባናል::'»

ይህ ምሳሌ ታላቁን ወንድም አስመልክቶ ሁለተኛውን ክፍል ይጀምራል:: ይህ የክርክር መደምደሚያ፣ ኢየሱስ ከቀረጥ ሰብሳቢዎችና ከኀጢአተኞች ጋር ጊዜ በማጥፋቱ ፈሪሳውያን ወደ ተበሳጩበት ወደ ቊጥር 1 እና 2 መልሶ ያመጣናል::

ታላቅ ወንድም ከዕርሻ ሲመለስ ሙዚቃና (ሲፎኒያስ) ዳንስ [ኮሮን] ይሰማል:: ጉጉት ያደረበት መሆኑ ግልጽ ነው:: ለአንድ ሰው ያልታሰበ ድግስ ተደግሶአል:: ምናልባት ለእኔ ነው ብሎ ሳያስብ አልቀረም:: የጠፋው ታናሽ ወንድሙ ወደ ቤት ማምጣቱንና ድግሱ የተዘጋጀውም ለእርሱ መሆኑን አንድ አገልጋይ ሲነግረው በቍጣ ነዶ ወደ ቤት አልገባም አለ:: ታናሽ ወንድሙ ጠብ በመሻት ውርስ እንዲሰጠው ጠየቀ፤ አባቱን አዋርዶአል፤ ሀብቱን አባክኖአል፤ የቤት ስሙንም አንገት አስደፍቶአል:: ታላቅ ወንድም በነገር አካሄድ ረገድና (በተጠየቅ) በሕግ ረገድ መቈጣቱ ትክክል ነው:: ይሁን እንጂ የሕግ

ጽሑፍ ከሕጉ መንፈስ ጋር ሁሌ አብሮ አይጓዝም:: ከቅጣት የሚበልጡት ርኅራኄና ይቅርታ ይጐድሉታል::

አባት ታላቅ ልጁን ለመቀበል ወደ ውጭ ወጣ::[28] ያንለት የጠፋ ልጅ ለማግኘት ለሁለተኛ ጊዜ መውጣቱ ነው:: ታላቁ ልጅ ግን ቤት ውስጥ በመካሄድ ላይ በነበረው ድግስ ስለ ቀና የግሉን መናኛ ነገር ለመተው ዝግጁ አልነበረም:: «እነሆ፤» የሚለው ቃል የዚህን ግንኙነት ድምፀት እውን ያደርገዋል:: ወንድሙን ብቻ ሳይሆን አባቱንም ወቅሶአል:: «ይህ ልጅህ» የሚለው ቃል እንደ ታመመ አውራ ጣት ጉልቶ ይታያል:: ጠፍቶ የነበረውን ልጅ ወንድሜ ብሎ ለመጥራት ፈቃደኛ አይደለም:: እውነት ስለ መሆናቸው እርግጠኛ የማይሆንባቸውን ክሶች በወንድሙ ላይ አቀረበ:: ለምሳሌ ታሪኩ የጠፋው ልጅ ከጋለሞታዎች ጋር ግንኙነት የነበረው ስለ መሆኑ አይገልጥም::

የአባትየው መልስ ጨዋና የኃላፊነት ስሜት ያለበት ነው:: ታላቁ ልጅ ሽልማት ይጠብቀዋል፤ ይህን ተገቢ ሽልማትም ያገኛል:: ጉዳዩ ግን ይህ አይደለም:: ቀዳሚው ጉዳይ ፍትሕ ማግኘት ሳይሆን ሐሤት ማድረግ ነው:: ወንድሙ[29] ጠፍቶ ነበር፤ አሁን ግን ተገኝቶአል (ኤፌ 2፥1-5)::

ይህን ሦስተኛ ምሳሌ የምንቋጨው፣ የጠፋው ልጅ በመገኘቱ ምክንያት ስለ ተፈጠረው ደስታ በመግለጥ ነው:: ይሁን እንጂ ታላቁ ወንድም ስ‾ ˙ን የሚማርክ አዲስ ነገር ያክላል:: ምን ሆነ? ከአባቱ

[28] G.W. Ramsey, "Plots, Gaps, Repetitions, and Ambiguity in Luke 15," *PRS* 17 (1990): 33-42 በማለት በጻፈው መሠረት አባትየው ልጁን ለመገናኘት መውጣቱ የምሳሌው ግማሽ ከፍተኛ ደረጃ ላይ (ጣራ ላይ) የደረሰበት ክፍል ነው::

[29] አባትየው መልሰ ሲመልስ ተመሳሳይ ሐረግ የተጠቀመ መሆኑን አስደናቂ ሐቅ "ho adelphos sou houtos . . ." (ቊ 32) (T. Corlett, "This *Brother* of Yours" *ExpT* 100 [1989]: 216) ሉቃስ ልብ ማለቱን የሚያንጸባርቁት በጣም ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጒሞች ናቸው::



ጋር ወደ ቤቱ ገብቷል? ወይስ አልገባም? ወንድሙ በመመለሱ ሐሤት ማድረግ አልጀመረም? ኢየሱስ ይህን አልተናገረ ይሆናል፤ ምክንያቱም ታሪኩ ገና አላለቀም:: ኢየሱስ ከጠፉት ልጆች መካከል ማለት ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች መካከል ቆሞአል:: ፈሪሳውያን ደግሞ ከዳር ቆመዋል:: ታሪኩ አሁንም እንደ ቀጠለ ነው:: ወጤቱ ገና አልተወሰነም::

**§117 ሀ**
**የብልኁ መጋቢ**
**ምሳሌነት**
**(ሉቃ 16፥1-13)**

የምዕራፍ 16ን ዐውድ ለመረዳት ወደ 15፥1-2[30] መመለስ ይኖርብናል:: ኢየሱስ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና ኀጢአተኞች በዙሪያው እንዲሆኑ ፈቅዷል:: ፈሪሳውያን ነቀፋቸውን እየሰነዘሩ ዳር ቆመዋል:: ምዕራፍ 15 በፈሪሳውያን ላይ ያነጣጠሩ ሦስት ተከታታይ ምሳሌዎችን ያቀፈ ነው:: የጠፉትን ለመፈለግ እግዚአብሔር ያደረገውን ተነሣሽነት ይናገራሉ:: በሌላ በኩል ምዕራፍ 16 የሚናገረው ስለ ሰዎች ተነሣሽነት ነው:: ከዚህ ላይ ጥንድ ምሳሌዎች አሉን:: የመጀመሪያው ወደ ደቀ መዛሙርቱ ያነጣጠረ ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደ ገና ወደ ፈሪሳውያን ያነጣጥራል:: የመጀመሪያው ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ገንዘባችንን እንዴት

[30] የኤን አይ ቪ ትርጒም አስፈላጊ የሆነ ቃል ትቶአል:- «በተጨማሪም::» «በተጨማሪም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤» ይህ ምዕራፍ ዐሥራ ስድስትን ከምዕራፍ 15፥1:2 ጋር ይያያዛል፤ M.R. Austin, "The Hypocritical Son" *EvQ* 57 (1985): 307-315 በሚለው ጽሑፉ የጠፋው በግ ምሳሌና የጠፋው ሳንቲም ምሳሌ ጥንዶች ናቸው፤ ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌና የብልኀ መጋቢ ምሳሌ ደግሞ ጥንዶች ስለሆኑ አንዱ ከሌላው ጋር ተያይዞ መነበብ አለባቸው ይላል:: በተጨማሪም David Landry, "Honor Restored: New Light on the Parable of the Prudent Steward (Lk 16:1-8a); *JBL* 119/2 (2000): 287-309, ይህ ምሳሌ ቀድሞት ከተጻፈው ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌ ጋር በአወቃቀር ረገድ ተመሳሳይ ነው:: ስለዚህ ሁለቱ ምሳሌዎች በፍቻቱ ረገድ ተያይዘው መታየት አለባቸው ይላል::

መጠቀም እንዳለብን ይነግረናል:: ሁተኛው ወደ ሲኦል ለመግባት ገንዘባችንን እንዴት መጠቀም እንዳለብን ይነግረናል::[31]

[1]ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤ **ሉቃ 16÷1-4**
«አንድ ሀብታም ሰው አንድ መጋቢ ነበረው፤ ይኸው
መጋቢ የሀብታሙን ሰው ንብረት እንደሚያባክን ለዚሁ
ሀብታም ሰው ወሬ ደረሰው:: [2]ስለዚህ አስጠራውና፣ 'ይህ የምሰማብህ ምንድን ነው? ከእንግዲህ አንተ መጋቢ ልትሆነኝ ስለማትችል የምታስተዳድረውን ንብረት መቆጣጠሪያ ሒሳብ አስረክበኝ' አለው::
[3]«መጋቢውም በልቡ እንዲህ አለ፤ 'ጌታዬ ከመጋቢነት ሊሽረኝ ነው፤ ለማረስ ጉልበት የለኝም፤ መለመን ደግሞ ዐፍራለሁ፤ ስለዚህ ምን ላድርግ? [4]ከመጋቢነት
የተሻርሁ እንደ ሆነ ሰዎች ቤታቸው እንዲቀበሉኝ የማደርገውን ዐውቃለሁ::'»

አንድ ጊዜ ከአገልጋዮቹ አንዱን በቤቱ ጉዳይ ሁሉ አለቃ ያደረገ ይህ ሀብታም ሰው ነበር:: አገልጋይ ነጻ ሰው ወይም በምግብ ቤት ውስጥ የገበታ ጠረጴዛ የሚያጸዳ ሰው አልነበረም:: የአለቃውን ሀብት ማለትም ምግብ፣ ደመወዝ፣ ወዘተ ማከፋፈል ነበር የሥራ ድርሻው:: አላግባብ የተጠቀመበት ይሁን እንጂ የተሰጠው ኀላፊነት ከፍተኛ ነበር:: አንድ ሰው ቃል ኪዳኑን አስሽሮታል:: ይህም ለአደገኛ ሁኔታ ዳርጎታል:: ወንበር ላይ ተቀምጦ ከሚያከናወነው ቀላል ሥራ ሰሊሰናበት ነው:: የነበሩት ምርጫዎች ጥቂትና የማይስቡ ነበሩ::

እንዲህ ያለ ታለቅ ኀላፊነት ያለው ሰው ወዲያውኑ ሊሰናበት አይችልም፤ የወረቀት ሥራውን ማጠናቀቅ፣ የዕቃ ዝርዝርን ማዘጋጀትና ጠረጴዛውን ንጹሕ ማድረግ አለበት:: ይህን አነስተኛ

---

[31] H.K. Farrell እንደሚለው የሉቃስ የጉዞ ትረካ ሰንሰለታዊነት (9÷51-19÷44) እነዚህን ምሳሌዎች ሉቃስ 12÷16-21 ውስጥ በገንዘብ ላይ ከተደረገው ንግግር ጋር ያጣምራቸዋል፤ The Structure and Theology of Luke's Central Section *TrinJ* 7 (1986): 33.



የዕድል በር ለራሱ ጥቅም አዋለው:: ኢየሱስ ለዚህ ድርጊቱ አሞገሰው:: የደገፈው ያከናወነውን ሥራ ሳይሆን የአሠራር ዘዴውን ነበር::

**ሉቃ 16÷5-9** [5]«ስለዚህ የጌታው ዕዳ ያለባቸውን ሰዎች
እያንዳንዳቸውን ጠራ፤ የመጀመሪያውንም ሰው 'የጌታዬ
ዕዳ ምን ያል አለብህ'? አለው::
[6]«እርሱም፣ አንድ መቶ ማድጋ[‖] ዘይት አለብኝ አለ::
«መጋቢውም፣ 'የውል ወረቀትህን እንካ፣ ቶሎ ተቀምጠህ «አምሳ ማድጋ»
ብለህ ጻፍ' አለው::
[7]«ከዚያም ሌላውን፣ 'አንተስ ስንት አለብህ'? አለው::
«እርሱም 'አምሳ ዳውላ[†] ስንዴ' አለው::
«መጋቢውም፣ 'የብድር ደብዳቤህን እንኪ፣ «አርባ ዳውላ» ብለህ ጻፍ'
አለው::
[8]ጌታውም አጭበርባሪውን መጋቢ በብልኀነቱ አደነቀው፤ የዚህ ዓለም ልጆች
ከመሰሎቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ከብርሃን ልጆች ይልቅ ብልኆች ናቸውና::
[9]ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የዚህ ዓለም ገንዘብ ባለቀ ጊዜ በዘላለም ቤት ተቀባይነት
እንዲኖራችሁ በዚሁ ገንዘብ ወዳጆችን ለራሳችሁ አፍሩበት::»

*‖6 ምናልባት 3ሺህ ሊትር ይሆናል::*
*‖7 ምናልባት 35 ሺህ ሊትር ይሆናል::*

መጋቢው ዕዳን ማቃለል ወዳጆችን ያፈራል:: የቤቱ መጋቢ እንደ መሆኑ መጠን ያን ለማድረግ አሁንም ሥልጣን አለው:: ይህ «ሰነድ» ዕዳ እንዲከፈል የሚያደርግ በግራ ቀኙ ወገኖች የተፈረመ ነበር:: ለባለ ዕዳው ከተመለሰለት ከግዴታው ነጻ ነበር:: ሒሳቡ «ሙሉ

በሙሉ» ተከፍሏል:: ይህ ሥነ ምግባራዊ ተግባር ባይሆንም፤ ሕጋዊ ነበር::

ጄ.ዲ.ኤም የተባለው ጸሐፊ እንደ ገለጸው መጋቢው የቀነሰው ዕዳውን ሳይሆን ብድሩ በጊዜ ሂደት ያስገኘውን ወለድ ነበር:: ጉዳዩ ይህ ቢሆን ኖሮ የብሉይ ኪዳንን ሕግ በትክክል ተከትሎ ነበር ማለት ነው (ዘፀ 22፥25፤ ዘሌ 25፥36-37፤ ዘዳ 15፥7-8፤ 23፥19-20)::[32] ይህ ተግባር የጌታውን ገቢ የሚቀንስ ቢሆንም፣ ዝናውን ከፍ ያደርግለታል:: እስከዚያ ሂደት ድረስ ለመጋቢውና ለጌታው የሚጠቅም፣ ጥበብ የተሞላበት እንቅስቃሴም ነበር::

ጌታው መጋቢውን አደነቀው:: እርግጥ ነው በመጭበርበሩ ደስ አልተሰኘም፤ ይሁን እንጂ በብልኀ መጋቢ ዕቅድ ተማርኳል::

[32] J.D.M. Derret, "Fresh Light on St Luke 16:1, The Parable of the Unjust Steward," *NTS* 7 (1961): 198-219. ይሁን እንጂ የDerrett's መደምደሚያው የተመሠረተው እስከ ሦስተኛው ምእት ዓመት መባቻ ድረስ በሕግ ሰነድነት ባልተያዘው በሚሻህ ጽሑፍ ላይ ነበር:: በተጨማሪም ምሳሌው አገልጋዩ ወለዱን መክፈል ከነበረበት ሀብት መቀነሱን አያመለክትም:: እንዲያውም፣ «አጭበርባሪውን መጋቢ» *[ቶን ኦይክኖሞን ቴስ ኣዲካያስ - ton oikonomon tes adikias]* የሚለው አገላለጽ መጋቢው መልካም ሰው ነበር የሚለውን አተያይ ያስተባብላል:: J.A. Fitzmyer, "The Story of the Dishonest Manager," *TS* 25 (1964): 23-42 በሚለው ጽሑፍ አማራጭ ገለጻ ያቀርባል:: መጋቢው ዕዳን የቀነሰው ሊያገኘው በሚችለው ኮሚሽን መጠን መሆኑን ሐሳብ ያቀርባል:: ስለዚህ Fitzmyer እና Derrett የመጋቢው ተግባር ሕጋዊና አርአያነት ያለው ነው በማለት ይተረጉማሉ:: ይህም ጌታው የተጭበረበረ ሥራን የማወደሱን ሁኔታ ጥያቄ ውስጥ ያስገባል:: ሁቱም ትወራዎች የጥንት የሥራ ውሎችንና (ኮንትራቶችን) የመጋቢዎችን ሥራ በተመለከተ ያሉትን በእጅ የሚገኙ ማስረጃዎች ችላ በማለት የሚጓዙ ይመስላል:: እንዲህ ያለ አመለካከት ያላቸው D. Landry እና B. May መጋቢው ያደረገው መልካም ነገር ነው በማለት ሐሳብ ያቀርባሉ:: ዋናው ጉዳይ ገንዘብ ሳይሆን ክብር ነው ይላሉ:: መናኛ ገንዘብ በመስረቅ አገልጋዩን መቈጣጠር ባለመቻሉ መሣቂያ የሚሆነውን ጌታውን ለኀፍረት ዳረገ:: ይሁን እንጂ አገልጋዩ ዕዳን ሲቀንስ ጌታው ቸር ተደርጎ እንዲታይ ያደርገዋል:: ስለዚህ አገልጋይ የጌታውን ዝና የሚቀንስ ነገር ከማድረግ ተቆጠበ:: "Honor Restored: New Light on the Parable of the Prudent Steward (Lk 16:1-8a," *JBL* 119/2 (2000): 287-309.



በእነዚያ ዘመናት አገልጋዮች አንዳንድ ጊዜ ጌታቻቸውን ያጭበረብሩ ነበር:: እርዳታ የተደረገላቸውም በምላሹ ብድራት እንዲከፍሉ ግዴታ ነበረባቸው::[33]

ኢየሱስ መጥፎ ሰውን የመልካም ምሳሌ አርአያ አድርጎ ተጠቅሞአል ብለን እንመን?[34] ለምን አናምንም? ጠላት እንኳ በተጋጣሚው ብልኀት ሊማረክ ይችላል::[35] ይህን የመሰለውን የነገር አካሄድ (ተጠየቅ) ያልተጠቀመ ወላጅ ማን አለ? አካሄዱ ይህን ይመስላል:- «ያ ብልሹ ተረፈ ዳርጌ (የፈጠራ ስም ነው) ለታናሽ እኅቱ መልካም ሰው ለመሆን ከቻለ፣ ያለጥርጥር አንተ ብዙ ልትሠራ ትችላለህ!»

ኢየሱስ የሰውየውን አታላይነት (ሸፋጭነት)፣ አባካኝነት፣ ስንፍናውን ወይም ትዕቢቱን አላሞገሰም:: ያሞገሰው ለሚመጣው አጋጣሚ ለመዘጋጀት አሁን ያለውንና ጊዜያዊ የሆነውን ሥልጣንና ሀብት የመጠቀም ችሎታውን ነው:: እኛ የብርሃን ልጆችም ከዚህ ያነሰ

[33] ከ John S. Kloppenborg, "The Dishonoured Master (Luke 16:1-8a)" *Biblica* 70 (1989): 474-495 ጋር ያነጻጽሩ::

[34] አንዳንዶች ኢየሱስ መጥፎውን ሰው መልካም ምሳሌ አድርጎ በማቅረቡ ነገሩን መረዳቱ ይቸግራቸዋል:: በመሆኑም የኢየሱስን ቃሎች ምጸት ናቸው ይላሉ:: ኢየሱስን የሚረዱት በዚህ መልኩ ነው፣ «በል እንግዲህ ገንዘብ አሳዳጆችን ወዳጅ ለማደረግ ሞክር፤ በዘላለም ሕይወት ውስጥ ያግዙህ እንደ ሆነ ታያለህ»:: ስለዚህ መጋቢው መደረግ የሌለበት ነገር ምሳሌ ነው (ከ D.R. Fletcher, "The Riddle of the Unjust Steward; Is Irony the key?" *JBL* 82 [1963]: 15-30) ጋር ያነጻጽሩ::

[35] ጮሌ አገልጋይ ጌታውን በብልኀት በልጦ በመገኘቱ ክብር የተቸረው መሆኑን የሚያሳይ በግሪክ ወሮማን ሥነ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎች አሉ:: እነዚህ በተለይ ከኤሶፕና ከፕለተስ ሕይወት የተገኙ ናቸው:: M.A. Beavis, "Ancient Slavery as an Interpretive Context for the New Testament Servant Parables with Special Reference to the Unjust Steward (Lk 16:1-8)," *JBL* 111/1 (1992): 37-54 ይመልከቱ:: አንዳንዶች በዚህ ታሪክ ላይ የእግዚአብሔርን ሥራ በአገባቡ ባለመወጣቱ ታማኝ ያልሆነው ኢየሱስ ነው እስከ ማለት ደርሰዋል (ከ W. Loader, "Jesus and the Rogue in Luke 16:1-8a: The Parable of the Unjust Steward," *RB* 96/4 [1989]: 518-532 ጋር ያነጻጽሩ)::

ማድረግ የለብንም:: ለዘላለም ሕይወት ለመዘጋጀት ኀይላችንን፣ ሀብታችንንና ችሎታችንን መጠቀም አለብን:: ይህን የምናደርገውም ቢያንስ በሁለት መንገዶች ነው: መጀመሪያ ሀብታችንንና ችሎታችንን የምንጠቀመው በዘላለማዊ ነገሮች ላይ ለማከማቸት ነው (ማቴ 6÷19-21:33):: እርዳታ አልባ በምንሆንበት ጊዜ (ለምሳሌ ፍርድ) ሊረዱን የሚችሉተን ወዳጆችን (በተለይ የእግዚአብሔርን ወዳጅነት) እናፈራለን፤ ይኸውም ሥራችንን ስናጣ (ማለትም ስንሞት) ምቹ ስፍራ እንዲኖረን ነው:: ሁለተኛም ያለንን ሀብትና ችሎታ በመጠቀም ለጠፉት ወንጌልን እንሰብካለን:: እነርሱም በበኩላቸው ለወደፊቱ እንዲዘጋጁ ነው ይህን የምናደርገው:: እነዚህ ሁለቱም ጉዳዮች በሁለተኛው ምሳሌ ላይ (ቊ 19-31) በይበልጥ በጉልሕ እንዲታዩ ይደረጋል::

የብርሃን ልጆች የዋሆች ሊሆኑ ይችላሉ (ኤፌ 5÷8)! ብልጦች ብንሆን የክርስትና ሕይወታችን ጐደሎ ይሆንብናል ብለን እንሠጋለን:: በመንግሥቱ ሥራ ውስጥ ዓለማዊ ችሎታዎችን ወይም ስልቶችን መጠቀም የለብንም ብለን እናስባለን:: ኢየሱስ ግን «እንደ እባብ ብልኆች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ» ብሎአል (ማቴ 10÷16):: ለዚህ ዓለም የብልኀተኝነት ምሳሌዎች መሆን አለብን::

ይህ «ሀብትን በብልኀት የመጠቀሙ ጉዳይ» ገንዘባችንንም ማካተት አለበት፤ ይህ በተለይ ገንዘብ የተረፈንን ወገኖች ሁሉ ይመለከታል! ጥበብ የተሞላበት የገንዘብ አጠቃቀም ለጊዜያዊ ደስታ ሳይሆን ለዘላለም ዋስትና መሆን ይኖርበታል:: አሁን ለድኾች የምናውለውን ገንዘብ በዘላለም ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ይቈጥረዋል:: ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በሁለተኛው ምሳሌ ላይ ተገልጾአል፤ ቊ 19-31::

**ሉቃ 16÷10-13**

10«በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም
ይታመናል፤ በትንሽ ነገር ያልታመነ በትልቁም
አይታመንም:: 11እንግዲህ፣ በዚህ ዓለም ሀብት

ካልታመናችሁ፣ እውነተኛውንማ ሀብት ማን ዐደራ ብሎ
ይሰጣችኋል? 12በሌላው ሰው ሀብት ካልታመናችሁ፣
የራሳችሁ የሆነውን ሀብት ማን ይሰጣችኋል?
13«በአንድ ጊዜ ሁለት ጌታዎችን ማገልገል የሚችል ማንም ባሪያ የለም፤
አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን ይጠጋል፤ ሌላውንም ይንቃል::
የእግዚአብሔርም የገንዘብም ባሪያ መሆን አትችሉም::»

ይህ ሳይታለም የተፈታ ነው፤ ከግሮሰሪው ትንሽ ትንሽ የሚሰርቅ ተራ ሠራተኛ ከመጨረሻው የኀላፊነት ደረጃ ላይ ሲደርስ ኩባንያውን ማጭበርበሩ አይቀርም:: ያለውን 5 ብር በከንቱ የሚያጠፋ ሰው ሎተሪ ሲደርሰውም እንዲሁ በከንቱ ገንዘቡን ማጥፋቱ አይቀርም:: የዚህ ተቃራኒው ደግሞ እውነት ነው:: የሚሰጠውን የዕለት ወጭ በብልኀት የሚያጠፋ ልጅ፣ ጕልማሳ ሰው ሲሆን አስተማማኝ ሀብት ይኖረዋል:: ከተከፈላት ትንሽ ገንዘብ ዐሥራት የምትሰጥ ሴት፣ ካገኘችው ከፍተኛ የውርስ ቸክ ዐሥራት መክፈሏ አይቀርም::

ይህ እውነት ከሆነ፣ እግዚአብሔር ቁሳዊ ሀብትን በያዝንበት መንገድ መንፈሳዊ ሀብትን እንዴት መያዝ እንዳለብን በእርግጥ ይነግረናል:: በገንዘባችን እግዚአብሔርን ብናከብር፣ የታላላቅ መንፈሳዊ ኀላፊነቶችና ንብረቶች ዐደራ ሊሰጠን ይችላል:: እግዚአብሔር በገንዘብ ቦርሳችን ላይ ቁጥጥር ከሌለው፣ የእኛ በሆነው በማንኛውም ነገራችን ላይ ሙሉ ቁጥጥር ያለው መሆኑ ያጠራጥራል::

## በሀብት ላይ የተሰጡ የሽግግር ትምህርቶች:-

**§ 117ለ**
**የአልዓዛርና**
**የሀብታሙ ሰውዬ**
**ታሪክ**
**ሉቃ 16÷14-31**

እነዚህ «የሽግግር ትምህርቶች» ከዚህ ላይ ያለቦታቸው በዘፈቀደ አንድ ላይ የተከማቹ ሊመስሉ ይችላሉ:: ያም ሆነ ይህ እነዚህ የሚገኙት ማቴዎስ በልዩ ልዩ ዐውዶች

ባቀረባቸው ትረካዎች ውስጥ ነው:: እዚህ ምንባብ ውስጥ ግን ሁለት ዋና ዋና ተግባሮች አሏቸው:: በመጀመሪያ በሀብት ላይ በቀረቡት ሁለት ምሳሌዎች መሸጋገሪያ ድልድዮች ናቸው፤ የመጀመሪያው ምሳሌ ያለመው ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ወደ ፈሪሳውያን ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ፈሪሳውያን ለገንዘብ ላላቸው ፍቅር አራት ተግባራዊ ውጤቶችን በዕጥርታ መልክ ያቀርባሉ:- (1) እግዚአብሔር ለሚጠላቸው ነገሮች ዋጋ ይሰጣሉ (ቁ 15):: (2) የእግዚአብሔን መንግሥት በኃይል ነጥቀው ለመውሰድ ጥረት ያደርጋሉ (ቁ 16):: (3) የእግዚአብሔር ቃል በተለይ ከገንዘብ ፍላጎታቸው ጋር የሚጣረስ ሆኖ ሲያገኙት ወደ ጐን ይተዉታል (ቁ 17):: (4) ሚስቶቻቸውን ይፈታሉ::

14ገንዘብ የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ
ሰምተው በኢየሱስ አፌዙበት:: 15እርሱም እንዲህ
አላቸው፤ «እናንተ በሰዎች ፊት ራሳችሁን የምታጸድቁ
ናችሁ፤ እግዚአብሔር ግን ልባችሁን ያውቃል፤ በሰዎች
ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት የረከሰ ነውና::
16«ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ድረስ ሲነገሩ ኖረዋል፤ ከዚያ በኋላ ግን
የእግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች ተሰብኮአል፤ ሰውም ሁሉ ወደዚያ ለመግባት
ይጋፋል:: 17ነገር ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ቢያልፍ
ይቀላል::
18«ሚስቱን ፈቶ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፤ ከባሏ
የተፋታችውንም ሴት የሚያገባ ያመነዝራል::»

ሉቃ 16፥14-18

ፈሪሳውያን ገንዘብን የሚወዱ በመሆናቸው በኢየሱስ ትምህርት ላይ አፌዙ:: የግሪኩ ቃል አፍንጫን የመንፋት ወይም በትምህርቱ ላይ የማንኰራፋት ፍከሬ (ትርጓሜ) አለው:: የዛሬ ሰዎችም ከእነዚያ የተለዩ አይደሉም:: ሀብታችን ዐይነተኛ ቁም ነገር ወደ አለው ነገር ስንዝር



ያህል እንኳን አላራመደንም:: እንዲያውም ጊዜያዊ ነገሮች በእኛና በእግዚአብሔር መካል አጥር ይፈጥራሉ::

[ቁ 16 =ማቴ 11፥12-13፣ የ57 ማብራሪያን ይመልከቱ]

የቁጥር 16 ሦስት ዋና ዋና ትርጓሜዎች አሉ:: ይህ በመጀመሪያ ኢየሱስን ለሚከተሉት መገሳ ሊሆን ይችላል::[36] Hendricken የተባለ ሰው እንዲህ ይላል፤

> ነገር ግን አስፈላጊ የሆነው ጉዳይ ሰዎች በብርቱ ኀይል ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመጣደፍ ላይ ነው፤ ደግና ሰዎች ከመጥምቁ ዮሐንስ ጊዜ ጀምሮ በማድረግ ላይ ያሉትም ይህንኑ ነው:: ወደ መንግሥቱ መግባት፣ እውነተኛ እራስ ክዳት፣ ቀንነት ያለበት ጥረት፣ የማይደክም ጉልበት እና በብርቱ መሥራትን ይጠይቃል::[37]

ይሁን እንጂ የኢየሱስ የመጀመሪያ አድማጮቹ (ተደራስያን) ተከታዮቹ ሳይሆኑ ፈሪሳውያን ናቸው (ቁ 14):: በተጨማሪም «ይሻማል» (ቢያዜታይ - biazetai) የሚለው ቃል የሚመለከተው ኀይልን ብቻ ሳይሆን ዐመፅንና ተቃውሞን ነው:: ይህ ደግሞ ማቴዎስ 11፥2 ውስጥ ይበልጥ ጉልሕ ነው::

Second J. Cortes (P. F. Godet 1889 መተርጐምን ተከትሎ) ቁ 16 የሚናገረው እንደሚከተለው ያለውን ነው:- «ሕግና ነቢያት እስከ [መጥምቁ] ዮሐንስ ድረስ ይሠሩ ነበር፤ የእግዚአብሔር መንግሥት

---

36 F.W. Danker, "Lk 16:16 - An Opposition Logion," *JBL* 77 (1958): 231-243 መሠረት፣ ይህ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች የወል (የጋራ) የሆነ አተያይ ነው::

37 W. Hendricksen, *The Gospel of Luke* (New Testament Commentary; Grand Rapids: Baker, 1978), p. 774.

የምሥራች [በኢየሱስ] እየታወጀ ስለሆነ እያንዳንዱ ወደ እርሱ ይገባ ዘንድ (ወደ *መንግሥት*) በፍጥነት እየተገፋፋ ነው::[38]» ይህም «ሁሉ» የሚለውን ቃል ለማብራራት ጥቅም አለው:: እንዲያውም ፈሪሳውያን «ሁሉ» ኢየሱስን አልተቃወሙትም፤ ወይም «ሁሉ»ም የኢየሱስ ተከታዮች በጽናት አልተከተሉትም:: ነገር ግን «ሁሉ»ም ሰዎች ወደ መንግሥቱ እንዲገቡ በብርቱ ይደፋፈራሉ::» በተጨማሪም *ቢያዜታይ* - *biazetzi* የሚለው ቃል ትርጉም «በብርቱ ማደፋፈር» ሊሆን ይችላል:: በሰብዓ ሊቃውንት ትርጉም ጥቅም ላይ የዋለውም በዚሁ መንገድ ነው:: በአዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ ከፓራቢባዞማይ - Parabibazomai ጋር ተመሳሳይ ሲሆን «በብርቱ ማደፋፈር» ማለት ነው (ከሉቃ 24÷29 እና ከሐሥ 16÷15 ጋር ያነጻጽሩ):: ይህ ትርጓሜ እዚህ ላይ የሚቻል ቢሆንም እንኳ («በብርቱ ማደፋፈር» የሚለው *የባይዜታይ* - *biazetai* ቀዳሚ ትርጉም ባይሆንም እንኳ)፣ ከማቴዎስ 11÷12 ጋር አይገጣጠምም:: ሁለቱ የተቀራረበ ተመሳሳይነት ስላላቸው፣ ለሁለቱም የሚስማማ ትርጓሜ መፈለጉ እጅግ የተሻለ ይመስላል::

ማቴዎስ 11÷12 ውስጥ እንደተመለከተው ይህ ለኢየሱስም ሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ድጋፍ አይደለም:: ለፈሪሳውያንም ስድብ ነው:: የእግዚአብሔር መንግሥት እስከ መጥምቁ ዮሐንስ ድረስ በነቢያት በኩል በተስፋነት ተሰጥቶ ነበር:: አሁን ግን ከዚህ አለ:: ፈሪሳውያን ይህን ምን አደረጉት? በአጠቃላይ በኀይል ተቃወሙት::

[ቊ 17 = ማቴ 5÷18 የቊ 54 መ ማብራሪያን ይመልከቱ]

ፈሪሳውያን በነቢያት የታወጀውን መንግሥት በመቃወማቸው ኢየሱስ ስሕተታቸውን በጉልሕ አሳይቷቸዋል:: አሁን ደግሞ ኢየሱስ አረጋገጠው:: ፈሪሳውያን የአሁኑን የእግዚአብሔር ሥራ የተቃወሙበት ምክንያት (ቊ 16)፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን

[38] J. B. Cortes, "On the Meaning of Luke 16:16," *JBL* 106/2 (1987): 247-259.



የእግዚአብሔር መገለጥ ችላ በማለት ነው (ቊ 17):: ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ገና ከእንግዲህ ለመጻፍ እንደማይችሉ ሁሉ፣ የመንግሥቱን እድገት ለመግታት አይችሉም:: የእግዚአብሔር ዐዋጆች ለዘላለም ይጸናሉ:: ኢየሱስን የሚቃወሙ ሁሉ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ይቃወማሉ:: አንዳቸው ይወድቃሉ፤ ማንኛቸው እንደ ሆኑ ለመገመት ትችላላችሁ?

[ቊ 18 = ማቴ 19÷9 እና ማር 10÷11፤ የቊ 122 ማብራሪያንና ማቴ 5÷32 እና 54ሠ ይመልከቱ]

ፈሪሳውያን ቅዱሳት መጻሕፍትን ችላ ማለታቸውን ይክዳሉ:: ለዚህ ነው ኢየሱስ ይህን እንዴት እንደሚፈጽሙት ለማስገንዘብ ከብዙዎቹ ማስረጃዎች አንዱን ያቀረበው:: የፍችን ጉዳይ እንመልከት:: መጽሐፍ ቅዱስ «'ፍችን እጠላለሁ' ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር» ይላል (ሚል 2÷16):: ፈሪሳውያን ግን ሕጉን አጣመው በመተርጐም የራሳቸውን መንገድ አመቻቹ:: ይህም ሴቶችን ለማጕሳቈልና የገንዘብ ትርፍ ለማግኘት «አስቻላቸው::» የፍች መዘዝ ከዛሬም የተለየ አይደለም:- የወንዶች ነጻነትና ንብረት እያደገ ሲሄድ የሴቶች እየቀነሰ ይሄዳል:: እግዚአብሔር አሁንም ይህን አይወደውም::

ወደያዝነው ነገር እንመለስ:: ኢየሱስ ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት ገንዘብን ስለ መጠቀም ይህን ምሳሌ ለደቀ መዛርቱ ነገራቸው (ሉቃ 16÷1-13):: ከዚያም ስለ ልዩ ልዩ «የገንዘብ ጉዳይ» ለመናገር ሐሳቡን ወደ ፈሪሳውያን አዞረ (ቊ 14):: ይህም በዚህ ተከታታይ ታሪክ ውስጥ የመጨረሻ ምሳሌያችንን እውን ያደርገዋል:: አንድ ሰው ወደ ሲኦል ለመግባት በገንዘብ እንዴት እንደሚጠቀም ይህ ምንባብ ይገልጻል::

## የአልዓዛርና የሀብታሙ ሰውዬ ታሪክ:-

ይህ ታሪክ ምሳሌ ከሆነ ያልተለመደ ምሳሌ ነው:: ለምሳሌ እንደ ሌሎቹ ምሳሌዎች መግቢያ የለውም:: ከሌሎቹ ምሳሌዎች በተለየ መልኩም አንዱን ገጸ ባሕርይ በስም ይጠቅሳል::

ይህም ገጸ ባሕርይ የአልዓዛር (ትርጉሙ እግዚአብሔር ይረዳል ነው) ነው:: እንዲህ ያለው ትእምርታዊ ስም በዚህ ምሳሌ ተገቢ ይሆናል::[39] ይሁን እንጂ አልዓዛርን ከሞት ወደማስነሣቱ የቀረበ ቢሆንም ልዩ ታሪክ ይመስላል (ዮሐ 11÷1-44 እና 118):: በመሆኑም አንዳንዶች ይህ ታሪክ አልዓዛር በመቃብር ያሳለፈው ተመክሮ ገለጻ ነው በማለት ይተረጉሙታል:: የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 11 አልዓዛር ግን የተሳካ ኑሮ የነበረው እንጂ፣ እንደዚህኛው መናጢ ድኻ አልነበረም:: በተጨማሪም ይህ ታሪክ የምሳሌነት ባሕርይ ስላለው ይህንኑ አካሄድ ይከተላል:: ስለዚህ በምሳሌነቱ ማየቱ ተገቢ ነው::[40] የምሳሌ ዝርዝር ጉዳይ ሁሉ ይተረጎም ዘንድ ስለማይጠበቅ፣ ከእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ለይተን እንዳናሳይና ሰዎች ሲሞቱ ወዲያውኑ ይህን ይመስላሉ እንዳንል መጠንቀቅ ይኖርብናል:: ይህ ምሳሌ ስለ ሙታን ሳይሆን ስለ ሕያዋን ነው:: ኢየሱስ ከነቢያት ይልቅ ገንዘብን ለሚወዱ ፈሪሳውያን ነበር የሚናገረው:: ይህ ምሳሌ የታቀደው የአሁኑ የሀብት

[39] R. Bauckham, "The Rich Man and Lazarus: The Parable and the Parallels," *NTS* 37 (1991): 225-246 በሚለው ጽሑፉ ውስጥ ሰዎችን ከሙታን በማስነሣት ታሪክ፣ ከሞት የተነሡት ግለሰቦች ስም ብዙ ጊዜ የተወሳ መሆኑን ያመለክታል:: ከዚህም በላይ የሀብታሙና የድኻው ሰውዬ ገለጻ ከሞቱ በኋላ ስለሚሆን እዚህ ላይ የአልዓዛርን ስም መጥቀሱ አስፈላጊ ሆኖአል::

[40] ይህ ምሳሌ ስለ መሆኑ ሙሉውን ሐተታ ለመገንዘብ፣ የCharles Ray, "The Rich Man and Lazarus (Lk 16:19-31)," *TheolEd* 56 (Fall 1997): 77-84 ይመልከቱ::



አጠቃቀማቸው ዘላለማዊ ውጤት ምን እንደሚመስል ሊያሳያቸው ነው:: በመሆኑም ይህ ምሳሌ ቀደም ያለው ምሳሌ ሌላ ገጽታ ነው:: ዐይነተኛ ጭብጡም «ተገላቢጦሽ» ነው:: በመጨረሻ እግዚአብሔር ለሁሉም እንደየሥራው ያደለድላል::[41]

**ሉቃ 16÷19-24**

19ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ሐምራዊና
ቀጭን በፍታ የለበሰ በየቀኑም በተድላ ደስታ የሚኖር
አንድ ሀብታም ሰው ነበረ:: 20በአንጻሩም፣ መላ ሰውነቱ
በቍስል የተወረረ አንድ አልዓዛር የሚባል ድኻ በዚህ
ሀብታም ሰው ደጃፍ ይተኛ ነበር፤ 21ከሀብታሙ ሰው ማእድ የወደቀውን ፍርፋሪ
እንኳ ሊመገብ ይመኝ ነበር፤ ውሾችም ሳይቀሩ መጥተው ቍስሉን ይልሱ ነበር::
22«ድኻውም ሞተ፤ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት::
ሀብታሙ ሰው ደግሞ ሞቶ ተቀበረ:: 23በሲኦልም እየተሠቃየ ሳለ ቀና ብሎ ከሩቅ
አብርሃምን አየ፤ አልዓዛርንም በእቅፉ ይዞት አየ:: 24እርሱም፣ 'አብርሃም አባት
ሆይ፤ ራራልኝ፤ በዚህ ነበልባል እየተሠቃየሁ ስለ ሆነ፣ አልዓዛር የጣቱን ጫፍ ውሃ
ነክሮ ምላሴን እንዲያቀዘቅዝልኝ እባክህ ላክልኝ' እያለ ጮኸ::»

ይህ ሀብታም የላቀን ነገር እጁ ውስጥ ያስገባና ይህንንም ለታይታ ለማዋል ወደ ኋላ የሚል ዐይነት ሰው አልነበረም:: ሐምራዊ ልብሱ በወቅቱ እጅግ ብርቅ ሲሆን የምግብ ገበታውም በልዩ ልዩ

[41] ኢየሱስ ያቀረበው ታሪክ በዐይነቱ ልዩ አይደለም:: በጥንት ጽሑፎች ውስጥ በርካታ ጉድኝቶች አሉት:- The Egyptian story of Osiris (cf R. Baucham, "The Rich Man and Lazarus," *NTS* 37 [1991]: 225-246); The Cynic story of Micyllus (cf R.F. Hock, "Lazarus and Micyllus: Greco - Roman Backgrounds to Luke 16:19-31," *JBL* 106/3 [1987]: 447-463); and the Jewish Apocrypha in 1 Enoch 22 (cf L. Kreitzer, "Lk 16:19-31 and 1 Enoch 22," *ExpT* 103 [1992]: 139-142). ይሁን እንጂ እነዚህ ታሪኮች ተመሳሳይ ዋና ሐሳብ ወይም መሠረታዊ ሜራ (መዋቅር) ስላላቸው አንዳቸው በሌላው የተደገፉ ናቸው ብሎ ለመገመት በቂ ምክንያት የለም:: በተለይ ኢየሱስ ይህን ዋና ሐሳብ ብቻውን ለማዋቀር ፍጹም የሆነ ችሎታ ነበረው:: ይህ የሚያመለክተው የኢየሱስ አድማጮች መሠረታዊውን የታሪክ መስመር ለመገንዘብ መቻላቸውን ነው::

ማራኪ ምግብ የተሞላ ሲሆን በአንጻሩ አልዓዛር ምስኪን ለማኝ ነበር:: ሽባ በመሆኑ ወዳጆቹ ምጽዋት ወደሚያገኝበት ቦታ በየቀኑ ተሸክመው ያመጡት ነበር:: በአማረ ልብስ በማጌጥ ፈንታ በሳንባ በሽታ ይሠቃያል:: በአይሁድ ዘንድ ምንጊዜም አስጸያፊ የነበሩት ውሾች ወደ እርሱ እየመጡ ቊስሉን ይልሱ ነበር:: ይህ ፍጹም ውርደት ነው::

ሳታስቡት እንደማትቀሩ ሁሉ በአልዓዛርና በሀብታሙ ሰውዬ የቀብር ሥነ ሥርዐት እንኳ ትልቅ ልዩነት ነበር::[42] የሀብታሙ ሬሳ ሽቶ ተቀብቶና በሚገባ ተከፍኖ ውድ በሆነ የመቃብር ቦታ ተቀምጧል:: የድኻው ሬሳ በንቀት ወደ ከተማው የቆሻሻ ማቃጠያ (ገሀነም) ሳይወረወር አልቀረም:: ከዚያ በኋላ «በሌላው ስፍራ» (በላይኛው ቤት) ላይ ምን እንደሚደረግ በውልብታ እንገነዘባለን::

የአዲሱ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም «ሲኦል» ቃል በቃል ሲተረጎም «ገሀነመ እሳት» ማለት ነው:: ግሪካውያን ደጋግ ሰዎች በልባዊነት የሚጽናኑበት፣ ክፉ ሰዎች ደግሞ የሚሠቃዩበት ስፍራ ነው ብለው ያምናሉ:: ሉቃስ የሚሰጠን ሥዕል ይህን ይመስላል:: የብሉይ ኪዳን የ«ሲኦል» ሥዕልም ይኸው ነው:: ስለዚህ በሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ውስጥ ሲኦል የሚለው ቃል በዕብራይስጡ *ገሀነመ እሳት* መባሉ ትክክል ነው::

*ገሀነመ* እሳት የክፉዎች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ አይደለም:: የመጨረሻው ዕጣ ፈንታ ገና አገልግሎት ላይ ያልዋለ የእሳት ባሕር ይሆናል (ራእ 20÷11-15)ፑ:: ገሀነመ እሳት ከሥጋ አካል ለተለዩት ነፍሶች ጊዜያዊ ማቆያ እስር ቤት ሲሆን፣ ከሚመጣው ሽልማት ወይም ቅጣት በፊት እውን የሚሆን ክሥተት ነው:: በመጨረሻው ፍርድ

[42] የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ሀብታሞችን ገጸ ባሕርይ ቱጃር ወይም ባለ ጸጋ ብላቸዋለች፤ ይህን ከሀብታሙ ሰው የላቲን ቋንቋ ምትክ ቃል ነው (ከ K. Groble, "... 'Whose Name was Neves,'" *NTS* 10 [1963-64]: 373-382) ጋር ያነጻጽሩ::



ገሀነመ እሳት በውስጡ ያትን ሙታኑን እንዲሰጥ ይገደዳል (ራእ 20÷12:13):: ከዚያም ገሀነመ እሳት ሙሽራ ከሆነው ሞት ጋር ለዘላለም ይወድማል (ራእ 20÷14፤ 1ቆሮ 15÷26):: በመጨረሻ (የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የእሳት ባሕር) በሲኦል ካሉት ተመክሮ የሚብስ ይመስላል:: በሌላ አባባል በሥቃይ ላይ የሚገኙት ሥቃያቸው ዕጥፍ ድርብ ሆኖ ያገኙታል:: በመጽናናት ላይ የሚገኙት ደግሞ በቋንቋ ሊገለጽ የማይችል ሐሤት ያገኛሉ::

**ሉቃ 16÷25-31**

[25]«አብርሃም ግን እንዲህ አለው፤ ልጄ ሆይ፤
አንተ በምድራዊ ሕይወትህ ዘመን መልካም ነገሮችን
እንደ ተቀበልህ፣ አልዓዛርም ደግሞ ክፉ ነገሮችን እንደ
ተቀበለ አስታውስ፤ አሁን ግን እርሱ እዚህ ሲጽናና፣
አንተ
በሥቃይ ላይ ትገኛለህ:: [26]ከሁሉም በላይ ከዚህ ወደ እናንተ ለማለፍ የሚፈልጉ
እንዳይችሉ፣ እዚያ ያሉትም ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ፣ በእኛና በእናንተ
መካከል ትልቅ ገደል ተደርጎአል::»

[27]«እርሱም እንዲህ አለ፤ 'አባት ሆይ፤ እንግዲያውስ አልዓዛርን ወደ አባቴ
ቤት እንድትሰደው እለምንሃሁ፤ [28]አምስት ወንድሞች አሉኝ፣ እነርሱም ወደዚህ
የሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ያስጠንቅቃቸው::'

[29]«አብርሃም ግን፣ 'ሙሴና ነቢያት አሏቸው፤ እነርሱን ይስሙ' አለው::

[30]እርሱም፣ 'አብርሃም አባት ሆይ፣ እንዲህ አይደለም፤ አንድ ሰው ከሙታን
ተነሥቶ ቢሄድላቸው ንስሓ ይገባሉ' አለ::

[31]አብርሃምም፣ 'ሙሴንና ነቢያትን የማይሰሙ ከሆነ፣ አንድ ሰው ከሙታን
ቢነሣ እንኳ አያምኑም' አለው::»

እዚህ ላይ ያለው ጉዳይ ከመቃብር ባሻገር ያለው አኩልነት አይደለም:: እንዲያውም አንድ ድኻ ሰው ራሱን ሥቃይ ውስጥ ያገኝ

ይሆናል፤ አንድ ሀብታም ደግሞ ራሱን በምቾት ውስጥ ሊያገኝ ይችላል። ሀብታሙ ሰውየ የተሠቃየው ለድሾች ማድረግ የነበረበትን የገንዘብ ድጋፍ ችላ በማለቱ ነው። ሀብታሙ በሥቃይ ላይ የሚገኘው በሀብት አያያዙ ላይ ጻድቅ ባለመሆኑ ነበር።

አሁን በማይላቀቅበት ሥቃይ ውስጥ ባለበት ጊዜ ቀደም ሲል ርዳታ ካላደረገለት አልዓዛር ርዳታ በማያገኝበት ስፍራ በመሰቃየት ላይ ነው። አሁን ሌላው ቢቀር ወንድሞቹን ከዚህ ዐይነቱ ዘግናኝ ዕጣ ፈንታ ሊያድናቸው ይፈልጋል። ሆኖም አልዓዛር እርሱን ለማዳን እንዳልቻ ሁሉ ወንድሞቹንም ሊያድንለት አይችልም።

ቦክ የተባለ የሥነ መለኮት ሰው ይህን ልዩ ማስተዋል እንደሚከተለው ያቀርበዋል፡- «ያልታደሉ ሰዎች የተፈረደባቸው፣ የማይረቡ ወይም ሁኔታው ሲያጋጥም መገልገያ ዕቃዎች አድርጋችሁ እንድታዩ ያደርጉ ዘንድ ለሀብትና በረከታችሁ አትፍቀዱላቸው። የሌሎችን ፍላጎት ከማየትና አይታችሁም ርዳታ ከማድረግ ትቆጠቡ ዘንድ፣ ሀብት ዐይኖቻችሁን እንዲሸፍናቸው አትፍቀዱለት። የአንድን ድኻ ስም ብቻ በማወቅ ፍላጎቱን ችላ አትበሉ።[43]

ተአምራት የወንጌል ሥርጭት መሣሪያዎች ናቸው ብለን ለማሰብ እንወዳለን፤ ነገር ግን አይደሉም። የኢየሱስ አስደናቂ ተአምራት ሁሉንም ሰው አላሳመኑም። ሰዎች ነቢያትን ለመስማት ካልፈለጉ፣ ትንሣኤን በመሰለ ታላቅ ተአምር እንኳን ልባቸው ሊነካ አይችልም።

ከዚህ ላይ ከመቃብር ባሻገር ያለን ውልብታ እናያለን። የዚህ ጽሑፍ ዋና ትኩረት እዚህ እና አሁን ላይ ነው። ይህ ምሳሌ እውነቱን የሚናገር ከሆነ በወንጌል ሥርጭት ላይ በላቀ ሁኔታ መሥራት ይኖርብናል። የኢየሱስን የምሥራች በማወጅና የሲኦልን አሥጊ

[43] D. Bock, "The Parable of the Rich Man and Lazarus and the Ethics of Jesus," *SwJT* 40/1 (1997): 67-72.



እውነትነት በማስጠንቀቅ ከመቃብር ወዲህ ባለው ስፍራ ከነቢያት ጐን እንቁም። ከዚህ ቀጥታ በሆነ መልክ ደግሞ የአሁኑ የገንዘብ አያያዛችን ዘላለማዊ ሳንካ (ውጤት) ያለው መሆኑን ይህ ምንባብ ያስጠነቅቀናል። ድኾችን ችላ ማለት የከፋ ውጤት ይኖረዋል።[44] ኤች ክቫልቤን የተባለ ጸሐፊ እንዲህ ይላል፤ «የሀብትና የምቾት ሕይወት ለእግዚአብሔር ቃል ጆሮህን እንድትዘጋ፣ ለወዳጅህ ፍላጎትም ዐይንህን እንድትከድን ያደርጋል።»[45]

**§ 117ሐ**
**በደቀ መዝሙርነት ላይ ልዩ ልዩ ትምህርቶች**
**ሉቃ 17፥1-10**

ከዚህ ላይ ኢየሱስ አንድ ደቀ መዝሙር ስለማይኖሩት መብቶች ይናገራል። ሌላውን ሰው ወደ ኀጢአት የሚመራ ከሆነ፣ «የራሳችንን ሥራ ለመሥራት» እንኳን መብት የለንም (ቍ. 1-2)። አንድ ሰው ኀጢአት ሲሠራ ብናየው፣ ዝም የማለት መብት የለንም (ቍ. 3)። ፈራጆች ወይም ቂመኞች የመሆን መብት የለንም (ቍ. 4)። ለጌታ ስንሠራ ግብዞች ወይም በራሳችን የምንተማመን ሰዎች የመሆን መብት የለንም (ቍ. 7-10)።

ሉቃስ እነዚህን ልዩ ልዩ ትምህርቶች እዚህ ላይ ያስፈራቸው፣ የተለመደውን የድርጊት ቅደም ተከተል ሳያሳይ ነው።[46] በተወሰነው ቀን

[44] የዚህ ምሳሌ መልእክት አልበርት ሽቬትዘር ልብ ደረሰ። ይህ ሰው የታወቀ የኮንሰርት ኦርጋን ተጫዋችና በስትራበርግ ዩኒቨርስቲ የአዲስ ኪዳን ዝነኛ ፕሮፌሰር ነበር። እ.ኤ.አ. በ1913 ዓ.ም. በኢኳቶሪያል አፍሪካ ሚስዮናዊ ለመሆን ይህን ሁሉ ተወ። በራሱ አባባልም፣ «የሀብታሙ ሰውና የአልዓዛር ምሳሌ በቀጥታ ለእኛ የተነገረ ይመስላል! እኛ ሀብታሞቹ ነን ... ከዚህም የተነሣ በራችን ላይ በቆመው ድኻ ሰው ላይ በደል እንፈጽማለን» (*On the Edge of the Primeval Forest* [1992])።

[45] H. Kvalbein, "Jesus and the Poor: Two Texts and a Tentative Conclusion," *Themelios* 12 (1986-87): 86.

[46] «'ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፤' የሚሉት የመግቢያ ቃሎች የድርጊትን ቅደም ተከተል ለመጠበቅ ጥረት እንዳልተደረገባቸው፣ በሌሎች

የቀረበውን ትምህርት ሊወክሉ ይችላሉ:: የሚመስለው ግን ኢየሱስ ዘግየት ብሎ በይሁዳ ማለትም በዮርዳኖስ ማዶ ያደረገውን ውይይት የሚያንጸባርቁ የዋና ዋና ሐሳቦች ስብስብ ይመስላሉ:: አንድ ዐይነት ከሆኑ አባባሎች ጋር ማቴዎስ 18 ውስጥም ተመሳሳይ ስብስብ ይገኛል (ከቍ 91-92 ጋር ያነጻጽሩ)::

[1]ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፤
«ሰዎችን የሚያሰናክል መምጣቱ አይቀርም፤ ነገር ግን
ለመሰናከሉ መምጣት ምክንያት ለሚሆን ለዚያ ሰው ሉቃ 17÷1-6
ወዮለት:: [2]ይህ ሰው ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን
ከሚያሰናክል፣ የወፍጮ ድንጋይ በዐንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር
ቢጣል ይሻለው ነበር:: ስለዚህ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ::
«ወንድምህ ቢበድል ገሥጸው፤ ቢጸጸት ይቅር በለው:: [4]በቀን ሰባት ጊዜ
ቢበድልህና ሰባት ጊዜ፣ 'ተጸጽቻለሁ' እያለ ወደ አንተ ቢመለስ ይቅር በለው::»
[5]ሐዋርያትም ጌታን፣ «እምነታችንን ጨምርልን» አሉት::
[6]ጌታም፣ «የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህን ሾላ፣
ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ተተከል ብትሉት ይታዘዝላችኋል» አላቸው::

[ቍ 1-2 = ማቴ 18÷6-7፤ የቍ 91 ማብራሪያን ይመልከቱ ]

«ሰዎችን የሚያሰናክል» የሚለው ሐረግ አንድ የግሪክ ቃል ነው [ስካንዳሎን - Skandalon] «የማሰናከያ ድንጋይ» ማለት ነው:: ሰዎችን ያደናቀፈ መሰናክል ነበር:: በዳር መንገድ ዳር ካለ የጉብታ ስንጥቅ ጋር ልናዛምደው እንችላለን:: አንዳንድ ጊዜ ሆን ብለው፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሳይታወቅ መምጣታቸው አይቀርም:: በኢአማንያን በኩል መጥተው መገኘታቸው አያስገርምም፤ ይህ ሊሆን ይችላል ብላችሁ

ቦታዎች ላይ እንደሚገኙት ያሉ ናቸው በማለት ያስታውሳል (e.g. 12:22, 54; 13:6; 16:1)» (p. 993)::



የምትጠብቁት ጉዳይ ነው:: የሚመጡት ሳይታሰብ ነውና በአማኞች በኩል ሲመጡ ግን ይበልጥ ጎጂዎች ናቸው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ጳውሎስ ለጣዖት የተሠዋን ሥጋ ስለ መብላት አስመልክቶ ሮሜ ምዕራፍ 14ና በ1ቆሮንቶስ 8-10 ውስጥ በሰፊው ይናገራል:: የሌሎች የመሰናክል ድንጋይ ላለመሆን ክርስቲያኖች የራሳቸውን ባሕርይ ይቈጣጠሩ ዘንድ ግድ ነው::

በተለይም ሕፃናትን ወደ ኀጢአት እንዲገቡ ማድረግ ከባድ መዘዝ አለው:: ኢየሱስ ስለ «መንፈሳዊ ሕፃናት» ሳይሆን (ከማቴ 18÷6-7 ጋር ያነጻጽሩ) ስለ ልጆች በቀጥታ ሳይናገር አልቀረም:: ልጆች የእኛን ነገረ መለኮታዊ እውነታ አይረዱ ይሆናል፤ አካሄዳችንን (ጠባያችንን) ግን በቅርብ ይከታተላሉ:: ዋናው ጉዳይ ቍጥር ሦስት ውስጥ ተቀምጦአል:- «ለራሳችሁ ተጠንቀቁ!» ምክንያቱም ልጆች ባጠገብ ያሉ መሆናቸውን ርግጠኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ::

ስለምናደርገው ነገር ሁሉ የግል ጉዳያችን ነው የማለት መብት የለንም:: ወይም አንድ ወንድም ኀጢአት ቢሠራ፣ የራሱ ጉዳይ ነው፤ እኛን አያገባንም የማለት መብት የለንም:: ወደዚያ ወንድም በፍቅር፣ በንጽሕና፣ በጨዋነት ሄደን እንገሥጸው ዘንድ ግዴታ አለብን:: ማቴዎስ 18÷15-20 አንድን ወንድም ስንገሥጽ የምንከተላቸውን ሦስት ደረጃዎች ይሰጣል (የቍ 92 ማብራሪያን ይመልከቱ):: ደረጃዎቹ ለመከተል አስቸጋሪዎች አይደሉም፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ተግባር ላይ አይውሉም:: ለምን? በመጀመሪያ ደረጃ የማንንም ስሜት ለመጕዳት አንፈልግም:: አብያተ ክርስቲያናትን የከፋፈለው ይህ ጉዳይ መሆኑን ታውቃለህ፤ ከዚህም በላይ ሰዎች በሥራችን ጣልቃ እንዲገቡ አንፈልግም:: ይህን ዐይነቱን በጎ ስሜት ለእኛም ያሳያሉ ብለን ተስፋ በማድረግ፣ ችግሩም በሆነ መንገድ ይቃለላል ብለን በማመን፣ እንተዋቸዋለን:: ውጤቱ ግን ኀጢአትን በጕያዋ የሸሸገች ቤተ ክርስቲያን ማፍራት ይሆናል:: በጉባኤያችን ላይ፣ አምልኮአችንን፣

ኅብረታችንንና የወንጌል ሥርጭታችንን የሚጋርድ ጥቁር መንፈሳዊ ደመና ይሆናል::

[ቍ 3-4 = ማቴ 18÷21-22፣ ቍ 92 ማራሪያን ይመልከቱ]

ከቍ 3-4 ውስጥ ሁለት ነገሮች መታወስ የሚገባቸው ናቸው:: በመጀመሪያ አንድ ሰው በአንተ ላይ በደል እንደሚያደርስ ኢየሱስ እጅግ ብዙ ጊዜ ደጋግሞ ተናግሮአል:: ይህ ግን እንዲሁ ሊሆን አይችልም:: አንድ ሰው በዚህን ያህል መልኩ በደል ከሚደርስበት በፊት ከተማን ለቆ ይሄዳል:: ነገሩን የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ኢየሱስ ይህንኑ ጉዳይ በየቀኑ እንዲፈጽሙት ማድረጉ ነው! ዋናው ጉዳይ በመሠረቱ፣ «አንድ ሰው የቱንም ያህል ይበድልህ» ይቅር ማለት ይኖርብሃል:: ርግጥ የኢየሱስ አነጋገር ሚያስደንቅ ነው:: ሁለተኛ ኢየሱስ «ንስሐ ቢገቡ» አላለም፤ ያለው «ተጸጽቻለሁ» ቢሉ ነው:: አንድ ሰው ከልቡ ንስሐ ይግባ ወይም አይግባ እኛ ፈራጆች መሆን የለብንም:: ልባቸውን ወይም አነሣሽ ምክንያታቸውን ለማየት አንችልም፤ የዚያን ሰው ንስሐ መቀበል አለብን::

የኢየሱስን ቃል በጥሬ ትርጉሙ ብናየውና በተግባር ብናውለው ከባድ ይሆናል:: ደቀ መዛሙርቱ፣ «እምነት ጨምርልን» (ቃል በቃል «እምነት ስጠን» ማለት ነው) በማለት መጮኻቸው አያስደንቅም:: ወዲያውኑ፣ በቅጽበትና ሳይታሰብ እውን የሚሆን እምነት ፈለጉ:: በአጠቃላይ ሲታይ ግን እምነት የሚያድገው እነርሱ በጠየቁት መንገድ አይደለም:: ብዙ ጊዜ እውን የሚሆነው በጽኑና አስጨናቂ ሁኔታ፣ በአሰልቺ የዕለት ተዕለት ህልውናችንና ሳይስተካከል ይፋ በሚወጣው ኢፍጹምነታችን ነው::

የችግራችን አንዱ ፈርጅ ትልቅ እምነት መፈለጋችን ነው፤ እውን ይሆንልን ዘንድ ኢየሱስ የሚፈልገው ግን እያደገ የሚጎዝን እምነት ነው:: የግሪኩ ጽሑፍ ቍ 6 ላይ «ትንሽ» የሚል ቃል



የለውም:: የሚለው «እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ያለ እምነት» ነው:: በሌላ ቦታ የእግዚአብሔር መንግሥት ከሰናፍጭ ቅንጣት ጋር ተያይዞአል (ሉቃ 13÷18-21):: አንድ ነገር ሲጀምር ትንሽ ሆኖ በመጨረሻ ግን እንዴት ትልቅ እንደሚሆን አጉልቶ ያሳያል:: አጽንዖቱ ያለው ግን በትንሽነቱ ሳይሆን ለማደግ ባለው ዐቅም ላይ ነው:: እምነት እንደዚህ ነው:: እያደገ መሄዱ አይቀርም:: በተግባር ላይ ብናውለው ከመጀመሪያው መጠን ሺህ ጊዜ ያድጋል:: ዋናው ነገር የት መጀመርህ አይደለም፤ ወዴት መጓዝህ ነው::

የሚያድግ እምነት ድንገት መዘዝ ብሎ እንደሚያድግ የእንጆሪ ዛፍ ታምራት ሊሠራ ይችላል:: የእንጆሪ ዛፍ እስከ 35 ጫማ ከፍታ ድረስ ስለሚያድግ ይህ አስደናቂ ጉዳይ ነው:: ነገር ግን ኢየሱስ በሚወዛወዙ ዛፎች ወይም በተራሮች ላይ ፍላጎት የለውም (ከማቴ 17÷20፤ ከ21÷21፤ ከማር 11÷23 ጋር ያነጻጽሩ):: እጅግ ብርቱ መሰናክሎቻችን ዛፎች ሳይሆኑ፣ አለቆችና ኀይሎች ናቸው:: የአንድ ክርስቲያን እውነተኛ የእምነት ሥራ እግዚአብሔርን መታዘዝና ወንጌልን ማካፈል ነው::

ሉቃ 17÷7-10

7ደግሞም ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ «ከእናንተ
መካከል አንድ ሰው ዐራሽ ወይም በግ ጠባቂ የሆነ
አገልጋይ ቢኖረው፣ ከዕርሻ የተመለሰውን አገልጋዩን፣
'ቶሎ ወደ ማእድ ቀረብ' ይለዋልን? 8ከዚህ ይልቅ፣
'እራቴን እንድበላ አዘጋጅልኝ፣ እኔ እስክበላና እስክጠጣ
ድረስ ታጥቀህ አገልግለኝ፤ ከዚያ በኋላ አንተ ደግሞ ትበላለህ፤ ትጠጣለህ'
አይለውምን? 10ስለዚህ እናንተም የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፣ 'ከቍጥር
የማንገባ አገልጋዮች ነን፤ ልናደርገው የሚገባንን ተግባር ፈጽመናል' በሉ።»

ይህ ማብራሪያ በጣም ግልጽ ነው፤ ትንሽ አስተያየትና ማስጠንቀቂያ ብቻ ነው የሚያስፈልገው:: በእኛ ባህል እነዚህ ቃሎች አይወደዱም:: የባሪያ ሥርዐት የተለመደና በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ሕጋዊ ሆኖ ባህል ላይ ተመሥርቶ የዳበረ እንደነበር በሚረዳ አእምሮ ማሰብ ይኖርብናል::[47]

አንድን ባሪያ የራስህ ገንዘብ ስታደርግ፣ ያ ባሪያ እንዲፈጽም የተነገረውን ሁሉ ይፈጽማል ብለህ ታስባለህ:: ሥራው ተፈጽሞ ሲገኝ ባሪያ እንዲያከናውን የታዘዘውን ጉዳይ በመፈጸሙ እርሱን ማመስገን አለብኝ ብለህ አታስብም:: አንድ ባሪያ የቱንም ያህል ሥራውን ያከናውን ከግዴታው በላይ እስካላከናወነ ድረስ ለጌታው ጥቅም የሚሰጥ ሰው አይደለም:: አንድ ባሪያ ጌታው ካሰበው በላይ ሲሠራ ነው ትርፋማ ባሪያ የሚሆነው::

እንደ ባሪያዎች እኛም ማድረግ አለባችሁ ከተባልነው ይበልጥ ሠርተን ካልተገኘን (ማንኛችንም ልንፈጽም አንችልም) ለእግዚአብሔር ጠቃሚዎች አይደለንም:: ስለዚህ ሁላችንም ጥቅም የማንሰጥ አገልጋዮች ነን:: ዐይነተኛው ጉዳይም:- በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለአንድ አገልጋይ ለግብዝነትም ሆነ በራስ ለመተማመን ቦታ የለም:: «ከቍ 1-6 ባለው ሐሳብ ውስጥ ተፈላጊዎቹ ነገሮች ከባድ ይሆኑ ይሆናል:: አፈጻጸማቸው ግን እግዚአብሔርን ግዴታ ውስጥ የሚያስገቡ አይደሉም:: ይህ ደግሞ እኛ ለእርሱ ማድረግ ካለብን ጋር ሲነጻጸር ምንም ማለት አይደለም» (Nolland, p. 841)::

[47] ኤም. ኤ. ቢቪስ የተባለ ሰው ባቀረበው ጽሑፍ መሠረት የባሮች መጠን ነጻ ከነበሩት ሰዎች ጋር ሲነጻጸር፣ በመላው የሮም ግዛት 1:5 ሲሆን በሮም ከተማ ውስጥ 1:3 ነበር:: ባሮች እንደ ንብረት ይቈጠሩ ነበር፤ አንዳንድ ጊዜም ለከፋ አስተዳደርና ጭካኔ ለተሞላበት ሥቃይ ይጋለጡ ነበር (M.A. Beavis, "Ancient Slavery as an Interpretive Context for the N.T. Servant Parables with Special Reference to the Unjust Steward (Lk 16:1-8)," *JBL* 111/1 [1992]: 37-54 ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)::



**§ 118ሀ**
**የአልዓዛር**
***መታመምና ሞት***
**ዮሐ 11÷1-6**

ይህ ምንባብ የዮሐንስ ወንጌል እምብርት ነው:: ወደ ኋላ መለስ ብሎ ኢየሱስ ያደረጋቸውን ምልክቶች ያጤናል፤ ወደፊት በመመልከትም የመጨረሻውንና ታላቁን ምልክት፣ ማለት ትንሣኤን ይመለከታል:: ይህ የኢየሱስ የይፋ አገልግሎት ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት ሲሆን፣ የሕማማቱም መንገድ ነበር:: ከዚህ ቀደም ከቶ ባልታየ ሁኔታ የኢየሱስን ትሰብእትነትና መለኮታዊ ባሕርዩን እንመለከታለን::[48]

**ዮሐ 11÷1-6**

1 በማርያምና በእኅቷ በማርታ መንደር በቢታንያ
ይኖር የነበረው አልዓዛር ታሞ ነበር::
2 ይህች ወንድሟ አልዓዛር የታመመባት ማርያም፣ በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ
እግሩን በጠጕሯ ያበሰችው ነበረች:: እኅትማማቾቹም፣ «ጌታ ሆይ፤ የምትወደው
ሰው ታሞአል» ብለው መልእክት ላኩበት::
4 ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ «ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ
ይከብር ዘንድ ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት የሚያደርስ አይደለም» አለ::
5 ኢየሱስም ማርታን፣ እኅቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር:: 6 ሆኖም አልዓዛር
መታመሙን በሰማ ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ::

ከዚህ ላይ በቍጥር 1 ላይ ዮሐንስ አልዓዛርን፣ ማርያምን፣ ማርታንና ከተማቸውን ቢታንያን ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንባቢዎቹ ጋር ያስተዋውቃል:: በቍጥር 2 መሠረት ዮሐንስ አንባቢዎቹ ስለ እኅትማማቾቹና ስለ ወንድማቸው ስለ አልዓዛር ያውቃሉ ብሎ ያስባል:: ምናልባት ዮሐንስ ስለ ማርያምና ስለ ማርታ አንባቢዎቹ ተመሳሳይ ትረካዎች አንብበዋል ብሎ ሊያስብ ይችላል:: ሉቃስ *10÷38-*

[48] ዮሐ 11÷1-44 ውስጥ ስለ ቀረበው ልሂቅ መልስ አዘላዊ (Rhetorical) ትንታኔ M.W. Stibbe, "A Tomb with a View: Jn 11:1-44 in Narrative-Critical Perspective," *NTS* 40 (1994): 38-54 ይመልከቱ::

42 ውስጥ ማርያም የማድቤቱን ሥራን ለማርታ ትታ በተማሪነት ኢየሱስ እግር ሥር መቀመጧን እናነባለን:: እንደሚታወቀው ማርታ ቅሬታዋን በማሰማት ማርያም እንድታግዛት ኢየሱስ ያዛት ዘንድ ጠየቀችው:: በሚያስደንቅና ባልታሰበ መልኩ ማርያም ተነሥታ እንድታግዛት ኢየሱስ ሊነግራት አልፈቀደም፤ ምክንያቱም ማርያም፣ «የተሻለውን» መርጣለች:: በተለይ በቊጥር ሁለት ላይ የተወሳው ሁለተኛ ታሪክ ኢየሱስ ከመሰቀሉ አንድ ሳምንት በፊት ይፈጸማል:: ይህም ማርያም ብዙ ገንዘብ በፈሰሰበትና ውድ በሆነ ሙሉ የብልቃጥ ሽቶ የኢየሱስን እግር በቀባች ጊዜ ነበር (ማቴ 26÷6-13፤ ማር 14÷3-9፤ ዮሐ 12÷1-8)::

ስለዚህ ዮሐንስ ይህን ታሪክ ከመናገሩ በፊት አንባቢዎቹ ስለ እነዚህ ሴቶች በመጠኑ ያውቃሉ:: የኢየሱስ ቅርብ ወደጆች እንደ ነበሩ የታወቀ ነው:: የእምነት ሴቶችም ነበሩ:: ይህም ማርታ በተግባራዊ መልኩ ሲሆን፣ ማርያም ደግሞ በልግስናና በአምልኮአዊ መልኩ ነበር:: ስለ አልዓዛር የምናውቀው በመጠኑ ቢሆንም ሀብታምና ዝና ያለው ሰው ነበር (ከቊ 19 ጋር ያነጻጽሩ)::

አልዓዛር በጣም ታመመ:: በመጥፎ ጊዜ ይህ መሆን አልነበረበትም:: ከመጨረሻዎቹ ሁለት ሰዓቶች የኢየሩሌም የፍርድ ሸንጎ አባላት ከእርሱ ጋር የነበራቸውን ግኙነት ካቋረጡ በኋላ ኢየሱስ በይሁዳ ዳርቻ በመዘዋወር ላይ ነበር:: በሞት የሚለይበት ጊዜ የቀረው ሁለት ወር ያህል ብቻ ነው::[49] በዚህ ጊዜ የዚህ ተንኰልና ምቀኝነት

[49] ኢየሱስ ዲሰምበር 29 ዓ.ም. በዋለው የቤተ መቅደስ እድሳት በዓል ላይ ተገኝቶአል:: ሉቃ 17-19 እና ማቴ 19-20 ውስጥ በተጻፈው መሠረት ኢየሱስ ገና ዮርዳኖስ ማዶ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የሚያከናውነው አገልግሎት አለው:: ስለዚህ ይህ ሁኔታ ከቤተ መቅደስ መታደስ በኋላ አንድ ወር፣ ከኢየሱስ ሞት በፊት ደግሞ ሁለት ወር ቀደም ብሎ ተከናውኖአል ብለን እንገምታለን::



ማዕከል በሆነችውና ከኢየሩሳሌም ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ወደምትገኘው ቢታንያ ኢየሱስ እንዲመጣለት አልዓዛር ይፈልግ ነበር::

ወዳጅነታቸውን በመተማመን ማርያምና ማርታ መልእክተኛ ወደ ኢየሱስ ላኩ:: ኢየሱስ ወደ ቤታንያ እንዲመጣ አልጠየቁትም:: አልዓዛር በሞት አፋፍ ላይ መሆኑ ብቻ እንዲነገረው አደረጉ:: እኅትማማቾቹ ትሑታን ነበሩና የእኛ ቤተ ሰብ ከኢየሱስ አገልገሎት የላቀ ነው አላሉም:: ቢሆንም ኢየሱስ አጣዳፊ የሆነውን የዙር አገልገሎቱን አቋርጦ ወንድማቸውን እንደሚፈውስላቸው በእርግጥ ተስፋ አድርገው ነበር:: ርባነቢስ በሆነ ጥያቄያቸው ኢየሱስን ላለማስቸገር በማሰብ ወይም ወደ ቢታንያ ተመልሶ በመምጣት አልዓዛርን ድኖ ቢያገኘውስ በሚል ፍርሃት የወንድማቸው ሕመም ከአሥጊ ሁኔታ ላይ እስከሚደርስ ድረስ ታገሱ:: ኢየሱስ መጥቶ ጣልቃ ካልገባ አልዓዛር መሞቱ አይቀርም ከሚባልበት ደረጃ ላይ ተደርሶ ነበር:: እንዲያውም በጣም ዘግይተዋል፤ ምክንያቱም መልእተኛው የአልዓዛርን ሁኔታ ለኢየሱስ በሚነግረው ጊዜ አልዓዛር ሞቶ ነበር::[50]

ኢየሱስ በትክክል የት እንደ ነበር ዮሐንስ አያመለክተንም:: ይሁንና መጥምቁ ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረበት አቅራቢያ ዮርዳኖስ ማዶ ነበር (ዮሐ 10÷40):: መልእክተኛው ኢየሱስ ከነበረበት ለመድረስ ሁለት ቀን ሙሉ ሳይወስድበት አልቀረም:: ባልተጠበቀ ሁኔታ ኢየሱስ መልእክተኛውን በሚከተሉት ቃሎች አሰናበረው፤ «ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ለእግዚአብሔር ክብር ነው

[50] የድርጊቱን ቅደም ተከተል በራሳችን አገላለጽ እንደ ገና አስፍረነዋል:- (1) አልዓዛር ከመሞቱ ሁለት ቀን በፊት መልእክተኛ ወደ ኢየሱስ ተካከ፤ (2) መልእከተኛው ከሁለት ቀን በኋላ ኢየሱስ ካለበት ቦታ ደርሶ አልዓዛር በሞት አፋፍ ላይ እንደሚገኝ ነገረው፤ (3) አልዓዛር እንደማይሞት ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ ይዞ (ቊ 4)፣ አልዓዛር በሞተ በሁለተኛው ቀን መልእክተኛው ወደ ቢታንያ ተመለሰ፤ (4) በዚያው ቀን ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ቢታንያ ለመሄድ ተነሡ፤ (5) አልዓዛር ከሞተ አራት ቀን ሆኖት ሳለ ከሁለት ቀን በኋላ ደረሱ (ቊ 17፣ 39)::

እንጂ ለሞት የሚያደርስ አይደለም» (ከ9÷3 ጋር ያነጻጽሩ):: ወደ ቢታንያ በተመለሰ ጊዜ ግን አልዓዛር ሞቶ ነበር::

እንግዲህ የአልዓዛር ሕመም (በዚህ ጊዜ ሞት) ለእግዚአብሔርና ለኢየሱስ ክብር የሚያመጣ የመሆኑ መልእክት ሲደርሳቸው ነገሩ እኅትማቾቹን ግራ ሳያጋባቸው አልቀረም:: ቢሆንም እንቆቅልሹ እምነታቸውን አላናወጠውም:: ኢየሱስ ስሕተት ፈጽሞአል ብሎ ከመቃወም ፈንታ ቃሉን ተምሳሌታዊ (ዘይቤአዊ) በሆነ መልኩ ተረጐሙት (ቍ 23-24):: የኢየሱስ ቃሎች ግን እማሬያዊ (ቃል በቃል) ነበሩ:: አልዓዛርን ከሞት ያስነሣዋል ብለው ለማሰብ ግን አልቻሉም:: ርግጥ የኢያኢሮስን ሴት ልጅ (ማቴ 9÷18-25፤ ማር 5÷21-43፤ ሉቃ 8÷40-56) በናይን ደግሞ የመበለቲቱን ወንድ ልጅ (ሉቃ 7÷11-17) ከሞት ማስነሳቱን ያወቃሉ:: እነዚህ «መነሣቶች» የተከናወኑት የከረረ ሁኔታ ከመከሠቱ በፊት ነው:: ይህ በዐይነቱ ልዩ የሆነ ተአምር ነው::

በቍጥር 11 መሠረት አልዓዛር መቼ እንደ ሞተ ኢየሱስ ያውቃል:: ይህን የተገነዘበው በመለኮታዊ ዐዋቂ ኩሉነቱ ሊሆን ይችላል:: መልእክተኛው አልዓዛር መሞቱን ለኢየሱስ እንዲነግረው ወዲያውኑ ተመልሶ ተልኮ ሊሆን ይችላል:: አንድም ኢየሱስ በአልዓዛር የቀብር ሥነ ሥርዐት ላይ እንዲገኝ ጠርተውት ሊሆን ይችላል፤ ወይም ምንም ማድረግ ስለማይቻል (አደገኛ ሁኔታም ስላለ) እንዳይመጣ ይነግረው ዘንድ ይሆናል መልእክተኛውን የላኩት::

ዮሐ 11÷7-10

7ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፣ «ወደ
ይሁዳ እንመለስ» አላቸው::
8እነርሱም፣ «መምህር ሆይ፤ ከጥቂት ጊዜ
በፊት አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩህ እየፈለጉህ ነበር፤
እንደ ገና ወደዚያ ትሄዳለህን? »አሉት::



9ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ «ቀኑ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ብርሃን
አይደለምን? ከዚህ ዓለም ብርሃን የተነሣ ስለሚያዩ በቀን የሚመላለስ አይሰናከልም፤
10የሚሰናከለው ግን በሌሊት የሚመላለስ ነው፤ ብርሃን የለውምና::»

ኢየሱስ ይሁዳን ለቆ የሄደው በቤተ መቅደስ መታደስ በዓል ላይ የግድያ ሙከራ ስለ ተደረገበት ነው (ዮሐ 10÷31:39-40፤ እንዲሁም 8÷59):: ወደዚያ መመለስ አደገኛ መሆኑ የታወቀ ነው:: እንዲያውም ከሁለት ወር በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሴም ሲሄድ ይገደላል:: ደቀ መዛሙርቱ ሊመጣ ያለውን አደጋ ያውቃሉ፤ ስለዚህ ኢየሱስ ወደ ይሁዳ እንመለሳለን ባለ ጊዜ ተቃውሞ አሰሙ::

ኢየሱስ ይህን እንቆቅልሽ አስመልክቶ መልስ የሰጠው በቀን ውስጥ ዐሥራ ሁለት የሥራ ሰዓት መኖሩን በማመልከት ነው (ከማቴ 20÷1-4 ጋር ያነጻጽሩ):: በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ለእግዚአብሔር የሚሠራው ሥራ ገና አላለቀም (ከ9÷4 ጋር ያነጻጽሩ):: ሰዓቱ እስከሚደርስ ድረስ ማንም በእርሱ ላይ ጣቱን ለማሳረፍ አይችልም (2÷4፤ 7÷6:30፤ 8÷20፤ 12÷23:27፤ 17÷1):: ኢየሱስ «ጊዜው» ስላልደረሰ እንዳይያዝ ጥንቃቄ ቢያደርግም፤ በኢየሩሳሌም እንኳ ሳይቀር ጊዜው ሳይደርስ ማንም ሊገድለው አይችልም:: በመሆኑም አስጊ ሁኔታ ላይ ያለው ኢየሱስ አይደለም:: ችግር ውስጥ የሚገቡት በዐይን አውጣነታቸው የእግዚአብሔርን ዕቅድ ችላ የሚሉት (በጭለማ የሚራመዱት) ናቸው::

ዮሐ 11÷11-16

11ይህን ከነገራቸው በኋላ፣ «ወዳጃችን
አልዓዛር ተኝቶአል፤ እኔም ከእንቅልፉ ላስነሣው
እሄዳለሁ» አላቸው::
12ደቀ መዛሙርቱም፣ «ጌታ ሆይ፤ ተኝቶ ከሆነስ ይድናል» አሉት::
13ኢየሱስ ይህን የነገራቸው ስለ ሞቱ ነበር:: ደቀ መዛሙርቱ ግን እንቅልፍ ስለ
መተኛቱ የተናገረ መሰላቸው::

14ስለዚህም በግልጽ እንዲህ አላቸው፤ «አልዓዛር ሞቶአል፤ 15ታምኑ ዘንድ፣
በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ አሁን ግን ወደ ወደ እርሱ እንሂድ።»
16ከዚያም ዲዲሞስ[51] የተባለው ቶማስ ለቀሪት ደቀ መዛሙርት፣ «እኛም
ሄደን ከእርሱ ጋር እንሙት» አላቸው።

አሁንም ኢየሱስ የተናገረውን ያስተዋለ ሰው የለም። ይህም የሆነው ቃሎቹ ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ ሳይሆን፣ በጥሬ ትርጉማቸው በመታየታቸው ነው። ደቀ መዛሙርቱ አልዓር በመተኛቱ ተደስተዋል። ይህ ብዙ ጊዜ የመዳን ምልክት ነው። ኢየሱስ ይናገር የነበረው ግን እንዲህ ስላለው እንቅልፍ አልነበረም። «ተኝቶአል» ሲል ሞቶአል ማለቱ ነበር (ከዘፍ 47÷30፤ ከ2ሳሙ 7÷12፤ ከማቴ 27÷52፤ ከሐሥ 7÷60፤ ከ1ተሰ 4÷13 ጋር ያነጻጽሩ)።[52] ይህ ሞት አስደሳች ተመክሮ ለሆነላቸው በተለይ ለአማኞች ተገቢ የሆነ አገላለጽ ነው (መዝ 116÷15፤ ሉቃ 16÷22፤ 23÷43፤ ዮሐ 14÷2፤ ፊል 1÷21:23፤ 2ጢሞ 4÷6)።

ደቀ መዛሙርቱ የተናገረውን ሐሳብ በቁሙ በመረዳታቸው ኢየሱስ መራራ የሆነውን እውነት አወጣው፤ *አልዓዛር ሞቶአል!* በማለት። ኢየሱስ በወዳጅ ሞት ሐሤት የሚያደርግና ልቡ በኃዘን የማይነካ ሰው ሊመስል ይችላል። እርሱ ገና ከጅምሩ መጨረሻውን ለማየት የሚችል ነው። የሚያውቀው አልዓዛር እንደ ገና ወደ ሕይወት የሚመለስ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ ይህን በማድረጉ ደቀ መዛሙርቱ

---

[51] የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ «መንታ» ማለት ነው። ይህ የቶማስ እማሬያዊ (ቃል በቃል) ገለጻ ነው ብለን የምንናገረው በግምት ብቻ ነው።

[52] ሄንድሪክሰን የተባለው ምሁር እንደ ጻፈው (ገጽ 143) ለ«ሞት» «እንቅልፍ» የሚለው አገላለጽ፣ ለ«ነፍስ-መተኛት» አስተምህሮ ተገቢ የሆነ መሠረት አይደለም። ነፍስ *ለዚህ* ዓለም «የተኛች» ብትሆንም (ኢዮ 7÷9:10፤ ኢሳ 63÷16፤ መክ 9÷6)፣ በራሷ ዓለም ግን ንቁ ናት (ሉቃ 16፤ 19÷31፤ 23÷43፤ 2ቆሮ 5÷8፤ ፊል 1÷21-23፤ ራእ 7÷15-17፤ 20÷4)።



በእምነታቸው ረገድ ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚሸጋገሩ መሆናቸውንም ነው።

ቶማስ የዚያ ቡድን አለቃ ሆኖ ብቅ አለ። (ይህ ሁኔታ ኤደርሼይም የተባለው ጸሐፊ ጴጥሮስና ዓሣ አጥማጅ አጋሮቹ ገሊላ አቅራቢያ በነበሩ ጊዜ ቤተ ሰቦቻቸውንና ሥራቸውን ለማየት የተወሰነ የዕረፍት ጊዜ አገኙ ብሎ ከመገመት አደረሰው። በሐዋርያቱ አራት ዝርዝሮች ውስጥ (ማቴ 10÷2-4፤ ማር 3÷16-19፤ ሉቃ 6÷14-16፤ ሐሥ 1÷13)፣ ቶማስ የተወሳው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ከትንሣኤም በኋላ ቶማስ ከጴጥሮስ ጋር ዓሣ ለማጥመድ ሄደ (ዮሐ 21÷2)። ርግጥ ነው በእጅጉ የታወቀው «የቶማስ ምንባብ» ዮሐንስ 20÷24-28 ነው። ይህም ኢየሱስ ከሙታን የተነሣ መሆኑን የተጠራጠረበት ክፍል ነው። ይህ ደግሞ ኢየሱስን ከማየታቸው በፊት ስለ ሌሎቹም ዐሥር ደቀ መዛሙርት ሊባል የሚችል ነው። («ተጠራጣሪው ቶማስ» ስለሚለው ተገቢ ያልሆነ አጠራር የቊ 17 ማብራሪያን ይመልከቱ)።

ይህ «ተጠራጣሪው ቶማስ» ከኢየሱስ ጋር ለመሞት ሙሉ እምነት አለው! ኢየሱስ ወደ ይሁዳ ቢመለስ የሚደርስበትን አደጋ በሚገባ ተረድቷል፤ ኢየሱስ በሚገደልበት ጊዜ ደግሞ ደጋፊው ሆኖ ለመቆም ፈቃደኛ ሆኖአል። አንዳንዶች እንዲያ መናገሩ ለማስመሰል ነው ምክንያቱም ከኢየሱስ ጋር የመሞቱ ጊዜ በመጣ ወቅት እርሱና (ሌሎቹ) ሩጠው አምልጠዋል (ማቴ 26÷56) ይላሉ። ጴጥሮስም ያደረገው ይህንኑ ነበር (ማቴ 26÷56)፤ ቶማስ ከልቡ የተናገረ መሆኑን ግን ማንም አይጠራጠርም። እንደ ብዙዎቻችንም የቶማስና የጴጥሮስ ሐሳብ ከተግባራቸው የተሻለ ነበር።

**§ 118ለ**
**አልዓዛር ከሞት ተነሣ**
**(ዮሐ 11÷17-44)**

17ኢየሱስ ሲደርስ አልዓዛር ከተቀበረ አራት ቀን
ሆኖት ነበር። 18ቢታንያ ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አምስት
ምዕራፍ[ii] ያህል ትርቅ ነበር። 19ብዙዎች አይሁድም

ማርታንና ማርያምን ስለ ወንድማቸው ሞት ሊያጽናኗቸው መጥተው ነበር፤ 20 ማርታ የኢየሱስን መምጣት ሰምታ ልትቀበለው ወጣች፤ ማርያም ግን በቤት ቀርታ ነበር።

21 ማርታም ኢየሱስን እንዲህ አለችው፤ «ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ባልሞተ ነበር። 22 አሁንም ቢሆን የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ ዐውቃለሁ።»

23 ኢየሱስም፣ «ወንድምሽ ይነሣል» አላት።

24 ማርታም፣ «በመጨረሻው ቀን፣ በትንሣኤ እንደሚነሣ ዐውቃለሁ አለችው።

25 ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት እንኳ በሕይወት ይኖራል፤ 26 በእኔ የሚኖር፣ የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህን ታምኛለሽን?»

27 እርሷም፣ «አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ† የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አምናለሁ» አለችው።

*″18 ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ነው*
*†27 ወይም መሲሕ*

ኢየሱስ በደረሰ ጊዜ ማርያምና ማርታ ሐዘን ላይ ከተቀመጡ አራት ቀን ሆኗቸው ነበር። በአንድ አይሁድ ሐዘን ላይ መቀመጥ አንድ ዓመት ሙሉ ሊወሰድ ይችላል። ርግጥ ነው በመጀመሪያው ቀን የመረረ ሐዘን አለ፤ ይህም በሦስተኛውና በሰባተኛው ቀን እያደር ይቀንሳል። ሐዘኑ ለዐሥራ ሁለት ወራት ቢዘልቅም፣ እስከሚቆምበት ዕለት ድረስ እየቀለለ ይሄዳል። ሐዘንተኞቹን ለማስተዛዘን ከኢየሩሳሌም የመጡ በጣም ዕውቅ «አይሁድ» አብረዋቸው አሉ፤ እነዚህም ለዳስ በዓልና ከቤተ መቅደስ መታደስ በዓል በኋላ ኢየሱስን በጣም አውቀውታል። ያለጥርጥር እነዚህ ብዙዎቹ አይሁድ ማርያም፣



ማርታና አልዓዛር «በኢየሱስ ቡድኖች» ወዳጆች እንደ ነበሩ ሁሉ እነርሱም ወዳጆች ነበሩ (ቊ. 45)። አንዳንዶቹ ግን ወዳጆች አልነበሩም (ከቊ. 46 ጋር ያነጻጽሩ)።

ኢየሱስ በመምጣት ላይ የመሆኑ ወሬ ሲሰማ ወደ ከተማ ከመግባቱ በፊት ልታስቀምጠው ማርታ ሮጠች፤ «አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ባልሞተ ነበር» ያለችው አነጋገር በኢየሱስ ድርጊት አለመናደዷን ነገር ግን በአልዓዛር ሞት ማዘኗን ያመለክታል። ኢየሱስ ግን ሐዘን ላይ እያለች እንኳን ተስፋ ሰጣት፣ «አሁንም ቢሆን የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሰጥህ ዐውቃለሁ» አለች። «የምትለምነውን» የሚለው ቃል አስደናቂ ነው ይላል ሄንድሪክሰን የተባለ ጸሐፊ (ገጽ 148-149)፡-

> ኢየሱስ ተጠቅሞበት በማያውቀውና ለጸሎት በሚያገለግለው ቃል ተጠቀመች (አይቲኦ - aiteo መለመን)። ማርታ የተጠቀመችበት ቃል፣ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ሰው፣ ማዕረግ (ክብር) ያለውን ሰው ሲጠይቅ የሚጠቀምበት ተገቢ ቃል ነው (4፥9፡10፤ 14፥13፤ 15፥7፡16፤ 16፥23፡24፡26)። በአንጻሩ ግን ኢየሱስ የራሱን ጥያቄ ሲያቀርብ የተጠቀመበት፣ የሁለቱን አካሎች እኩልነት በሚያመለክተው ቃል ነው (*ኤሮታኦ - erotao*)።

አልዓዛር የማይሞት መሆኑንና በእርሱ ሕመምም እርሱና እግዚአብሔር እንደሚከብሩ ተስፋ በመስጠት ኢየሱስ መልእክተኛውን መልሶ ወደ ማርታ ላከው። አልዓዛር ግን በዚያ ጊዜ ሞቶአል። አልዓዛርን ባለመፈወሱ ማርታ ኢየሱስን ልትወቅሰው አትችልም። መልእክተኛው በጣም ዘግይቶ ወደ እርሱ መላኩ የታወቀ ነው። ኢየሱስ የላከው መልእክት ግን የአልዓዛርን ሞት ያገናዘበ አይመስልም። ለዚህ ነው ማርታ በኢየሱስ ያላት እምነት ሳይናወጥ፣

አልዓዛርን በፍርድ ቀን እንደሚያስነሣው ተረድታ የኢየሱስን ቃል በመንፈሳዊ ረገድ የተረጐመችው::

በፍርድ ቀን ኢየሱስ ተስፋችን ነው:: ምን ያህል ቡሩክ ተስፋ ነው! እርሱ በእርግጥ «ትንሣኤና ሕይወት ነው» (ዮሐ 6÷39-40:44:54፤ 1ቆሮ 6÷14፤ 15÷20-28፤ 2ቆሮ 4÷14፤ እንዲሁም ሐሥ 4÷2፤ 23÷6፤ 24÷15፤ ሮሜ 6÷5፤ 1ቆሮ 15÷42፤ ፊል 3÷10-11፤ ራእ 20÷5-6):: ስለዚህ ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ «እኔ ነኝ» የሚለው የኢየሱስ የእምነት ቃል ይገኛል:: ቃሉ በማርታ ውስጥ አንድ ነገር ቀሰቀሰ:: ስለዚህ ከጴጥሮስ ታላቅ የእምነት መግለጫ ጋር በሚወዳደር ሁኔታ በክርስቶስ ያላትን የእምነት ቃል ተናገረች (ማቴ 16÷16-18)::

## በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ክርስቶስ አዳኝና ጌታ መሆኑን በማመን የቀረበ የእምነት መግለጫ

| | |
|---|---|
| መጥምቁ ዮሐንስ | «እነሆ፤ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (1÷29):: |
| እንድርያስ | «መሲሑን አገኘነው» (1÷41):: |
| ፊልጶስ | «ሙሴ በሕግ መጻሕፍት፣ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉለትን ... አግኝተነዋል» (1÷45):: |
| ናትናኤል | «ረቢ! አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፣ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ» (1÷49):: |
| ሳምራውያን | «ይህ ሰው በእውነት የዓለም አዳኝ እንደ ሆነ እናውቃለን» (4÷42):: |
| ስምዖን ጴጥሮስ | «አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ አንተ አንድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆንህ አምነናል፤ ዐውቀናልም» (6÷68-69):: |
| ማርታ | «አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አምናለሁ ...» (11÷27):: |



የማርታ ተስፋና እምነት ኢየሱስ ከሰጣት ተስፋ ልክ አይደርስም:: ዞሮ ዞሮ ኢየሱስ የሚሰጠው የዘላለም ሕይወት ከአልዓዛር ከሞት መነሣት ይበልጣል:: ይሁን እንጂ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 11 ውስጥ ያለው ተአምር ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ሊሰጠን የሚችል ለመሆኑ ከዋና ዋና ማረጋገጫዎቹ አንዱ ነው:: በሌላም አገላለጽ ዛሬ አልዓዛርን ከሞት የሚያስነሣ ከሆነ ወደፊት እኛን ከሞት ሊያስነሣን ይችላል::[53]

ዮሐ 11÷28-37

[28]ይህን ካለች በኋላ፣ ተመልሳ እኅቷን
ማርያምን ለብቻዋም ጠርታ፣ «መምህሩ መጥቷል፤
ይፈልግሻልም» አለቻት:: [29]ማርያምም ይህን እንደ
ሰማች፣ ፈጥና
ተነሥታ ወደ እርሱ ሄደች:: [30]በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ማርታ እርሱን በተቀበለችበት ቦታ
ነበር እንጂ ገና ወደ መንደር አልገባም ነበር:: [31]ማርያምን ሊያጽናኑ በቤት ውስጥ
የነበሩ አይሁድም፣ ብድግ ብላ መውጣቷን ሲያዩ፣ ወደ መቃብሩ ሄዳ የምታለቅስ
መስሎአቸው ተከተሏት::
[32]ማርያምም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቦታ ደርሳ እንዳየችው፣ እግሩ ላይ
ተደፍታ፣ «ጌታ ሆይ፤ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፣ ወንድሜ ባልሞተ ነበር» አለችው::
[33]ኢየሱስም እርሷ ስታለቅስ፣ ተከትለዋትም የመጡት አይሁድም ሲያለቅሱ
ባየ ጊዜ መንፈሱ በሐዘን ታውኮ፣ [34]«የት ነው ያኖራችሁት?» ሲል ጠየቀ::
እነርሱም፣ «ጌታ ሆይ፤ መጥተህ እይ» አሉት::
[35]ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ::

[53] J.P. Martin የአልዓዛር ከሞት መነሣት የኢየሱስን ከሞት መነሣት ተስፋ የሚያመለክትና የሚያረጋግጥ ብቻ ሳይሆን፣ እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች በአንድ ላይ ሆነው ዮሐንስ ወንጌልን አንባቢዎች እነርሱም በመጨረሻው ቀን እንደሚነሡ ያረጋግጥላቸዋል:: ስለዚህ ይህ ታሪክ ከታሪክ ፋይዳነቱ በተጨማሪ ሥነ ፍጻሜያዊ ጉንና ጥብቅ ምክር አለው ("History and Eschatology in the Lazarus Narrative, John 11:1-44" *SJT* 17 [1964]: 332-343).

**36ኢየሱስም፣ «እንዴት ይወደው እንደ ነበር እዩት!» አሉ።**

**37ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን፣ «የዐይነ ስውሩን ዐይን የከፈተ፣ ይህም ሰው እንዳይሞት ማድረግ አይችልም ነበር?» አሉ።**

ማርታ እስከተመለሰችበት ወቅት ድረስ ኢየሱስ መምጣቱን ማርያም ያላወቀች ይመስላል። ማርያምን ለብቻዋ ጠርታ ኢየሱስ መምጣቱን ነረገቻት። መገመት እንደምንችለው ወዲያውኑ ወደ በሩ ሮጠች። እርሷን ለማጽናናት ከኢየሩሳሌም የመጡት ወዳጆቿ ከቤት በፍጥነት በወጣች ጊዜ ሥጋት ገባቸው። የሚያላቅሳት ሰው ያስፈልጋት እንደ ሆነ ወይም እርሷን የሚደግፋት ጠንካራ ክንድ ያለው ሰው ያስፈልጋት እንደ ሆነ በማሰብ ተከተሏት። ወደ ኢየሱስ ቀጥ ብላ መራቻቸው።

በሆነ ምክንያት ኢየሱስ አሁንም በከተማዋ ዳርቻ ላይ ነው። ምናልባት «መቃብሩ አካባቢ» ሊሆን ይችላል። ምናልባትም ወደ ከተማዋ መግባቱን ተከትሎ የሚመጣውን አደጋ ስላልፈለገ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ማርታን በግል እንዳነጋገራት ሁሉ ማርያምንም በግል ሊያነጋግራት ፈልጎ ሊሆን ይችላል።

ማርያም እንደ ደረሰች እግሩ ላይ ወደቀች። ከዚያ ላይ መጽናናትን (ብርታትን) የምታገኝ ይመስላል (ከሉቃ 10፥29፤ ከዮሐ 12፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። የእኅቷን ንግግር ቃል በቃል ደገመች። ኢየሱስ ወንድሟን ማዳን ይችል እንደ ነበር እርሷም ታምናለች። ባለፈው ሳምንት ኢየሱስ እዚህ ቢሆን ኖሮ! የሚለውን እነዚህ እኅትማማቾች ምን ያህል ደጋግመውት ይሆን። በተመሳሳይ ቃላት ማርታ ኢየሱስን ወደ ነገረ መለኮታዊ ውይይት ስታነሣሣው ማርያም ግን ልቡን ማነሣሣቷ የሚያስደንቅ ነው!

ትስብእት በዚህ ጽሑፍ ላይ ከመለኮት ጋር እንዴት እንደ ተዋሐደ መመልከቱ አስገራሚ ነው! ከዚህ ወቅት ጀምሮ አልዓዛር



እንደገና እንደሚኖር ኢየሱስ ያውቃል። ሣቅና ሐሤት ይሆናል። ይሁን እንጂ በወቅቱ በነበረው ስሜት ልቡ ተነክቶአል። ወዳጁ ሞቶአል፤ ማርያም ደግሞ እንባዋን እያወረደች እግሩ ላይ ወድቃለች። ለማስተዛዘን የመጡት ሰዎች እንባቸው እየወረደ በሐዘነ ወደ እርሷ ይመለከታሉ። ኢየሱስ በሐዘን ልቡ ተነካ።

የኢየሱስን ስሜት ለመገለጽ የገቡት ሁለት ቃሎች ብርቱ ናቸው። የመጀመሪያው *ኢምብሪማኦማይ - embrimaomai* ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ የሚያገለግለው ሐዘንን ሳይሆን ቍጣን ለመግለጽ ነው (ማቴ 9፥30፤ ማር 1፥43፤ 14፥5)። ቃል በቃል ሲገለጽ «እንደ ደረሰ ማናፋት» ማለት ነው። ሁለተኛው ቃል *ታራሶ - tarasso* ማለት «ለቍጣ መነሣሣት» ወይም «አነሣሣ» ማለት ነው። ማዕበል የሚያናውጠውን ባሕር ለመግለጽ ያገለግላል (ኢሳ 24፥14፤ ሰብዓ ሊቃናት ትርጕም)። ኢየሱስ ማዘን ብቻ ሳይሆን፣ ነገሩ አሳስቦታል። በዔደን ገነት ከተከሠተው ውድቀት የተነሣ በተከሰተው ሞት ላይ የተቈጣ መሆኑን ለመገመት እንዲያውም እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። የዔደንን ውብ ዓለም በመበከሉ ብቻ ሳይሆን አሁን በዙሪያው ያለቱትን ሰዎች ማጥፋቱን በመቀጠሉ በሰይጣን ላይም ተቈጥቶአል። እንዲሁም ሕይወትን ራሱን የፈጠረ በፊታቸው የቆመ መሆኑን ባለማመናቸውና ባለመረዳታቸው በዙሪያው ባሉት ሰዎች ተቈጥቶአል። አሁን ከማርያም ጋር ከሚያለቅሱት አይሁድ አንዳንዶች ከዛሬ ሦስት ወር በኋላ ከዚህ ቦታ ሦስት ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው ቦታ በመስቀል ላይ በሚሰቃየው የኢየሱስ አካል ሐሤት ያደርጋሉ።

ኢየሱስ በጠየቀው መሠረት የአልዓዛርን መቃብር አሳዩት። ጌታችን በሰው ዘር ሁኔታ ድባብ ውስጥ ሲገኝ አሁንም ልቡ ተነካ። ቍጥር 35 የኢየሱስን ትስብእትነት በእንዲህ ዐይነቱ ግልጽነትና ጥልቅ እውነታ አስፍሮታል፦ «ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ።» የኢየሱስ እንባ

ለታይታ ዋይታቸውን እንደሚያሰሙት (አንዳንዶች ጥርጣሬ በሚያሳድር ቅነት) እንደ አይሁድ ሳይሆን እንዲሁ የሚወርድና በቍጥጥር ሥር የሚገኝ ነው (ከዕብ 5፥7 ጋር ያነጻጽሩ)::[54] ይሁን እንጂ እንባው የሕዝቡን ሐሳብ ማርኳል:: ይህ እንባ አልዓዛርን የቱን ያህል ይወደው እንደ ነበር ግልጽ ምልክት ነው:: ከዚህ የሚከተለውን በልቡ ሳያብላላ አልቀረም:- «ቀደም ሲል ከዚህ አለመገኘቱ አሳፋሪ ነው:: በእርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ነገር ማድረግ ይችል፤ ሁላችንንም ከዚህ ሐዘን ያድነን ነበር::» በስፍራው በመገኘታቸው እና ኢየሱስ ቀደም ሲል እዚያ ባለመገኘቱ የቱን ያህል ዕድለኞች መሆናቸውን የሚያወቁት ከሕዝቡ ከስንት አንድ ናቸው::

**ዮሐ 11፥38-44**

38ኢየሱስ ልቡ ደግመኛ በሐዘን ተነክቶ ወደ
መቃብሩ መጣ፤ መቃብሩም በድንጋይ የተገጠመ ነበር፤
39እርሱም፣ «ድንጋዩን አንሡት» አለ::
የሟቹም እኅት ማርታ፣ «ጌታ ሆይ፤ አሁንማ አራት ቀን ስለ ቈየ ይሸታል»
አለችው::
40ኢየሱስም፣ «ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለሽ ብዬ
አልነገርሁሽም?» አላት::
41ስለዚህ ድንጋዩን አነሡ:: ኢየሱስም ወደ ላይ ተመልክቶ እንዲህ አለ፤
«አባት ሆይ፤ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ 42ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፤
ይህን መናገሬ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደላከኸኝ ያምኑ ዘንድ ነው::»
43ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ በታላቅ ድምፅ፣ «አልዓዛር ና ውጣ!» ብሎ
ተጣራ:: 44የሞተውም ሰው እጅና እግሩ በቀጭን ስስ ጨርቅ እንደ ተጠቀለለ፣ ፊቱን
በሻሽ እንደ ተጠመጠመ ወጣ::
ኢየሱስም «መግነዙን ፍቱለትና ይሂድ» አላቸው::

[54] የማርያምን አለቃቀስና (ቍ 31:33) የአይሁድን አለቃቀስ (ቍ 33) ለመግለጽ የገባው ቃል *ክላዮ - klaio* ሲሆን፣ «እየጮኹ ማልቀስን» ያመለክታል:: የኢየሱስን አለቃቀስ ለመግለጽ የገባው ቃለ ግን *ዳክርዮ - dakryo* ሲሆን፣ እንባ ማፈሰስን ብቻ ያመለክታል::



ኢየሱስ ዋሻው ፊት ለፊት ቁሞአል፤ ምናልባት መቃብሩ ከድንጋይ የተወቀረ ሊሆን ይችላል::[55] ጥንብ አንሣዎች እንዳይደርሱበት ሲባል ዋሻው ልዩ ቅርጽ ባለው በትልቅ ድንጋይ ተከድኖአል:: ይህ ክዳን በመበስበስ ላይ ያለውን አካል ሽታ በመጠኑም ቢሆን «አፍኖ ለማስቀረት» ያግዛል:: ለመደበኛ ቀብር የተለመደው ሰባ አምስት ፓውንድ የሚመዝነው የቅመማ ቅመም ሽቶ እንኳ (ዮሐ 19፥39)፣ ሽታውን ውጦ ለማስቀረት በቂ አልነበረም:: ስለዚህ ኢየሱስ ድንጋዩ እንዲነሣ ሲያዝ ማርታ ተቃወመች:: ዘግናኝ ሽታና ዘግናኝ ተግባር ይሆን ነበር:: በአንድ አይሁድ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉት እጅግ አሳዛኝ ድርጊቶች ውስጥ አንዱ አስከሬኑን ማጕሳቈል ነው:: ድንጋዩን ማንከባለል እንግዲህ ካለው አሳዛኝ ድርጊት የራቀ ቢሆንም፣ ስሕተት ወደ ሆነ አቅጣጫ የሚያመራ አላስፈላጊ እንቅስቃሴ ነበር::

ኢየሱስ ቃል በመናገር ብቻ ድንጋዩን ለማስወገድ ይችላል:: አልዓዛር ከመቃብር ሲወጣ ድንጋዩን አሽቀንጥሮ ያስወግድ ዘንድ ለእርሱ ኀይል ለማስታጠቅ ይችላል:: እንቅፋቱ ይህ ድንጋይ ሳይሆን እምነት አልባ መሆናቸውና ተስፋ አልባ የሆነው ልባቸው ነው:: ድንጋዩን እንዲያስወግዱ በማድረጉ በአንድ ጊዜ ሁለት መሰናክሎችን አስወገደ::

ድንጋዩን ማስወገድ ለተአምሩ የመጀመሪያው ሲሆን፣ ጸሎቱ ደግሞ ሁለተኛው ዝግጅት ነው:: ኢየሱስ የጸለየው ለራሱ ሳይሆን ለሕዝቡ ሲል ነው:: ይህን ተአምር እንዲሠራ እግዚአብሔርን አልጠየቀም፤ ተአምሩን በመሥራቱ አመሰገነው እንጂ:: ይህ ሁኔታ

[55] ኤደርሼም የተባለው ተመራማሪ አማካይ የቤተ ሰብ መቃብሮችን ለክቶአል፤ 6 ጫማ ስፋት፣ 9 ጫማ ጥልቀት እናም 6 ጫማ ከፍታ አላቸው:: ብዙ ጊዜ ለስምንት ቡድኖች የሚሆኑ ፋካዎች አሏቸው፤ ግራና ቀኝ ሦስት ሦስት ሲሆኑ ከመግቢያው ትይዩ ደግሞ ሁለት ይገኛሉ:: በድኑ ደርቆ ሙሉ በሙሉ ከፈረሰ በኋላ የቤተ ሰቡ አባላት አፅም በሣጥን እየተደረገ የሚቀመጥበት ጥርብ ጥርብ ጉድጓዶች አሉ::

ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን ግልጽ ያደርጋል፡- (1) *ኢየሱስ የተላከው ከእግዚአብሔር ነው::* እግዚአብሔር መለኮታዊ ኀይል ሰጥቶታል፤ ምንጊዜም እርሱን ይሰማል፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሰው ብቻ ሳይሆን ሰው የሆነ እግዚአብሔር ነው፤ ወይም እግዚአብሔርም ሰውም ነው:: (2) *ይህ ተአምር መዝናኛ ሳይሆን ማስረጃ ነው::* አልዓዛርም እንደገና ይሞታል:: እነዚያ ሰዎችም ያን በመሰለ ሐዘን ውስጥ ዳግም ማለፍ ይኖርባቸዋል:: አልዓዛር ከሞት በመነሣቱ ቢደነቁ እና በኢየሱስ ኀይል ቢገረሙም እንኳ፣ እርሱን ጌታ አድርገው ካልተቀበሉት ዋናውን ጉዳይ አጥተዋል ማለት ነው::

«አልዓዛር፤ ና ውጣ!» በማለት ኢየሱስ «በታላቅ ድምፅ ... ተጣራ::» በታላቅ ድምፅ የተጣራው በመግነዝ የተጠቀለለውና በዋሻው ውስጠኛ ስፍራ የሚገኘው አልዓዛር እንዲሰማው ሊሆን ይችላል:: ይሁን እንጂ የአልዓዛር ነፍስ በዚያ ወቅት በመበስበስ ላይ ባለው ሥጋ ውስጥ ስለሌለች ይህ የማይሆን ጉዳይ ነው:: ኢየሱስ በታላቅ ድምፅ የተጣራው በአንድ በኩል ሥልጣን ያለው መሆኑን ለሕዝቡ ለመግለጽ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ግን ከሕዝቡ ሲቃና የሳግ ድምፅ ጎላ ብሎ እንዲሰማ ነው::

አልዓዛር ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ እንደ ተገነዘ ወጣ:: አንዳንዶች እግሮቹ ታስረው ስለነበር እየተራመደ ከመምጣት ይልቅ እንጣጥ እንጣጥ እያለ ከዋሻው ሳይወጣ አልቀረም በማለት ሐሳብ ያቀርባሉ:: ይህም ለትረካው ፈገግ የሚያሰኝ ነገርን ይጨምራል::[56] የራስ ጥምጥሙን እንዲፈቱለት ኢየሱስ ሲነግራቸውም እንዲሁ

---

[56] ድንጋዩና የመግነዝ ጨርቆቹ የኢየሱስን ትንሣኤ በአሻጋሪ ያመለክታሉ:: W.E. Reiser, "The Case for the Tidy Tomb: The Place of the Napkins of John 11:44 and 20:7" *HeyJ* 14 (1973): 47-57 በሚለው ጽሑፉ ውስጥ የመግነዝ ጨርቆቹ ሁለቱን ሁኔታዎች ማገናኘት ብቻ ሳይሆን፣ ያነጻጽሯቸዋል ይላል:: ለአልዓዛር ያ ጨርቅ የሞት ምልክት ሲሆን፣ ለኢየሱስ የሕይወት ምልክት ነው፤ ለዮሐንስ ደግሞ በኢየሱስ ትንሣኤ ለማመን ወሳኝ ማስረጃ ነው ይላል (ዮሐ 20፥6-8)::



ያሥቃል:: (ይተነፍስ ዘንድ) ማን ማንን በማየት ይበልጥ ይደነቅ ይሆን፧ ማርያምንና ማርታን? ወይስ አልዓዛርን? በማለት አንድ ሰው እራሱን መጠየቅ አለበት::

5,000ውን መመገቡ የገሊላ አገልግሎቱ ከፍተኛ ደረጃ እንደሆነ ሁሉ፣ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱም የኢየሱስ ትንሣኤ መግቢያ እና የይሁዳ አገልግሎቱ ከፍተኛ ደረጃ ነው:: እያንዳንዳቸው ሰባቱ ምልክቶች [የዮሐንስ] የኢየሱስን መለኮታዊ ሥልጣን ልዩ ገጽታ ያሳያሉ፤ ይህኛው ግን በመጨረሻውና ሊቋቋሙት በማይቻለው የሰው ዘር ጠላት ማለትም በሞት ላይ ያለውን ሥልጣን ያሳያል:: ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት ብቻ ሳይሆን፣ የአራት ቀን መበስበስ ያስከትል የነበረውን ሁኔታ ለወጠው:: አይሁድ ሕይወቱ ያለፈ ሰው ነፍስ በአካሉ ዙሪያ ሦስት ቀን ሙሉ ትረብባለች ያለው ተስፋ ሁሉ መሟጠጡን ስታይ ትታ ትሄዳለች ብለው ያምናሉ::

ገና ከወዲሁ ሊታወቅ እንደሚችለው ሕዝቡ ተገርመዋል:: ይህም ከሁለት ወር በኋላ በሚከበረው በፋሲካ ዕለት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል:: ሰዎች ስለዚሁ ጉዳይ ይናገራሉ:: ሰዎች ኢየሱስንና አልዓዛርን ለማየት ይፈልጋሉ፤ ይህም በዘመናችን የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ጋዜጠኞች ቃለ መጠይቅ የሚጐርፍበት ዐይነት ነው::

**§ 119**
**ኢየሱስን ለመግደል የፍርድ ሸንጎው ውሳኔ**
**(ዮሐ 11፥45-54)**

የሞተን ሰው ማስነሣቱ ድንጋጤ ፈጥሮአል:: የድንጋጤው ማዕበል ኢየሩሳሌም ደርሶአል:: የፍርድ ሸንጎውን ማእከላዊ አካል እንኳ አሸብሯል:: ቀያፋ፣ «ይህ ሰው መወገድ አለበት» ባለ ጊዜ የተናገረው መሰሎቹን በመወከል ነበር:: በእርግጥም መላውን ሕዝብ በመወከል ትንቢት ተናገረ:: ኢየሱስ መሞት ይኖርበታል፤ የሚሞተው ግን ይህ ማስተዋል

የጐደለው ነቢይ ካቀረበው ሐሳብ ልዩ በሆኑ ምክንያቶች ነው::

[45]ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፣ ኢየሱስ ያደረገውን ካዩት አይሁድ በዙዎች በእርሱ አመኑ:: [46]አንዳንዶቹ ግን ሄደው ኢየሱስ ያደረገውን ለፈሪሳውያን ተናገሩ፤ [47]ከዚያም የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን የአይሁድን ሸንጎ ሰብሰባ ጠሩ::

ዮሐ 11÷45-48

እነርሱም እንዲህ አሉ፤ «ይህ ሰው ብዙ ታምራዊ ምልክቶችን እያደረገ ስለ ሆነ ምን ብናደርግ ይሻላል? [48]እንዲሁ ብንተወው ሰው ሁሉ በእርሱ ያምናል፤ ሮማውያንም መጥተው ስፍራችንንና* ሕዝባችንን ይወስዱብናል::»

**48 ወይም መቅደሳችንን*

ብዙዎች በኢየሱስ ማመናቸው ወይም ብዙዎቹ መሪዎች በእርሱ አለማመናቸው አያስደንቅም:: የአልዓዛር ከሞት መነሣት በጣም አስፈላጊ ድርጊት በመሆኑ የሃይማኖት መሪዎች ማወቅ እንደሚኖርባቸው ሁሉም ተስማሙ:: ነገሩ የነገረ መለኮታዊ ብቻ ሳይሆን፣ የፖለቲካዊም ጉዳይ ነበር:: ይህ ታምር በሕዝቡ ዘንድ ሊያስከትል የሚችለውን ከፍተኛ ስሜት ፈጥሮአል:: አይሁድ ለዐመፅ የሚነሣሡ በመሆናቸው ሮማውያን በዐይነ ቁራኛ ይከታተሏቸው ነበር:: ይህን ባለፉት ቅርብ ዓመታት ውስጥ በተደጋጋሚ አረጋግጠዋል:: ይህ ነው ኢየሱስን ለመያዝና (ዮሐ 7÷30-32:44-45፤ 10÷39) ለመግደል (ዮሐ 5÷18፤ 8÷59፤ 10÷31) ለፍርድ ሸንጎው የጐላ ምክንያት የሆነለት:: የሮማውያኑ ድርጊት የሕዝቡን ደኅንነት የመጠበቅ ጉዳይ ነበር::

አንዳንድ የዐይን ምስክሮች በኢየሩሳሌም ላሉት «ባለሥልጣናት» ተናገሩ:: የፍርድ ሸንጎው በአስቸኳይ እንዲሰበሰብ



ተደረገ:: ከሦስት መደምደሚያዎችም ላይ ደረሱ:- (1) ኢየሱስ ብዙ አስደናቂ ታምራት በማድረግ ላይ ነው:: (2) እርሱን ለማስቆም ያደረጉት ጥረት ከንቱ ሆኖአል:: ለመያዝ ያደረጉትን ሙከራ መና አድርጎ ማስቀረቱ ብቻ ሳይሆን (ዮሐ 7÷44-45፤ 8÷59፤ 10÷39) ከቀን ወደ ቀን ብዙ ሰዎች ይከተሉታል (ዮሐ 7÷31:40-41፤ 8÷30፤ 9÷36፤ 10÷19-21):: (3) እነርሱ የማያስቆሙት ከሆነ ሮማውያን ያስቆሙታል:: የሚያስገርመው ነገር ቀያፋ ኢየሱስን ለማስቆም ያደረገው የነገር አካሄድ (ተጠየቅ) ደቀ መዛሙርቱን ይተዋቸው ዘንድ የፍርድ ሸንጎውን በመከረው በገማልያል መገለጡ ነው:: ገማልያል የፍርድ ሸንጎ አባላቱ ደቀ መዛሙርቱን ማሳደድ ካላቆሙ እነርሱ ራሳቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣሉ መሆናቸውን አስጠንቅቆ ነበር (ሐሥ 5÷38):: ቀያፋና ገማልያል በሁለቱም ስብሰባዎች ሳይገኙ አልቀሩም:: የተነገረው ነገር ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመገልበጡ በሆነው ነገር ከመገረም በቀር ማንም የሚያደርገው ነገር አልነበረም::

ሦስተኛው የሚያሳዝን መደምደሚያ የኢየሱስ ተልእኮ የተሳሳተ መረዳት ማግኘቱ ነው:: የጋራ የሆነው (የወል የሆነው) አይሁዊ ተስፋ ምድራዊ ወይም የፖለቲካዊ መሲሕ ማግኘት ነበር:: የሮምን የቅኝ አገዛዝ እግር ብረት አስወግዶ የአይሁድን ነጻነት (የበላይነት ባይሳካ እንኳን) መልሶ እውን የሚያደርግ ሰው ፈለጉ:: ፈሪሳውያንም እንዲህ ያለውን ተስፋ ተጋሩ፤ ያንኑ ተስፋም ሰበኩ:: ነገር ግን፣ አሁን እየመጣ መሆኑን ቢመለከቱም ፈጽሞ አይፈልጉትም:: ደም ያለበት አብዮት የሚያስከትለው አደጋ እጅግ ከፍተኛ ነው:: ከዚህም በላይ በሮም ላይ ይህን ያህል ቢያጉረመርሙም እንኳ፣ እውነቱ ይነገር ከተባለ፣ ሁኔታዎች አሁን ባሉበት ሁኔታ ይቀጥሉ ዘንድ ይፈልጋሉ:: ሥልጣናቸው ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ወይም መሲሕ በሚሆን ሰው እንዲገፈፍ አይፈልጉም::

ይህ የሰዱቃውያን (የፍርድ ሸንጎ) ጉባኤ፣ ስለ አባላቱ መሰሪ ሁኔታዎች ያሉት ነው:: (1) ከእግዚአብሔር መንግሥት ይልቅ ለሹመታቸው በጣም ይጨነቃሉ:: (2) ከአሥጊ ጠላት እግዚአብሔር ይዋጋልናል ብለው እምነታቸውን በእርሱ ላይ አይጥሉም:: (3) በመንፈስ ሳይሆን በሥጋ ስለሚያስቡ መደምደሚያዎቻቸው ስሕተቶች ናቸው:: (4) የሕዝቡን በጎ ነገርና የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት ይሻሉ ብሎ ስለ እነርሱ የሚያስበውን የአይሁድ ሕዝብ በማታለል ላይ ናቸው:: (5) መሲሑን አይፈልጉም:: የኢየሱስን ታምራትና መሲሕን የሚያሳዩትን የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነቶች ዋጋ ያሳጣሉ:: ይህን ለማድረግ ግን አልቻሉም:: በመሆኑም ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሹመታቸውን እየመረጡ መሲሓዊ ተስፋቸውን አሽቀንጥረው ይጥላሉ::

ነገሩን እጅግ የከፋ ያደረገው ስለ መሲሑ ያላቸው የተሳሳተ ግንዛቤ ነው:: የኢየሱስ መንግሥት በወታደር ኀይል የሚቆም መንግሥት አይደለም:: ጲላጦስ ይህን ተገንዝቦአል (ዮሐ 18÷33-38):: ሆኖም ኢየሱስን በመጥላታቸው በጲላጦስ በኩል ከሮም ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጡ:: ኢየሱስን በመግደላቸው ደግሞ በቲቶ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ተጋፈጡ:: በ70 ዓ.ም. ኢየሱስ በተነበየው መሠረት ቤተ መቅደሱን ጨምሮ የእግዚአብሔር ቊጣ ከተማቸውን አወደማት (ማቴ 24÷2፤ ሉቃ 21÷20፤ 23÷27-31):: ቤተ መቅደስ ስለ ወደመ የእንስሳት መሥዋት ተቋረጠ:: ስለዚህ የሰዱቃውያን ወገን ከፍርድ ሸንጎው ጋር ተበተነ:: ሹመታቸውንና ስፍራቸውን ለማዳን ጥረት ቢያደርጉም አወደሚቸው:: ይህ የመንግሥቱ አይአዎ (ተቃራኒ መሰል እውነት) አንድ አካል ነው (ማቴ 10÷39)::

ዮሐ 11÷49-54

[49]ከመካከላቸውም አንዱ፣ በዚያ ዓመት ሊቀ ካህናት የነበረው ቀያፋ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ «እናንተ እኮ ምንም አታውቁም! [50]ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት የሚሻል መሆኑን አታስተውሉም::»

[51]ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ፣ ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንዲሞት ትንቢት መናገሩ ነበር፤ [52]ለዚያም ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው:: [53]ከዚያን ቀን ጀምሮም ሊገድሉት አሤሩ::

[54]ስለዚህ ኢየሱስ ከዚያ ወዲያ በአይሁድ መካከል በይፋ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን በምድረ በዳ አጠገብ ወደምትገኝ ኤፍሬም ወደ ተባለች መንደር ገለል አለ፤ በዚያም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሰነበተ::



ቀያፋ በሊቀ ካህንነት ሹመቱ ከ18-36 ዓ.ም. ኖረ:: ሊቀ ካህናት የነበረው የሐና አማች ነበር:: አይሁድ ሊቀ ካህናቸውን እስከ ዕድሜ ልክ ይቀበሉት ስለ ነበር፣ ሕዝቡ አሁንም ሐናን ለመሪነት ይፈልጉት ነበር:: ኢየሱስ ወደ ቀያፋ ከመወሰዱ በፊት ወደ ሐና በመወሰዱ ሁኔታውን ለመረዳት ይቻላል:: ሮማውያን ግን አንድ ግለሰብ ለዘለቄታው በሥልጣን ላይ እንዲቆይ አይፈልጉም:: ሊቀ ካህኑን ብዙ ጊዜ በሌላ የሚተኩትም ከዚህ የተነሣ ነው:: «በዚያ ዓመት» (ቊ 49) የሚለው ሐረግ ትርጉምም ይህ ሊሆን ይችላል::

ቀያፋ ጉረኛና ባለጌ የነበር ሲሆን፣ የአንድ ሰዱቃዊ አምሳያ ነው::[57] ኢዮሳፍስ (እርሱ ራሱ ፈሪሳዊ ነበር)፣ ስለ ሰዱቃውያን እንዲህ ይላል:-

ፈሪሳውያን እርስ በርስ ይዋደዳሉ፤ ከማኅበረ ሰቡም ጋር ስምም የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋሉ:: ሰዱቃውያን ግን እርስ በርሳቸው እንኳ ንፉጎች ናቸው፤ በጠባያቸው ባለጌ ለባዕዳን እንደ

[57] ብልሹ ጠባይ ማንነቱን ጉልሕ አድርጎ ያሳያል:- ማቴ 26÷3:57፤ ሉቃ 3÷2፤ ዮሐ 11÷49፤ 18÷13:14:24:28፤ ሐሥ 4÷6::

ሆኑትም ለአቻዎቻቸው (ለብጤዎቻቸው) ጨዋነት የጐደላቸው ናቸው::

ሊቀ ካህናቱ ቀያፋ ሳይታወቀው ትንቢት ተናገረ (ከ1ጴጥ 1÷10-12 ጋር ያነጻጽሩ):: እርሱ ልብ ሳይለው እግዚአብሔር ተጠቅሞበታል:: የቃሉን እውነተኛ ትርጉም ትክክለኛነት ቢገነዘብ ኖሮ፣ በመጠኑም ቢሆን ሳያፍር አይቀርም ነበር:: የኢየሱስ ሞት ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ ይሆናል:: ይህ ብቻ ሳይሆን ዮሐንስ፣ የኢየሱስ ደም ዓለምን ሁሉ አንጽቶአል ብሏል (1ዮሐ 2÷1-2)!

የፍርድ ሸንጎው የምሥጢር ሤራ ይበልጥ ይፋ ሆነ:: ኢየሱስን ለመያዝ፣ ለመወንጀልና ለመግደል ከልብ የሆነ የጋራ ጥረት ጀመሩ:: አንድ ሰው (ምናልባትም ኒቆዲሞስ) ለኢየሱስ ማስጠንቀቂያ ላከ:: ከዚህም የተነሣ ዘወር ብሎ በኤፍሬም አገር ቆየ:: የቅሪተ አካል ሊቃውንት ኤፍሬም የተባለው ስፍራ በትክክል የት እንደ ነበር ለማወቅ አልቻሉም:: ሆኖም ምድረ በዳ እንደ መሆኑ መጠን ኢየሱስ በቀላሉ «ዘወር ብሎ» እንዲቆይ አመቸው:: በመጨረሻ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ውስጥ እስከሚገኝ ድረስ፣ የሚቀጥሉት ወሮች በየስፍራውና በመንገዶች ላይ ውይይቶች የሚካሄዱባቸው ይሆናሉ:: ኢየሱስ በቀዳሚነት በገጠር አካባቢዎች ራሱን ገለል አድርጎ ይኖራል፤ የፍርድ ሸንጎው በእርሱ ላይ ከሚያካሂደው አደን (ፍለጋ) ለማምለጥም ከቦታ ቦታ ይዘዋወራል::

## የመጨረሻ ጉዞ ወደ ኢየሩሳሌም

**§ 120ሀ**
**ለምጻሞችን ማዳን**
**(ሉቃ 17÷11-19**

እንደ ብሉይ ኪዳኑ ንዕማን ይህ ሳምራዊ ከእግዚአብሔር ነቢይ ፈውስን አገኘ (2ነገ 5÷8-19):: ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ይህ



ዐይነቱ ነገር እንደሚሆን ተናግሮ ነበር (ሉቃ 4÷23-27):: እንደ ዮሐንስ 4 ሳምራውያንም ይህ ሰው «የዓለምን አዳኝ» አገኘ፤ ያመልከውም ዘንድ ተመለሰ::[58]

**ሉቃ 17÷11-13**

[11]ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ በሰማርያና በገሊላ ድንበር በኩል ዐለፈ:: [12]ወደ አንድ መንደር እንደ ገባም ለምጽ[†] የያዛቸው ዐሥር ሰዎች አገኙት፤ እነርሱም በርቀት ቆመው፣ [13]በታላቅ ድምፅ «ኢየሱስ፤ ጌታ ሆይ፤ ራራልን!» አሉት::

*[†]12 የግሪኩ ቃል ከለምጽ ጋር ብቻ የተያያዙ የተለያዩ የቈዳ በሽታዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ይውላል::*

አልዓዛርን ከሞት ካስነሣ በኋላ የፍርድ ሸንጎው በየአውጣጫው በኢየሱስ ላይ ማስታወቂያ አወጣ:: በመጥፎ ሁኔታ ሊይዙት ፈለጉ:: ኢየሱስ ጊዜው ገና ያልደረሰ መሆኑን ዐውቆ ኤፍሬም በተባለች መንደር ለመደበቅ ወደ ገሊላ ሸሸ (ዮሐ 11÷54):: የፀደይ ወር በመምጣት ላይ ነበር:: ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም የሚወጣበት ወቅትም ነው:: ተመሳሳዮቹ ወንጌላት ሁሉ ይህን የመጨረሻ የማስተማር ጉዞ መዝግበዋል (ማቴ 19÷1-2፤ ማር 10÷1፤ ሉቃ 17÷11):: የታወቁ አንዳንድ ሴቶችን ጨምሮ (ማር 15÷40-41) ብዙ ሕዝብ ከኤፍሬም ጀምሮ እስከ ኢየሩሳሌም ድረስ ተከትለውታል:: ያለ ጥርጥር ለፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ነው::

በገሊላና በሰማርያ መካከል ሲጓዝ በርከት ያሉ ለምጻሞች ጮኸው በጠሩት ጊዜ ኢየሱስ ወደ «ዳርቻ» መንደሮች ለመግባት ተቃርቦ ነበር:: እነዚህ ዘጠኝ አይሁድና አንድ ሳምራዊ በተመሳሳይ ደዌ

[58] D. Hamm, "What the Samaritan Leper Sees: The Narrative Christology of Luke 17:11-19," *CBQ* 56/2 (1994): 273-287.

በመስቃየት ላይ ነበሩ (የቍ 45 ማብራሪያን ይመልከቱ)። ይህ አስጸያፊ በሽታ ባይደርስባቸው ኖሮ በአንድ ላይ አይታዩም ነበር።

ዘሌዋውያን ምዕራፍ 14 የለምጽን ምንነት ቍልጭ አድርጎ ይገልጻል። የሀንሰን በሽታ ብለን የምናውቀው የሥርዐተ ነርቭ በሽታ አይደለም። የለምጽ በሽታ ተላላፊ የቈዳ በሽታ ነው። አስፈሪና ፈውስ የማይገኝለት በሽታ ነበር። እንዲያውም የእግዚአብሔር ሥራ ነው በማለት ማንም ሰው ከለምጽ በሽታ ከቶ ተፈውሶ አያውቅም ነበር። ሕመሙን አስከፊ የሚያደርገው ደግሞ በሰውየው ሕይወት ውስጥ ከኀጢአት ጋር መያያዙ ነበር። ስለዚህ ለምጻሞች ከማኅበረ ሰባቸው ይገለሉ ነበር። ለምጻምን በተመለከተ ሕጋዊ ከሆኑት እገዳዎች (ክልከላዎች) አንዱ፣ በሽተኛው ከጤነኛ ሰው አጠገብ ለመገኘት የሌለበት መሆኑ ነበር። አንድ ጤነኛ ሰው ሳያውቅ ወደ ለምጻም ሰው ቢቀርብ ለመጻሙ፣ «እርኩስ! እርኩስ!» ብሎ የመጮኽ ግዴታ ነበረበት። የሚያዋርድ በሽታ ነበር።

ሉቃ 17÷14-19

14እርሱም ባያቸው ጊዜ፣ «ሂዱና ራሳችሁን
ለካህናት አሳዩ» አላቸው። እነርሱም ወደዚያው በመሄድ
ላይ ሳሉ ነጹ።
15ከእነርሱም አንዱ መፈወሱን ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን
እያከበረ ተመለሰ፤ 16በኢየሱስም እግር ላይ በፊቱ ተደፍቶ አመሰገነው፤ ይህም ሰው
ሳምራዊ ነበረ።
17ኢየሱስም እንዲህ ሲል ጠየቀው፤ «የነጹት ዐሥር ሰዎች አልነበሩምን?
ዘጠኙ የት ደረሱ? 18ከዚህ ከባዕድ ሰው በስተቀር ተመልሰው እግዚአብሔርን
የሚያመሰግኑ የሉም ማለት ነውን?» 19ሰውየውንም፣ «ተነሥተህ ሂድ፤ እምነትህ
አድኖሃል» አለው።

ኢየሱስ ራሳቸውን ለካህን እንዲያሳዩ አዘዛቸው። የመንጻት ሥርዐቱ ሕግም ይኸው ነው (ዘሌ 14÷8-11)። ኢየሱስ ወዲያውኑ



ሳይፈውሳቸው መቅረቱ የሚገርም ነው። በዚህ ፈንታ ወደ ካህናት እንዲሄዱ የነገራቸውን እስከሚታዘዙ ድረስ ቆየ። በእምነት ከእርሱ ተለዩ፤ በመንገድም ላይ እያሉ ከበሽታቸው ነጹ።

እነዚህን ሰዎች በአንድ ላይ ሊያስተሳስራቸው የቻለው ለምጽ መሆኑ የሚያሳፍር ነው። ወዳጆች ሊሆን የቻሉት በሕመም ብቻ ነው። ፈውስን እንዳገኙ ሳምራዊው ሌሎችን ትቶ ተመለሰ። ርግጥ ነው እርሱ ለአይሁድ ካህን ራሱን አያሳይም! የሚሄድበት የራሱ ካህን አለው። ወዳጆቹ ከነበሩት አጋሮቹ ጋር በመኼዝ ፈንታ ኢየሱስን ለማመስገን ተመለሰ።

እንግዲህ ዘጠኙ በመፈጸም ላይ ያሉት የተነገራቸውን ነው። ኢየሱስንና ሕጉን በመታዘዝ ላይ ናቸው። የሚያደርጉት ትክክል የሆነውን ነው። ይሁን እንጂ ሳምራዊው በመፈጸም ላይ ያለው የላቀውን ጉዳይ ነበር። ይህ ለክርስቲያኖችም ቢሆን ከባድ (ብርቱ) ልዩነት ነው። ብዙ ጊዜ ትክክል የሆነውን ለመታዘዝና የእግዚአብሔርን ሕጎች ወደ መፈጸም እናዘነብላለን። ይህን መፈጸሙ በርግጥ ስሕተት አይደለም። ነገር ግን የላቀው ጉዳይ ኢየሱስን ማምለክ ነው። አሁንም ቢሆን በሥርዐትና በግንኙነት መካከል ልዩነትን እናስተውላለን። ትክክል የሆነውን ሁሉ ፈጽሞ ኢየሱስን ሳያገኙ መቅረት አለ።

**§ 120ለ**
**የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣትና የሰው ልጅ**
**(ሉቃ 17÷20-37)**

ይህ ምንባብ ልዩ በሆነ ዳራ ከመቅረቡ በቀር በዐይነኛነቱ ከማቴዎስ ምዕራፍ 24 ጋር አንድ ነው። የተለየ ጊዜ ነው፤ ልዩ ተደራሲም (አድማጭም) ነው፤ የቀረበው ጥያቄም ልዩ ነው። ማቴዎስ 24 ውስጥ ሐዋርያት በቤተ መቅደሱ ስለሚገኙት ውብ ሕንጻዎች ጠየቁ (ከሉቃ 21÷5-38 ጋር ያነጻ)። እዚህም ላይ ስለ

ቤተ መቅደሱ ሳይሆን ስለ መንግሥት ኢየሱስን የሚጠይቁት ፈሪሳውያን ናቸው::

መንግሥት የሚመጣው ደረጃ በደረጃ በመሆኑ ይህ አስቸጋሪ ፅንሰ ሐሳብ ነው:: ኢየሱስ መጀመሪያ ሲገለጥ (ሉቃ 11÷20፤ 17÷21) መንግሥት ነበር:: መንግሥት በጰንጠቆስጤ ዕለት መጣ (ማር 9÷1፤ 16÷28):: የሺህ ዓመት መንግሥት ሆኖም መጥቶአል (ራእ 20÷4):: በመጨረሻና ሙሉ በሙሉም በአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ይገለጣል (ራእ 21÷1-6)::

ኢየሱስ ስለ የትኛው ደረጃ እንደሚናገር ለመለየት አስቸጋሪ ነው:: ይበልጥ አስቸጋሪ የሚያደርገው ደግሞ ማቴዎስ ምዕራፍ 24 በብዛት የሚናገረው በ70 ዓ.ም. ስለ ተፈጸመው ስለ ኢየሩሳሌም መውደም መሆኑ ነው (ከሉቃ 21÷5-38 ጋር ያነጻ):: እዚህ ላይ አንድ ዐይነት ቋንቋ የሚጠቀም ቢመስልም መልእክቱ ግን አይመስልም:: ሁለት ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን ለመግለጽ ተመሳሳይ አጉልቶ ማሳያዎችና ምሳሌዎች የተሰጡ ይመስላል:: ይህ በመጠኑም ቢሆን ግራ ያጋባል:: ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢት የተለመደ ነው::

ኢየሱስ በሁለት ልዩ ልዩ ወገኖች ስለ መንግሥት ሁለት ጥያቄዎችን ተጠይቃል:: በመጀመሪያ ፈሪሳውያን፣ «መንግሥት መቼ ትመጣለች?» በማለት ጠየቁት:: በኋላም በውይይቱ ውስጥ የራሱ ደቀ መዛሙርት፣ «መንግሥት የት ትመጣለች?» በማለት ጠየቁት::

[20]ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ እንደምትመጣ ኢየሱስን በጠየቁት ጊዜ እንዲህ ሲል መለ[illegible]፤ «የእግዚአብሔር መንግሥት በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም፤ [21]ሰዎችም፣ 'እዚህ ነው' ወይም 'እዚያ ነው' ማለት አይችሉም፤ እነሆ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ[ነ] ናትና::»

ሉቃ 17÷20-21



*[ነ]21ወይም በውስጣቸው*

«የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት» ስለ መንግሥት ፍላጎት እንደ ነበራቸው ሁሉ፣ ፈሪሳውያንም ፍላጎት አድሮባቸዋል:: ከሞላ ጐደል ሁሉም ወገኖች ስለ መሲሐዊ መንግሥት ተመሳሳይ ተስፋ አላቸው:: እንዲህ ያ መንግሥት፣ (1) ፖለቲካዊ - መሲሑ የእስራኤልን ጠላቶች ሁሉ (በተለይ ሮማውያንን) በወታደር ኀይል ይደመስሳቸዋል:: (2) ብልፅግና፤ ማመን እስከሚያቅት ድረስ እውን ይሆናል፤ ከመለኮት እንኳን ሳይቀር ለእያንዳንዱ እስራኤላዊ ዜጋ ይሰጣል:: (3) የሚታይ ይሆናል - ሁሉም ማየት ይችሉ ዘንድና በዓለም ሲከበር ተሳታፊዎች ይሆኑ ዘንድ ዕጹብ ድንቅ በሆነ፣ በጕልሕና በሚማርክ ሁኔታ ይከናወናል::

ኢየሱስ፣ «በሚታዩ ምልክቶች አትመጣም» ሲል ሦስተኛውን ሐሳብ ማመልከቱ ነው:: በሰማይ ላይ እንደሚወረወር ሮኬት ወይም በሰልፍ ላይ እንደሚበተን ወረቀት የሚታይ ዐይነት አይደለም:: የሚያሳዝነው ሐሳባቸው ፈጽሞ የተሳሳተ ነበር:: ምክንያቱም ከመንፈሳዊ መንግሥት ይልቅ ምድራዊ መንግሥትን ጠበቁ::

ይህ መንግሥት የሚታይ ሳይሆን መንፈሳዊ በመሆኑ፣ ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ (ይኸውም «በመካከላችሁ ናትና») ነው:: ይሁን እንጂ ይህ ሐረግ፣ «በእናንተ ዘንድ» ወይም ደግሞ «አጠገባችሁ ነው»[59] ተብሎ ሊተረጐም ይችላል:: ኢየሱስ በውስጣቸው ስላለው መንግሥት ዐላማ፣ ባሕርይና ዐይነተኛ ጉዳይ ግንዛቤ ለሌላቸው ፈሪሳውያን የተናገረ መሆኑ ሲታሰብ፣ ኢየሱስ የተናገረው ይህንኑ ሳይሆን አይቀርም:: ስለዚህ በመካከላቸው እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር

[59] H.J. Cadbury, "The Kingdom of God and Ourselves," *ChrCen* 67 (1950): 172-173 and C.H. Roberts, "The Kingdom of Heaven (Lk 17:21)" *HTR* 41/1 (1948): 1-8.

መንግሥት መገለጫ መሆኑን አመላከታቸው፡፡ ከፈለጉ ሊቀበሉት ይችላሉ፡፡ በሌላ አባባል ፈሪሳውያን «መንግሥት መቼ ይመጣል?» ብለው ጠየቁ፡፡ ኢየሱስም፣ «ለመጠየቅ አመች ሆኜ በመካከላችሁ ቁሜአለሁ» በማለት መለሰ፡፡

**ሉቃ 17፥22-29**

[22]ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አላቸው፤
«ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ለማየት የምትመኙበት ጊዜ
ይመጣል፤ ደግሞም አታዩትም፡፡ [23]ሰዎች፣ 'እዚያ ነው'
ወይም 'እዚህ ነው' ይሏችኋል፤ ተከትላችኋቸውም
አትሂዱ፤ [24]ምክንያቱም መብረቅ በርቆ ሰማዩን ከዳር
እስከ ዳር
እንደሚያበራ፣ የሰው ልጅም በሚመጣበት ቀን ልክ እንደዚሁ ይሆናል፡፡ [25]ነገር ግን
ይህ ከመሆኑ በፊት የሰው ልጅ ብዙ መሠቃየትና በዚህም ትውልድ መናቅ
ይኖርበታል፡፡
[26]«በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው ሁሉ፣ በሰው ልጅ ዘመንም እንደዚሁ ይሆናል፡፡
[27]ኖኅ ወደ መርከብ እስከ ገባበት ቀን ድረስ ሰዎች ይበሉና ይጠጡ፣ ያገቡና ይጋቡ
ነበር፤ የጥፋትም ውሃ መጥቶ ሁሉንም አጠፋቸው፡፡
[28]«በሎጥ ዘመንም እንዲሁ ነበር፤ ሰዎች ይበሉና ይጠጡ፣ ይገዙና ይሸጡ፣
ተክል ይተክሉና ቤት ይሠሩ ነበር፤ [29]ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ዕለት ግን እሳትና ዲን
ከሰማይ ዘንቦ በሙሉ አጠፋቸው፡፡»

ንግግሩ ከፈሪሳውያን ወደ ደቀ መዛሙርቱ ይለወጣል፤ ርእሰ ጉዳዩ ግን ያው ነው፡- «ይህ ሁሉ መቼ ይሆናል?» በመካከላቸው የሚገኘው ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሀልዎት ቢወክልም እንኳ፣ የመንግሥቱ መገለጥ ከክርስቶስ ሕማማት በኋላ እንጂ አሁን (ቍ. 25) እውን አይሆንም፡፡ በኢየሱስ ትንሣኤ ተፈጽሞአልን? አልተፈጸመም፤ ምክንያቱም የተገለጠው ለጥቂቱ ነው፤ «መብረቅ በርቆ ሰማዩን ከዳር እስከ ዳር እንደሚያበራ» (24) ራሱን አልገለጠም፡፡



ይህ ደግሞ ምጽአቱን ማመልከት አለበት፡፡ ይህ ከማቴዎስ ምዕራፍ 24 ጋር በተጓዳኝ የሚሄድ ነው፡፡ ማቴዎስ 24 ውስጥ ኢየሱስ መብረቅንና ኖኅን አጉልቶ ማሳያ በማድረግ ያቀረበው ገለጻ ዳግም ምጽአቱን ያመለክታል፡፡

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እኛ ክርስቶስ ነን ወይም ክርስቶስን አይተነዋል የሚሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ ሉቃስ ወንጌሉን በጻፈበት ጊዜ እንኳ ኢየሱስ ዳግም መጥቶአል የሚል ወሬ ይነፍስ ነበር (2ተሰ 2፥1-2)፡፡ የንጉሥ ኢየሱስን ክብረ በዓል ለማየት በጣም ስለምንናፍቅ (ቍ. 22) እነርሱን ለመከተል ማዘንበሉ ክፉኛ የሚፈታተን ነው፡፡ ስለሆነም እነርሱን ለመከተል መታለል የለብንም፡፡ ኢየሱስ በሚመጣበት ጊዜ ከዳር እስከ ዳር እንደሚያበራው መብረቅ የሚታወቅ ይሆናል (24)፡፡

እነዚህ ቍጥሮች በቀረው የምዕራፉ ክፍል የሥነ ፍጻሜን ጊዜ ይዘረጋሉ፡፡ ይኸውም አሁን የክርስቶስን ዳግም ምጽአት እየተመለከትን ነው፡፡ ከኢየሩሳሌም መውደም ጋር አያሌ ጉድኝቶች አሉት (ከማቴ 24፤ ከማር 13፤ ከሉቃ 21፥5-38 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሆኖም እዚህ ላይ በራሱ ዐውድ ነው የሚታየው፡፡

ቍጥር 27 እና 28 ውስጥ የሚገኙት ግሶች ሁሉ ቀጣይ ኀላፊ ድርጊትን በማሳየት ኢፍጽመት ናቸው፡፡ በሌላ አባባል ሕይወት ባለፈው መጥፎ እንደ ነበር ሁሉ አሁንም በዚያው መልክ ይቀጥላል፡፡ ሰዎች በዘወትራዊ የሕይወት ሁኔታዎች ያለማቋረጥ ተጠምደው ነበር፡፡ በኖኅ ዘመን እንደ ሆነው ሁሉ የተለመደው ሥራ ይቀጥላል፡፡ የጥፋት ውሃ ድንገት እንደ መጣባቸው ሁሉ ሰዎች ሳያስቡት ክርስቶስ ዳግም ይመጣባቸዋል፡፡ በሎጥ ዘመን እንደ ነበረው ሁሉ የሕይወት ጉዞ እንደ ተለመደው ይቀጥላል፡፡ በሎጥ ዘመን እሳትና ድኝ ድንገት እንደ መጣባቸው ሁሉ ሰዎች ሳያስቡት ክርስቶስ ዳግም

ይመጣባቸዋል:: ኢየሱስ ሳይታሰብና ሳይጠበቅ ድንገት ይመጣል (1ተሰ 5÷2-3፤ 2ጴጥ 3÷8-10)::

ሉቃ 17÷30-33

30«የሰው ልጅ በሚገለጥበትም ቀን እንደዚሁ ይሆናል:: 31በዚያን ቀን በቤቱ ጣራ ላይ ያለ ማንም ሰው በቤቱ ውስጥ ያለውን ንብረት ለመውሰድ አይውረድ፤ እንዲሁም በእርሻ ቦታ ያለ ሰው ወደ ኋላው አይመለስ:: 32የሎጥን ሚስት አስታውሱ:: 33ሕይወቱን ለማሰንበት የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል፤ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያቆያታል::»

«የድንገተኛነት» ዐይነተኛ ሐሳብ (ዋና ሐሳብ) እንደ ቀጠለ ነው:: ኢየሱስ ሳይታሰብ ድንገት ስለሚመጣ ሀብትን (ንብረትን) ለመሰብሰብ እንኳ ጊዜ አይኖርም:: ክርስቶስን የሚወዱ ንብረታቸው የሚያስፈልጋቸው አይሆንም:: ክርስቶስን የማይወዱት በሀብታቸው ከጥፋት አያመልጡም::

ስለዚህ ቍጥር አንድ ማስጠንቀቂያን ቍጥር 30-31 ውስጥ እንሰማለን:- ኢየሱስ ድንገት ስለሚመጣ ንብረትህን ለመሰብሰብ እንኳ ጊዜ አይኖርህም:: ማስጠንቀቂያ ቍጥር ሁለትን ደግሞ ቍጥር 32-33 ውስጥ እንሰማለን:: ለንብረትህ ያለህ ፍቅር ከሚመጣው መንግሥት ውጭ ሊደርግህ ይችላል:: የሎጥ ሚስት የራሷን ከተማ ትወድ ነበር:: ከተማዋ ስትጠፋ ለማየት ዘወር ባለች ጊዜ ድኅነቷን አጣች:: ያው መርሕ አሁንም ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሥራ ላይ ውሎአል:: ይህን ዓለም የሚወዱ ሁሉ በክርስቶስ መግንሥት ቦታ አይኖራቸውም::

ኢየሱስ እነዚህን ሁለት ማስጠንቀቂያዎች አዘውትሮ በሚጠቀሰው ምሳሌ አጠቃለለ:- «ሕይወቱን ለማሰንበት የሚፈልግ ሁሉ ያጣታል፤ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያቈያታል::» ቀደም ሲል ደቀ መዝሙርነት የቱን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል



ለማመልከት፣ ሥነ ምግባራዊ በሆነ መልኩ ይህ አገልግሎት ላይ ውሎ ነበር (ማቴ 10÷39):: ከዚህ ላይ ለሀብት ያለንን ፍቅር አስመልክቶ ተግባር ላይ አዋዋሉ በጣም ተጨባጭ ነው:: መርሑ ያው ነው:- ለማን መገዛት (ታማኝ መሆን) እንዳለብህ መምረጥ ይኖርብሃል:: ለክርስቶስ ነው? ወይስ ለዚህ ዓለም? ወደ ክርስቶስ ከመጣንበት ጊዜ አንሥቶ እርሱ ወደ እኛ እስከሚመጣ ድረስ ይህ የአንድ ደቀ መዝሙር ዋና ጥያቄ ነው::

34«እላችኋለሁ፤ በዚያች ሌሊት ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይተኛሉ፤ አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል:: 35ሁለት ሴቶች አብረው ይፈጫሉ፤ አንዷ ትወሰዳለች፤ ሌላዋ ትቀራለች:: 36ሁለት ሰዎች በእርሻ ቦታ አብረው ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል::»[7]

ሉቃ 17÷34-37

*[7]36 አንዳንድ ቅጆች ቍ 36 የላቸውም*

የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ድንገት ይሆናል:: በቤትና በሥራ ላይ በሚሆን ጉልሕ መለያየት እውን ይሆናል:: ሰው ሁሉ የሚድንበት ብዙ ቤት ይኖራል፤ በአንጻሩም ሰው ሁሉ የሚጠፋበት ብዙ መደብር ይኖራል:: ዋናው ጉዳይ አንድ ክርስቲያን ቤት ውስጥ ያሉትን ሁሉ ሊያድን አለመቻሉ ነው:: ኢየሱስ ዳግም ሲመጣ ሥቃይ የሚበዛበትና አንዱን ከሌላው የሚለይ ፍርድ ይኖራል:: ስለዚህ ከሀብታችን (ከንብረታችን) በላይ ለእርሱ ታማኝ እንድንሆን ጥሪ ያቀርብልናል::[60]

[60] ቍጥር 36 በብዙዎች የጥንት የግሪክ ቅጆች አይገኝም:: በመሆኑም በዘመኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ላይ ተገድፎአል:: እንዲህ ይነበባል፤ «ሁለት ሰዎች በዕርሻ ቦታ አብረው ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል፤ ሌላው ይቀራል

የፍርድ ሐሳብ ምንጊዜም ከዳግም ምጽአት ጋር የተሳሰረ ነው:: እዚህ ላይ ከፍርድ ቤት ተወስዶ በጦር ሜዳ እንዲታይ ተደርጎአል:: ኢየሱስ በሥዕላዊ መልክ የሚያቀርበው ሐሳብ ጅምላ ጭፍጨፋ የተካሄደበትንና በድን የተከማቸበትን መስክ ነው:: መስኩ ላይ ጅምላ ጭፍጨፋ የተካሄደበት በድን ተበታትኖ አሞሮች ሲመገቡት ይታያል:: «በድን ባለበት ስፍራ ሁሉ አሞሮች ይሰበሰባሉ (ማቴ 24÷28):: እንደዚሁም ኀጢአት ባለበት ፍርድ ይኖራል:: ደቀ መዛሙርቱ «የት ነው ጌታ? ... መንግሥት በፍርድ ራሱን የሚገልጥበት የት ነው?» በማለት ጠየቁ: ኢየሱስም፣ «በየትም ቦታ በማንኛውም ቦታ ነው» በማለት መለሰ:: በእርግጥ በአሜሪካ አገር ቤተ ሰቦች ልጆቻቸው እንዳያዩት እንደሚሸሽጉት እንደ PG-13 ሥዕል ዐይነት ነው:: ኢየሱስ በጣም ቊልጭ አድርጎ ዮሐንስ ራእይ ውስጥ ዳግም ለዮሐንስ ሣለለት:-

ከዚያም ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፤ እነሆ አንድ ነጭ ፈረስ ነበረ፤ በፈረሱም ላይ፣ «ታማኝና እውነተኛ» የሚባል ተቀምጦ ነበር፤ እርሱም በጽድቅ ይፈርዳል፤ ይዋጋልም:: ... የሰማይም ሰራዊት ነጭ፣ ንጹሕና ከተልባ እግር የተሠራ ቀጭን ልብስ ለብሰው፣ በነጫጭ ፈረሶች ላይ ተቀምጠው ይከተሉት ነበር:: ሕዝቦችን የሚመታበት ስለታም ሰይፍ ከአፉ ወጣ፤ «በብረት በትርም ይገዛቸዋል::» እርሱም ሁሉን ቻይ የሆነውን የእግዚአብሔርን የብርቱ ቊጣ ወይን መጭመቂያ ይረግጣል:: በልብስና በጭኑ ላይ እንዲህ የሚል ስም ተጽፎአል፤ «የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ::»

---

(ከማቴ 24÷40 ጋር ያነጻ):: ጽሑፉን እንረዳ ዘንድ የእርሱ መታከል ወይም ሳይታከል መቅረት የሚያመጣው ለውጥ የለም::



ቀጥሎም አንድ መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ አየሁ፤ እርሱም በሰማይ መካከል ለሚበሩ ወፎች ሁሉ እንዲህ ሲል በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ «ኑ፤ ወደ ታላቁ የእግዚአብሔር እራት ተሰብሰቡ፤ የምትሰበሰቡትም የነገሥታትን ሥጋ፣ የጦር አዛዦችን ሥጋ፣ የብርቱ ሰዎችን ሥጋ፣ የፈረሶችንና የፈረሰኞችን ሥጋ እንዲሁም የሰዎችን ሥጋ እንድትበሉ ነው::» ... የቀሩት ደግሞ በፈረሱ ላይ ከተቀመጠው አፍ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው በልተው ጠገቡ (ራእ 19÷11:14-18:21)::

## § 121
## ስለ ጸሎት ሁለት ምሳሌዎች
## (ሉቃ 18÷1-14)




ኢየሱስ ከብዙ አጃቢዎች ጋር ከኤፍሬም ወደ ኢየሩሳሌም ረጅሙን ጉዞ ቀጠለ:: በጉዞውም ላይ አስተማረ:: እንዲህ ባለአዓቲው ባንድ ወቅት ስለ ጸሎት ሁለት ምሳሌዎችን ሰጠ:: የመጀመሪያው የቀረበው (የታለመው) ለደቀ መዛሙርቱ ነው:- ጸልዩ፤ አታቋርጡም! ሁለተኛው ምሳሌ የቀረበው ራሳቸውን ጻድቅ ለሚያደርጉት ፈሪሳውያን ነው:: ዋናው ሐሳብ እንደ መጀመሪያው ግልጽ ነው:- በራስ የሚተማመንና ነቀፋ ያለበት ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የለውም::

[1]ደቀ መዛሙርቱ ሳይታክቱ ሁልጊዜ መጸለይ እንደሚገባቸው ለማሳየት ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ ሉቃ 18÷1

ገና ከመጀመሪያው ሉቃስ የዚህን ምሳሌ ትርጉም ይሰጣል:: ይህ ያልተለመደ አቀራረብ ነው፤ ሆኖም ሳያቋርጡ የመጸለይን

አስፈላጊነት ረጋ ብሎ ያስገነዝባቸዋል:: ይሁን እንጂ የምንባቡን ዐውድ ልብ ማለት አለብን:: ኢየሱስ ስለ ዳግም ምጽአቱ መናገሩን ጨርሷል:: ለደቀ መዛሙርቱም፣ «ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ለማየት» እደሚናፍቁ ነግሮአቸዋል (17÷22):: ዳግም ምጽአቱን ሲጠባበቁ ሳለ፣ የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት የሚያጸናቸው ዘወትርና በጽናት የሚደረግ ጸሎት ነው:: ሳንታክት «መጸለይ» አለብን:: በትጋት ማካሄድና መጸለይ አድካሚ ሊሆን ይችላል:: በአጉል ዐይን የሚታዩትንና በሚገባ ያልተያዙትን ደቀ መዛሙርት ደኅንነት ለመጠበቅ ኢየሱስ የሰጠው መፍትሄ በጽናት ሳያቋርጡ መጸለይ ነው (ከ1ተሰ 5÷17 ጋር ያነጻጽሩ)::

ሉቃ 18÷2-5

[2]እንዲህም አላቸው፤ «በአንዲት ከተማ
የሚኖር እግዚአብሔርን የማይፈራና ሰውን የማያከብር
አንድ ዳኛ ነበር:: [3]በዚያችው ከተማ የምትኖር አንዲት
መበለት ነበረች፤ እርሷ ከባላጋራዬ ጋር ስላለብኝ ጉዳይ
ፍረድልኝ እያለች ወደ እርሱ ትመላለስ ነበር::
[4]«ዳኛውም ለተወሰነ ጊዜ አልተቀበላትም ነበር፤ በኋላ ግን በልቡ እንዲህ
አለ፤ ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ፣ ሰውንም ባላከብር፣ [5]ይህች መበለት
ስለምትጨቀጭቀኝ እፈርድላታለሁ፤ አለበለዚያ ዘወትር እየተመላለሰች ታሰለችኛለች::»

ምሳሌው የሚጀምረው ኢፍትሐዊና ጨካኝ በሆነው ዳኛ ላይ ነው:: ኤንደርሽይም የተባለ ጸሐፊ እነዚህን የመንደር ዳኞች የሚገልጻቸው ጊዜ ያለፈባቸው ሹሞች በማለት ነው:: እንዲህ ያሉት ዳኞች በትናንሽ ከተሞች ውስጥ የሰላም አስከባሪ ኀይሎች ሆነው በሮማውያን ተሹመው ነበር:: የፖለቲካ ሥልጣን የሚናፍቁና ጉቦ የሚቀበሉ ብልሹ ሰዎች ናቸው:: ይህች መበለት መጣች:: ሁኔታው ያልተለመደ ነበር:: በዚያን ዘመን ሴቶች በወንድ ጠበቃ ይወከሉ ነበር እንጂ ብቻቸውን ወደ ፍርድ ቤት አይሄዱም:: ይህች ድኻ ሴት ግን



ጉዳይዋን የሚያቀርብላት ሰው አልነበራትም፤ ባል፣ ወንዶች ልጆች ወይም አማቾች አልነበሯትም:: ይህች ምስኪን ሴት ከደንብ ውጭ በመሆንና ራሷን በማዋረድ ዳኛው እንደ ጠበቃ እንዲሆናት ለመነችው:: ማንም የሌላትና በከባድ አደጋ ውስጥ የምትገኝ ሴት ነበረች (ከማር 12÷40፤ ከሉቃ 20÷47 ጋር ያነጻጽሩ):: የነበራት ተስፋ ኢፍትሓዊው ዳኛ ብቻ ነው:: ይህ አሳዛኝ ምስል ነው::[61] ፍትሕ የማግኘቷ ዕድል ጠባብ ቢሆንም ያላት ዕድል ይህ ብቻ ነበር:: ስለዚህ ድርጊቷን በጽናት ቀጠለች:: በመጨረሻም ንዝነዘዋ አሸናፊ ሆነ::

በጥንቷ እስራኤል መበለቶች ተገቢውን አክብሮት አያገኙም ነበር:: የሚያጡት ወይም የሚወስድባቸው ነገር ስላልነበራቸው በጉትጎታ ጉዳያቸውን ለማቅረብ ይችሉ ፍትሕ ለማግኘትም በየቀኑ ለመጮኽ ይችሉ ነበር:: ማኅበረሰባዊ ሚናቸውም ይኸው ነው:: እንዲያ ቢያደርጉም ዕረፍት የለሽ ወትዋቾች ተደርገው አይታዩም:: ይልቁን የማኅበረ ሰቡ አስተማሪዎች ነበሩ:: ድል ያለው በፈላጭ ቈራጩ ንጉሥ ሳይሆን በተገፉት ወገኖች እጅ መሆኑን ለእስራኤል አሳዩ::[62]

«ታሰለቸኛለች» የሚለው በባህሉ መሠረት ሲተረጐም «አንድን ሰው ከዐይኑ ሥር ሰንበር እንዲኖርበት አድርጎ መምታት» ማለት ነው:: «አዋረደችው»[63] ለማለት በምሳሌያዊ አነጋገር የገባ አባባል ነው:: ውትወታዋ በአንዳንድ ረገድ ዳኛውን አዋርዶታል፤ (1) ሥራውን በሚገባ በመወጣት ላይ አለመሆኑን ያሳያል:: ይህ ለእድገቱ እንቅፋት

---

[61] መበለቶች በእጅጉ ለአደጋ የተጋጡ በመሆናቸው ክብካቤ ያደርጉላቸው ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሰዎች አጥብቆ ይመክራል (ዘፀ 22÷22-24፤ ዘዳ 10÷18፤ 24÷17፤ 27÷19፤ ኢዮ 24÷3:21፤ ኢሳ 1÷17፤ 10÷2፤ ኤር 22÷3፤ ሚል 3÷5፤ ማር 12÷40፤ ሐሥ 6÷1፤ 9÷41፤ 1ጢሞ 5÷13-15፤ ያዕ 1÷22)::

[62] ከ V. Matthews and D. Benjamin, *Social World of Ancient Israel* (Peabody, M.A: Hendrickson, 1993), pp 132-141 ጋር ያነጻጽሩ::

[63] J.D.M. Derrett, "Law in the NT: The Unjust Judge." *NTS* 18 (1971-72): 178-191.

ሊሆን ይችላል:: (2) ሰውዬው ኢፍትሐዊ ዳኛ መሆኑን በድርጊቷ አሳየች:: ድርጊቱ ሰውዬው በማኅበረ ሰቡ ዘንድ ያለውን ዝና ያጐድፍበታል:: (3) አያሌ ውድ ጊዜውን አባክናበታለች:: እግዚአብሔርን የማይፈራና የሰዎችንም ሐሳብ የማያከብር ቢሆንም ይህችን ሴት ችላ በማለቱ የሚያመጣበት መዘዝ ግን በጣም ከፍተኛ ነው:: ውሎ ባደረ ቍጥር ከፍ እያለ ነው የሚሄደው::

ሉቃ 18፥6-8

> 6ጌታም እንዲህ አለ፤ «ዐመፀኛው ዳኛ ያለውን
> ስሙ:: 7እግዚአብሔርስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ
> ለሚጮኹ ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? ከመጠን በላይስ
> ችላ ይላቸዋልን? 8እላችኋለሁ፤ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል፤
> ነገር ግን የሰው ልጅ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ላይ
> እምነትን ያገኝ ይሆን?»

ይህ አታላይ በዚህ ምሳሌ እግዚአብሔርን እንዴት ሊወክል ይችላል? አንድ ሰው በጸሎት ከወተወተ የሚፈለገውን ነገር ያገኛል ነው የሚለው ኢየሱስ? ይህ *የማወዳደር* ሳይሆን *የንጽጽር* ምሳሌ ነው:: ኢየሱስ የሚለው ኢፍትሐዊው ዳኛ በጽናት ለሚቀርብለት ልመና (ምልጃ) የሚሸነፍ ከሆነ፣ የፍቅር ባለቤት የሆነው አባታችን አብማ ለ«ምርጦቹ» የቱን ያህል ይሰጣቸዋል? ነው የሚለው (ቍ 7፤ ከማቴ 24፥22፤ ከሮሜ 8፥33፤ ከ1ጴጥ 2፥9፤ ከራእ 17፥14 ጋር ያነ):: የታሪኩ ዋና ሐሳብ የለመንነውን እስከሚሰጠን ድረስ እግዚአብሔርን እንወትውተው የሚል አይደለም:: ዋናው ሐሳብ በምንጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔርን *መወትወታችን አይደለምና* ተስፋ መቍረጥ የለብንም የሚል ነው::

ይህ በኢየሱስ አድማጮች ላይ በመጠኑም ቢሆን ድንጋጤ ይፈጥር ይሆናል:: የአይሁዳውያን ነገረ መለኮት ለፍላጎታችን ስንል



እግዚአብሔርን ብንወተውተው ድርጊታችንን አሳፋሪ እንደ ሆነ አድርጎ ይቈጥረዋል::[64] ኢየሱስ ግን ይህንኑ እንድናደርግ ነግሮናል:: «ለምኑ፤ ... ፈልጉ፤ ... አንኳኩ፤»[65] የሚሉትን ቃላት አስታውሱ:: ከዚያም ያለማቋረጥ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ለማሳየት ጥንድ ምሳሌዎችን ሰጠን (ሉቃ 11፥5-8፤ 18፥1-8):: ይህ በቂ እንዳልሆነ በመቍጠር እንዴት መጸለይ እንደሚኖርብን ራሱ አሳየን (ማቴ 14፥35-42)::

ጸሎታችን መልስ የሚያገኝ ስለ መሆኑ ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቷል:: ፍትሕን በፍጥነት እንቀበላለን:: ይህ ማለት ግን ወዲያውኑ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንቀበላለን ማለት ነው:: ኢየሱስ ዳግም እስከሚመጣ ድረስ ጠብቅ (17፥29-37፤ ከራእ 22፥20 ጋር ያነ):: በማንኛውም ጊዜ ሊሆን ይችላል:: እውን በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ በፍጥነት ይሆናል:: ሀይክስ የተባለው የሥነ መለኮት ሰው የሰጠው ትርጒም ይህን ሐሳብ ለመረዳት ያግዛል:- «የዘገየባቸው ቢመስልም እንኳን ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ የሚጮኹ ምርጦቹን እግዚአብሔር ነጻ አያወጣቸውምን?»[66] ያን ቀን ልንጠባበቅ ነው፤ ግን ቃሌን ልብ በል፤ ያ ቀን ይመጣል፤ እስከዚያው ጸሎትህን ቀጥል!

ኢየሱስ ሲመጣ እምነትን ያገኝ ይሆን? ኢየሱስ ከዳግም ምጽአቱ ጋር በተዛመደ ሁኔታ ስለ ጸሎት መናገሩን እናስተውላለን:: እርግጥ ነው መጠበቅ ይኖርብናል:: የእግዚአብሔርን የጊዜ ሰሌዳ በጸሎት ልናፋጥን አንችልም:: ነገር ግን በሕይወታችን የእርሱን የፍቅር ክብካቤ ዘወትር እናስተውላለን:: ኢየሱስ የሚጠይቀው ጥያቄ

---

[64] Talmud *Berakh* 3:6; 31a.

[65] እነዚህ ሦስት ትእዛዞች ቀጣይ ድርጊትን የሚያሳዩ ሲሆኑ፣ የአሁን ጊዜ ትእዛዛዊ አንቀጾች ናቸው:: ኢየሱስ ስለ ጸሎት ሲያስተምር የኀላፊ ጊዜን ትእዛዛዊ አንቀጽ ከዳር እስከ ዳር የተጠቀመ መሆኑ ይህ ይበልጥ ይገርማል::

[66] J.M. Hicks, "The Parable of the Persistent Widow (Luke 18:1-8)" *RestQ* 33 (1991): 209-223.

«እስከምመለስ ድረስ በጸሎት ታማኝ ትሆናለህን? ይቻልሃልን (ይሳካልሃልን)?» የሚል ነው:: ይህ ጥያቄ እስከዚህ ዕለት ድረስ መልስ አላገኘም:: ከኢየሱስ ይልቅ እኛ በደንብ የምንመልሰው ብቸኛ ጥያቄ ይህ ሊሆን ይችላል:: እንግዲህ ይህ የእኛ ጉዳይ ነው:: ጌታችን እስኪመለስ ድረስ ታማኞች እንሆናለንን?

ሉቃ 18÷9-12

9ራሳቸውን እንደ ጻድቃን በመቍጠር ሌሎችን በንቀት
ዐይን ለሚመለከቱ ሰዎች እንዲህ ሲል ይህን ምሳሌ
ነገራቸው፤ 10«ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ ቤተ መቅደስ
ወጡ፤ አንዱ ፈሪሳዊ፣ ሌላው ቀረጥ ሰብሳቢ ነበረ:: 11ፈሪሳዊውም ቆሞ ስለ[ኘ] ራሱ
እንዲህ ይጸልይ ነበር፤ «እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ቀማኛ፣
ዐመፀኛ፣ አመንዝራ፣ ይልቁንም እንደዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ ባለመሆኔ አመሰግንሃለሁ፤
12በሳምንት ሁለት ጊዜ እጾማለሁ፤ ከማገኘውም ሁሉ ዐሥራት አወጣለሁ::»

[ኘ]11 ወይም ለራሱ

ኢየሱስ ኢፍትሐዊ ስለ ሆነው ዳኛ ተናግሮአል:: ራሱን ጻድቅ የሚያደርግን ምእመን ንስሐ ከሚገባ ኀጢአተኛ ጋር በማነጻጸር ላይ ነው:: ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት ብቃት እንዳላቸው ያስባሉ:: ከሃይማኖታዊ ድርጊታቸው የተነሣ እግዚአብሔርን የመጠየቅና ሌሎችን የመናቅ (የማጣጣል) መብት አለን ብለው ያምናሉ (ከሉቃ 18÷30፤ ከማቴ 23÷5-7፤ ከማር 7÷6፤ ከፊል 3÷4-6 ጋር ያነ)::

ፈሪሳዊው «ስለ ራሱ ጸለየ» (ወይም ይበልጥኑ በትክክል ሲገለጽ «ወደ ራሱ ጸለየ»):: ይህ ሰው ጸሎቱ ሳይመለስለት ወደ ቤቱ የተመለሰበት ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ወደ ራሱ በመጸለዩ ነው:: አንዳች ነገር ከቶ አልጠየቀም:: ያደረገው ነገር ቢኖር በጸሎቱ ውስጥ አምስት ጊዜ «እኔ» የሚለውን ቃል በመደጋገም የቱን ያህል



ድንቅ ሰው እንደ ሆነና ቀረጥ ሰብሳቢው ምንኛ መጥፎ ሰው ስለ መሆኑ ዘገባ ማቅረብ ነው:: መንፈሳዊ «ብቃቱን» በቀላሉ ለመዘርዘር ይችላል:: በሳምንት ሁለት ጊዜ ይጾማል፤ ዐሥራቱንም በጥንቃቄ ይከፍላል (ከ11÷42 ጋር ያነጻጽሩ):: ፈሪሳውያን ሰኞንና ኀሙስን ይጾማሉ:: ሕጉ የሚጠይቀው በዓመት ውስጥ አንድ ጾም ብቻ ነው (ከዘሌ 26÷29፤ ከዘኍ 29÷7 ጋር ያነ):: ነገር ግን ገበያ የሚውለው በእነዚህ ቀኖች በመሆኑ ሰዎች ወደ ከተማ ይመጣሉ:: ልዩ የምኵራብ ሥርዐት ይካሄድ ነበር፤ ሸንጎውም ይሰበሰብ ነበር:: ትኵረትን ለመሳብ ይህ አመች ጊዜ ነበር::

ይህ የፈሪሳዊያን የታወቀ የልብ ዝንባሌ (ሐሳብ) ነበር (ነውም):: ራባይ ሳይመን ቤት ጆቻይ የተባሉ ሰው «በዓለም ውስጥ ሁለት ጻድቃን ሰዎች ካሉ እኔ ልጄ እነዚህ ሁለት ሰዎች ነን፤ አንድ ጻድቅ ብቻ ካለ ደግሞ ያ ሰው እኔ ነኝ!» ብለዋል::

ሉቃ 18÷13-14

13«ቀረጥ ሰብሳቢው ግን በርቀት ቆሞ፣ ወደ
ሰማይ ቀና ብሎ ማየት እንኳ አልፈለገም፤ ነገር ግን
ደረቱን እየደቃ 'እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ኀጢአተኛውን
ማረኝ' ይል ነበር::
14«እላችኋለሁ፤ ከፈሪሳዊው ይልቅ ይኸኛው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ
ጻድቅ ተቈጥሮ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤
ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል::»

ቀረጥ ሰብሳቢው በንጽጽር የሚታይ ነው:: በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም የማይገባው ሰው መሆኑን ተገንዝቦ በሩቁ ቆሞአል:: የተለመደውን የአይሁድ የጸሎት አቀራረብ ተከትየና ቆሜ ወደ ሰማይ ቀና በማለት ለመጸለይ ብቃት የለኝም አለ:: ይህ ሰው እንደ ተቈጡት ልጅ የአባቱን ዐይኖች ለማየት እንኳ ፈቃደኛ አይደለም:: ፈሪሳዊው

በሩቁ ቁሞ በዚህ ቀረጥ ሰብሳቢ ላይ ሲኵሳተር፣ ቀረጥ ሰብሳቢው ቆሞ ደረቱን ይደቃል:: ወደ ራሱ በመጸለይ ፈንታ፣ ወደ እግዚአብሔር ይጸልያል:: ልመናው (ምልጃው) ግልጽ ነው፤ «እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔን ኀጢአተኛውን ማረኝ» የሚል ነበር:: የግሪኩ ጽሑፍ መስተአምር አለውና «ኀጢአተኛውን» ተብሎ መነበብ አለበት:: ፈሪሳዊው ራሱን ከፍ በማድረግ ጻድቅ ሰው ነኝ ሲል፣ ቀረጥ ሰብሳቢው ራሱን ዝቅ በማድረግ ኀጢአተኛ ነኝ አለ::

ሁለቱም ከልብ የጸለዩበትን ነገር ያገኛሉ:: ቀረጥ ሰብሳቢው ጻድቅ ሆነ፤ ፈሪሳዊው ግን ምንም አላገኘም:: የጠየቀው በትክክል ይህንኑ ነበር:: የሚፈልገውም ይህንኑ ነው በማለት አስቧል:: ሉቃስ ለድኾችና ለጠፉት ርኅራኄ እንድናደርግ (5÷12:27፤ 7÷34:37፤ 15÷1-2፤ 16÷20) ፈሪሳዊውኑንም እንድንንቅ (5÷17፤ 6÷2:7፤ 7÷39፤ 11÷37-54፤ 15÷2፤ 16÷14)[67] ስላዘጋጀን የዚህ ታሪክ ተጽዕኖ አይሰማን ይሆናል:: በኢየሱስ ዘመን ግን የዚህ ምሳሌ ተገላቢጦሽ አስደንጋጭ ይሆን ነበር:: በእኛም ዘመን እንዲሁ ነው:: እግዚአብሔር የማንን ጸሎት እንደሚቀበል በትክክል ከተረዳን ድንጋጤ እንዲያድርብን የተደረግን ሊመስለን ይችላል::

**§ 122**
**ፍች እንደ ጋብቻ ሳያገቡ መቅረት**
**(ማቴ 19÷1-12 ማር 10÷1-12፤ ሉቃ 16÷18 ጋር ያነጻጽሩ)**

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በሚጓዝበት ጊዜ በዙሪያው የሚሰበሰበው ሕዝብ በየዕለቱ እየበዛ ሄደ:: ፈሪሳውያን ሁልጊዜ ከኋላ ይሸሽጉና አንድ ጥያቄ ይዘው ወደ ፊት ይመጣሉ:: የሚፈልጉት መልስን ሳይሆን

[67] በሉቃስ የገጸ ባሕርይ አቀራረጽ ላይ ፈሪሳውያንና ቀረጥ ሰብሳቢዎች ተቃራኒዎች ናቸው (3÷12-13፤ 5÷27-30፤ 7÷34፤ 15÷1፤ 18÷11-13፤ 19÷2:10):: በባህል ረገድ ፈሪሳውያን ነጭ ባርኔጣ ሲደፉ፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ደግሞ ጥቊር ባርኔጣ ይደፉ ነበር:: ሉቃስ ግን አለዋውጦአቸዋል (cf. A.M. Okorie, "The Characterization of Tax Collectors in The Gospel of Luke," *CurTM* 22/1 [1995]: 27-32.



ኣጋጣሚ ነው:: የፍችን ጉዳይ አስታከው ኢየሱስን በጋብቻ ጉዳይ ሊያጠምዱት ፈለጉ:: ሁሉም ጸጥ አለ:: ጆሮ ሁሉ አቆበቆበ፤ ዐይኖች ሁሉ ወደ ኢየሱስ አተኰሩ:: ቃሎቹ እንደ ተለመደው አስገራሚዎች ናቸው:: ፍችን በተመለከተ በሴቶች ላይ ብቻ ተጥሎ የነበረውን ፍጹም ዕገዳ ለመጀመሪያ ጊዜ በወንዶቹም ላይ እውን እንዲሆን አደረገ:: እንደ ፈሪሳውያን የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የሚፈልጉ ወንዶች ከሚያደርሱባቸው ጥቃት በመታደግ ወደር ያልተገኘለትን ጥበቃ ለሴቶች ሰጣቸው::

**ማቴ 19÷1-3 ከማር 10÷1 ጋር**

1 ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ፣ ገሊላን ትቶ ከዮርዳኖስ ማዶ ወዳለው ወደ ይሁዳ አውራጃ ሄደ:: 2 ብዙ ሕዝብም ተከተለው፤ በዚያም ፈወሳቸው::
3 ፈሪሳውያንም ሊፈትኑት ቀርበው፣ «ለመሆኑ አንድ ሰው በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን መፍታት ተፈቅዶለትን?» ሲሉ ጠየቁት::

ከሁለተኛ ዓመት አገልግሎቱ ጀምሮ ኢየሱስ ብዙ ተከታዮችን የማፍራቱን ያህል ፈሪውያንንም ይማርክ ነበር:: ፈሪሳውያኑ ደቀ መዛሙርት ሳይሆኑ፣ ነገር አቀባዮችና ይፋ ጠላቶች ነበሩ:: ሸንጎው ኢየሱስን ለመግደል በይፋ ያሤሩ በመሆኑ (ዮሐ 11÷53) ከወር ባልበለጠ ጊዜም ይታሠር ዘንድ «ማዘዣ» በማስተላለፋቸው (ዮሐ 15÷57) ይህ ይበልጥኑ እውነት ነው:: አስቀድሞውኑ ኢየሱስን ወደዚህ እንዲመጣ ያደረገውም ይኸው ነው (ዮሐ 11÷54፤ ሉቃ 17÷15)::

ጥያቄያቸው የታለመው ኢየሱስን ለማጥመድ ነው (ከማቴ 16÷1፤ ከማ 10÷2፤ ከሉቃ 11÷53 ጋር ያነ):: የፍች ጉዳይ የተጧጧፈ ክርክር አስነስቷል:: እንዲያውም ታልሙድ የአይሁዳውያን ባህልና ሕግጋት የተሰኘው መጽሐፍ «ጊቴን» - Gittin በሚል ርእስ ለዚህ

ጉዳይ አንድ ሙሉ ምዕራፍ መድቦለታል:: ከሁለት ወር ቀደም ብሎ ኢየሱስ ይህን ጉዳይ በይሁዳ ምድር አንሥቶ ነበር፤ ያን ጊዜ ግን ጉዳዩን ለክርክር ለማቅረብ ዕድል አልነበረም (ሉቃ 16÷14:18):: አሁን ግን ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር ተጋፈጡ፤ ይህን ጉዳይ በማንሳት ውዝግብ ገጠሙት:: በዚህ ጊዜ ጉዳዩ ለውይይት ክፍት ሆነ::

ፍችን በተመለከተ የፈሪሳውያን ሐሳብ በሁለት ጐራዎች የተከፈለ ነበር:: አንዱ ወገን ሄሌል የተባለውን ሰው አስተሳሰብ ሲከተል ሌላው ወገን ሽማይን የተባለውን ሰው አስተሳሰብ ይከተል ነበር (ሁለቱም ከብዙ ዐሥርተ ዓመታት በፊት ሞተዋል):: ሂሌል ሚስት በማንኛውም ምክንያት[68] ባሏን ለማስደሰት ባትችል ባል ሊፈታት ይችላል ይላል:: እንዲያውም አኪባ የተባለው የሂላል ደቀ መዝሙር አንድ ወንድ የላቀ ውበት ያላት ሴት ካገኘ ሚስቱን ለመፍታት ይችላል ይላል::[69] ሽማይ ግን አንድ ወንድ ሚስቱን ሊፈታ የሚችለው አስጸያፊ የወሲብ ነውር ሲያገኝባት ብቻ ነው ይላል:: ኢየሱስ ምንም ዐይነት መልስ ቢሰጥ ግማሹ ያህሉ ሕዝብ መቆጣቱ አይቀርም::

ከሂሌል ይልቅ የሽማይ አተያይ ወደ ኢየሱስ ሐሳብ ይቀርባል:: የሂሌልና የሽማይ ሀሳብ ግን በጣም ይራራቃሉ:: በመጀመሪያ ነገር ፍችን በተመለከተ የሽማይ ነገረ መለኮት የተመሠረተው በዘዳግም 24÷1-4 ላይ ነው:: የኢየሱስ አስተምህሮ ግን በዘፍጥረት 1-2 ላይ ነው

[68] በሂላውያን ደንብ መሠረት ለፍች አጥጋቢ የሆኑት ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:- (1) የባልን እራት ማሳረር፣ (2) ራሷን ሳትሸፍን በአደባባይ መውጣት፣ (3) ከወንዶች ጋር መነጋገር፣ (4) በአውራ ጐዳና ላይ መፍተል (ማዳወር)፣ (5) በባሏ ፊት አገቡኞቿን በማዋረድ መናገር፣ (6) ጨቅጫቃ ወይም ጠብ ጫሪ ስትሆን፣ (7) በዐሥር ዓመታት ውስጥ ልጅ ሳትወልድ ስትቀር::

[69] ፈሪሳዊና ፊት የነበረው ኢዮሳፍስ በሂላል አመለካከት ቡድን ውስጥ በመሆኑ በማንኛቸውም ዐይነት ምክንያት ፍቺ የሚቻል ነው ብሎ ያምን ነበር (Ant. 4:253)::



የተመሠረተው:: ሁለተኛ ሽማይ የሚያተኩረው በወንዶች ሕጋዊ የመፍታት መብት ላይ ሲሆን፣ ኢየሱስ የሚያተኩረው ግን ወንዶችና ሴቶች ባለባቸው መንፈሳዊ ግዴታ ላይ ነው:: ሦስተኛ አይሁድ ፍጹም መብት ነው ብለው በሚመለከቱት በዳግም ጋብቻ ላይ ማዕቀብ የጣለ ኢየሱስ ብቻ ነው::

መጥምቁ ዮሐንስ ሕይወቱን እንዲያጣ ያደረገው ይኸው ጉዳይ መሆኑንም ልብ ማለት አለብን (ማቴ 14÷3-12):: ፈሪሳውያን ከኢየሱስ ጋር ፊት ለፊት የተገናኙት በዮሐንስ «የማጥመቂያ ስፍራ» ላይ ነው (ከዮሐ 10÷40-41፤ ከሉቃ 17÷11 ጋር ያነ):: ዮሐንስ እንዳደረገው እንዲናገር ማድረግ ቢችሉ ኖሮ እርሱም የዮሐንስ ዕጣ ይደርስበት ነበር:: ያም ፈሪሳውያንን ያስደስታቸው ነበር::

ማቴ 19÷4-6

[4]እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ «ፈጣሪ
በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደ ፈጠራቸው
አላነበባችሁንም? [5]እንዲህም አለ፤ 'ሰው አባቱንና
እናቱን ይተዋል፤ ከሚስቱም ጋር ይጣመራል፤ ሁለቱም
አንድ ሥጋ ይሆናሉ' የተባለው በዚህ ምክንያት አይደለምን? [6]ከእንግዲህ አንድ ሥጋ
ናቸው እንጂ ሁለት አይደሉም፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን ያጣመረውን ሰው አይለየው::»

ኢየሱስ ከብርቱ ጦርነት ከቶ አፈግፍጎ አያውቅም:: በጣም አስቸጋሪና አገርን ዳር እስከ ዳር በሚያዳርስ ጉዳይ ፍልሚያ ገጠሙት:: እርሱም ፊት ለፊት ተጋፈጣቸው:: የመልሱ መግቢያም፣ «አላነበባችሁምን?» የሚል ጥያቄ ነበር (ማቴ 12÷3-5፤ 21÷16:42፤ 22÷31፤ ማር 12÷10:26):: ይህም ማንበብ ብቻ ሳይሆን ብዙውን ቶራ በቃላቸው ይዘው ለነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን የሚያበሳጭ ነበር::